## ማውጫ ፡

# የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

# የባሕር ፡ ሕግ ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ መርከብ ፡

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፩ | ስለ ፡ መርከብ ፡ ትርጓሜ ። .... .... .... .... | ፩ |
| ፪ | ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎች ። . .... .... .... .... | ፩ |
| ፫ | መርከብ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። .... .... | ፩ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **ስለ ፡ መርከብ ፡ ዜግነት ።** | |
| ፬ | ለኢትዮጵያዊ ፡ መርከቦች ፡ ባለቤትነት ፡ በቂ ፡ ስለ ፡ መሆን ። | ፩ |
| ፭ | እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መርከቦች ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ መርከቦች ። | ፪ |
| ፮ | ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መርከቦች ። .... .... .... .... .... | ፪ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፫ ።** | |
| | **ስለ፡መርከብ ፡ ባለሀብትነት ።** | |
| ፯ | የመርከብ ፡ ባለሀብትነት ። .. .... .... .... .... | ፪ |
| ፰ | ስለ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ።.. .... .... .... | ፪ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፬ ።** | |
| | **ስለ ፡ መርከብ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ።** | |
| ፱ | የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ መብት ፡ .... .... .... .... | ፪ |
| ፲ | የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ግዴታ ። .. .... .... .... .... | ፫ |
| ፲፩ | መርከብ ፡ አከራይ ፡ የሆነው ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ሥልጣን ። | ፫ |
| ፲፪ | የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ድርሻ ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። .... .... .... | ፫ |
| ፲፫ | የሌሎች ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ። | ፫ |
| ፲፬ | የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ መርከብ ፡ ስለ ፡ መሸጥ ። | ፬ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## መርከቡን ፡ መያዣ ፡ ስለማድረግና ፡ በሱም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሚሰጥ ፡ ልዩ ፡ መብት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ።


| ቍጥር | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፲፭ | ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ዝርዝር ፡ ተራ ። | ፬ |
| ፲፮ | ልዩ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በየመርከቡ ፡ ጕዞ ፡ ተራ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። .. .... .... .... .... | ፭ |
| ፲፯ | ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ጕዞ ፡ የሚመለከቱ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅያ ፡ መብቶች ፡ ተራ ፡ አሰጣጥ ። .... .... .... | ፭ |
| ፲፰ | ካንዱ ፡ የባሕር ፡ አደጋ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ቀን ፡ አቈጣጠር ። .... .... .... | ፮ |
| ፲፱ | ስለ ፡ ማስረጃ ። .... .... .... .... .... | ፮ |
| ፳ | መያዣ ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራ ። ... .... .... .... .... .... .... | ፮ |
| ፳፩ | በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ። | ፮ |
| ፳፪ | የመርከብ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣሪያና ፡ የጭነት ፡ ትርጓሜ ። | ፮ |
| ፳፫ | እንደ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወይም ፡ ከመርከቡ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ከጭነቱ ፡ ውጭ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ያህል ፡ የሚቈጠሩ ፡ ገንዘቦች ። ... .... .... .... .. | ፯ |
| ፳፬ | በመርከቡ ፡ የጭነቱ ፡ ዋጋዎችና ፡ በተጨማሪ ፡ መሣሪያዎች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ተቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ። .... .... .... .... .... .... | ፯ |
| ፳፭ | መርከቡን ፡ የሚከተል ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ። | ፯ |
| ፳፮ | ስለ ፡ ይርጋ ። . .... .... .... .... .... | ፯ |
| ፳፯ | የቀደምትነት ፡ መብት ፡ የሚቀርበት ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ። .... .... .... .... .... .... | ፰ |
| ፳፰ | የቀዳሚነትን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ። .... .... | ፱ |
| ፳፱ | መርከቡን ፡ የሚያካሂደው ፡ ባለሀብቱ ፡ ያልሆነበት ፡ ጊዜ ። | ፱ |


### ክፍል ፡ ፪ ።

### መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።


| ቍጥር | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፴ | መያዣ ፡ የማድረጉ ፡ ወሰን ። .... .... .... .... . | ፱ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፴፩ | መያዣ ፡ ስጪ ፡፡ | ፲ |
| ፴፪ | መያዣ ፡ ስለሚሆኑት ፡ ንብረቶች ፡፡ | ፲ |
| ፴፫ | ገና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መርከብ ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡፡ | ፲፩ |
| ፴፬ | የአፈጻጸሙ ፡ ፎርም ፡፡ | ፲፩ |
| ፴፭ | የወለድን ፡ ልክ ፡ መወሰን ፡፡ | ፲፩ |
| ፴፮ | የአመዘጋገቡ ፡ ሥርዐት ፡፡ | ፲፩ |
| ፴፯ | የመመዝገቡ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡፡ | ፲፪ |
| ፴፰ | መያዣ ፡ የሆነውን ፡ መርከብ ፡ ስለ ፡ ማስያዝና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡፡ | ፲፪ |
| ፴፱ | መያዣዎቹን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ፡፡ | ፲፫ |
| ፵ | ከዋጋው ፡ በላይ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ስለ ፡ መጨመር ፡፡ | ፲፫ |
| ፵፩ | ሐራጅ ፡ የሚጠይቅ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋውን ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ፡፡ | ፲፬ |
| ፵፪ | ስለ ፡ ሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡፡ | ፲፬ |
| ፵፫ | መርከቡ ፡ መያዣ ፡ የሆነበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያመለክት ፡ አጭር ፡ ሰሌዳ ፡፡ | ፲፬ |
| ፵፬ | በኢትዮጵያ ፡ ን/ ነ/ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ መያዣ ፡ የሆነውን ፡ መርከቡ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ እንዳይሸጥ ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡፡ | ፲፬ |


## ምዕራፍ ፡ ፯ ፡፡

### ስለ ፡ መርከቡ ፡ አመዘጋገብና ፡ መርከቡን ፡ ስለሚመለከቱ ፡፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ አጻጻፍ ፡፡


| | | |
|---|---|---|
| ፵፭ | ስለ ፡ መዝገቦች ፡፡ | ፲፬ |
| ፵፮ | የመርከብ ፡ መለያ ፡ ምልክት ፡፡ | ፲፭ |
| ፵፯ | የኢትዮጵያ ፡ መርከቦች ፡ አመዘጋገብ ፡፡ | ፲፭ |
| ፵፰ | የመርከቡ ፡ መመዝገብ ፡ የሚሰረዝበት ፡ ሁኔታ ፡፡ | ፲፭ |
| ፵፱ | ያልተመዘገበ ፡ መርከብ ፡ የሚያዝበት ፡ ሁኔታ ፡፡ | ፲፭ |
| ፶ | የመርከቡ ፡ መመዝገብ ፡ የሚያስከትለው ፡ ሁኔታ ፡፡ | ፲፮ |
| ፶፩ | የአመዘጋገቡ ፡ ፍጹም ፡ አስረጂነት ፡፡ | ፲፮ |
| ፶፪ | የአመዘጋገቡን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መሰረዝና ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ፡፡ | ፲፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **ምዕራፍ ፡ ፯ ።** | |
| | **ስለ ፡ መርከቡ ፡ መያዝ ።** | |
| | **ክፍል ፡ ፩ ።** | |
| | **ለመጠባበቂያ ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።** | |
| ፺፫ | ሁኔታዎች ። | ፲፯ |
| ፺፬ | ዋስትናዎችን ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ መያዣዎችን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ። | ፲፯ |
| ፺፭ | መርከቡ ፡ እንዲያዝ ፡ የታዘዘበትን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ። | ፲፯ |
| ፺፮ | የመቅረቢያ ፡ ጥሪ ። | ፲፰ |
| ፺፯ | የማጽናት ፡ ፍርድ ። | ፲፰ |
| | **ክፍል ፡ ፪ ።** | |
| | **ፍርድን ፡ ስለ ፡ ማስፈጸም ።** | |
| ፺፰ | ፍርድን ፡ ለማስፈጸም ፡ እንዲጠበቅ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ። | ፲፰ |
| ፺፱ | ስለ ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ጕዳይ ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻልበት፡ ሁኔታ። | ፲፰ |
| ፻ | የመክፈል ፡ ጥያቄ ። | ፲፰ |
| ፻፩ | ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ እንዲጠበቅ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ። | ፲፱ |
| ፻፪ | በፍርድ ፡ ማስፈጸሚያው ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ መረጃዎች ። | ፲፱ |
| ፻፫ | ማስታወቂያና ፡ ጥሪ ። | ፲፱ |
| ፻፬ | ፕሮሴቬርባሉን ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ። | ፳ |
| ፻፭ | በመዝገብ ፡ ለተጻፉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ። | ፳ |
| ፻፮ | የሐራጅ ፡ ሽያጭ ። | ፳ |
| ፻፯ | ሐራጅ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ማመልከት ። | ፳፩ |
| ፻፰ | በቍ/ ፻፯ ፡ ለተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አፈጻጸም ፡ የማመልከቻዎቹ ፡ አቀራረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ። | ፳፩ |
| ፻፱ | የተያዘ ፡ መርከብ ፡ ሽያጭ ። | ፳፩ |
| ፻፲ | የመግለጫዎቹና ፡ የተለጣፊ ፡ ማስታወቂያዎቹ ፡ አገላለጽ ። | ፳፩ |
| ፻፲፩ | የዋጋ፡ ማበላለጥ፡ ጨረታ ፡ ማድረግን ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ መከልከል ። | ፳፪ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፸፪ | የጨረታውን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ። .... .... .... | ፷፪ |
| ፸፫ | በተገኘ ፡ ዋጋ ፡ በሐራጅ ፡ እንደገና ፡ ስለመሸጥ ። .... .... | ፷፪ |
| ፸፬ | የአቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ። .... .... .... .... | ፷፪ |
| ፸፭ | የሐራጅ ፡ ጨረታውን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ። | ፷፪ |
| ፸፮ | የሐራጁ ፡ ሽያጭ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። .... .... | ፷፫ |
| ፸፯ | የገንዘቡ ፡ መከፋፈል ። .... .... .... .... | ፷፫ |

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ መርከቡ ፡ ባለሀብቶች ፤ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ ስለ ፡ ካፒቴኑ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ መርከቡ ፡ ባለሀብቶችና ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ አላፊነት ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፸፰ | የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ትርጓሜ ። .... .... .... | ፷፫ |
| ፸፱ | በባለሀብቱ ፡ ላይ ፡ ኀላፊነትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ነገሮች ። | ፷፫ |
| ፹ | የኀላፊነት ፡ ወሰን ። .... .... .... .... .... | ፷፫ |
| ፹፩ | የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ባለይዞታ ፤ ጠባቂ ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪ ፡ በመሆን ፡ የሚመጣ ፡ ኀላፊነት ። .... .... .... | ፷፬ |
| ፹፪ | ኀላፊነትን ፡ መወሰን ፡ የማይቻልበት ፡ ሁኔታ ። | ፷፭ |
| ፹፫ | ስለ ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ። .... .... .... .... .... | ፷፭ |
| ፹፬ | ኀላፊነትን ፡ ስለ ፡ አለመቀበል ። .... .... .... .... | ፷፭ |
| ፹፭ | የተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ አወሳሰን ። | ፷፭ |
| ፹፮ | ለተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚከፈል ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ | ፷፮ |
| ፹፯ | ሥነ ፡ ሥርዐት። .... .... .... .... .... .... | ፷፯ |
| ፹፰ | የመርከቡ ፡ ክብደት ፡ የሚታሰብበት ፡ ሁኔታ ። | ፷፯ |
| ፹፱ | ስለ ፡ መርከቡ ፡ መያዝ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ። | ፷፯ |
| ፺ | ስለ ፡ መርከቡ ፡ ኀላፊነት ። .... .... .... .... | ፷፰ |
| ፺፩ | የመርከቡ ፡ ባለሀብቶች ፡ ባልሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ። .... .... .... | ፷፰ |
| ፺፪ | በመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ። | ፷፰ |
| ፺፫ | የጭነታቸው ፡ ክብደት ፡ ከ፫፻ ፡ ቶን ፡ ያነሱ ፡ መርከቦች ። | ፷፰ |

ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ካፒቴኑ ።

፺፬ የካፒቴኑ ፡ ሹመትና ፡ ተግባር ። .... .... .... ፳፱
፺፭ የካፒቴኑ ፡ ሹመት ፡ የሚያልቅበት ፡ ሁኔታ ። ፳፱
፺፮ የካፒቴኑ ፡ ሥልጣን ። .... .... .... .... .... ፳፱
፺፯ የካፒቴኑ ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ። ፳፱
፺፰ የካፒቴኑ ፡ ኀላፊነት ። .... .... .... .... .... ፴
፺፱ የካፒቴኑ ፡ ግዴታዎች ። .... .... .... .... ፴
፻ በመርከቡ ፡ አንዳድ ፡ እረገድ ፡ ካፒቴኑ ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ። ፴
፻፩ ስለ ፡ መርከቡ ፡ መንዳት ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ። ፴
፻፪ የመርከብ ፡ ሰነዶች ።.. .... .... .... .... .... ፴
፻፫ የመርከቡ ፡ የዕለት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብና ፡ የመርከቡ ፡ ሞተር ፡
መዝገብ ። .... .... .... .... .... .... ፴፩
፻፬ መርከቡ ፡ ከወደብ ፡ ሲደርስ ፡ በመዝገቦቹ ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡
ስለ ፡ ማድረግ ። .... .... .... .. ፴፩
፻፭ የባሕር ፡ ዴክላራሲዮን ። .... .... .... .... ፴፩
፻፮ የባሕር ፡ ዴክላራሲዮን ፡ ምርመራ ። .... .... .... ፴፩
፻፯ አስቸኳይ ፡ ነገር ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ካፒቴኑ ፡ ስለሚያደር
ገው ፡ የጭነቱን ፡ ዕቃ ፡ አስይዞ ፡ መበደር ፡ ወይም ፡ መሸጥ ። ፴፩
፻፰ መርከቡ ፡ የባሕር ፡ ጕዞውን ፡ ለመቀበል ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡
ካፒቴኑ ፡ ሊሸጠው ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ። .... .... ፴፪
፻፱ ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ በባሕር ፡ የሚጓዝ ፡ ካፒቴን ። .... .... ፴፪
፻፲ የመርከቡ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ የሆነውን ፡ ካፒቴን ፡ ከሥራው ፡
ስለ ፡ ማሰናበት ። .... .... .... .... ፴፪

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## የባሕር ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንበት ፡ ደንብ ።

፻፲፩ የመርከበኛ ፡ ትርጓሜ ። .... .... .... .... .... ፴፫
፻፲፪ መርከበኛ ፡ የሚቀጠርበት ፡ ውል ። .... .... .... .... ፴፫
፻፲፫ የመቀጠሪያው ፡ ውል ፡ አገላለጽ ። .... .... .... .... ፴፫
፻፲፬ ከትርፉ ፡ ገቢ ፡ ወይም ፡ ከጭነቱ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ የሚከፈል ፡ የአ
ገልግሎት ፡ ዋጋ ። .... .... .... .... .... ፴፫

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፻፲፭ | በየጕዞው ፡ የሚታሰብ ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ። . .... .... | ፵፬ |
| ፻፲፮ | የመርከበኛው ፡ ግዴታ ። .... .... .... .... . | ፵፬ |
| ፻፲፯ | በራሱ ፡ ሒሳብ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ እንዳይጭን ፡ ክልክል ፡ ስለመሆኑ ። .. .... .... .... .... .... .... | ፵፬ |
| ፻፲፰ | ከደመወዝ ፡ አስገድዶ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ። .... .... . | ፵፭ |
| ፻፲፱ | ስለ ፡ ቤት ፡ ሰብ ፡ አበል ። .... .... .... .... .... | ፵፭ |
| ፻፳ | አስቀድሞ ፡ ከደመወዝ ፡ ላይ ፡ የተወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መመለስ ። .... .... .... .... .... .... | ፵፭ |
| ፻፳፩ | ደመወዝን ፡ ስለ ፡ መያዝ ። . .... .... .... .... | ፵፭ |
| ፻፳፪ | ከመቀጠር ፡ በፊት ፡ የሚደረግ ፡ የሐኪም ፡ ምርመራ ። .... | ፵፮ |
| ፻፳፫ | በመርከብ ፡ አገልግሎት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መታመም ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መቍሰል ። ... .... ........ .... .... | ፵፮ |
| ፻፳፬ | ለታመመው ፡ ወይም ፡ ለቈሰለው ፡ መርከበኛ ፡ የሚከፈል ፡ ደመወዝ ፡ ወይም ፡ ዳረጎት ። .... .... .... .... | ፵፮ |
| ፻፳፭ | ወደ ፡ አገሩ ፡ ስለ ፡ መመለስ ። .... .... .... .... | ፵፮ |


## አንቀጽ ፡ ፬ ።

## በመርከብ ፡ ለመገልገል ፡ ስለሚደረጉ ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ባዶ ፡ መርከብ ፡ ስለማከራየት ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፻፳፮ | ትርጓሜ ። .... .... .... .... .... ... ... | ፵፮ |
| ፻፳፯ | አሳልፎ ፡ ማከራየት ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። .... .... | ፵፯ |
| ፻፳፰ | የአከራዩ ፡ ግዴታ ። .... .... .... .... .... | ፵፯ |
| ፻፳፱ | የአከራዩ ፡ ኀላፊነት ። .... .... .... .... .... | ፵፯ |
| ፻፴ | የተከራዩ ፡ ግዴታዎች። .... .... .... .... | ፵፯ |
| ፻፴፩ | ውሉ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ። .... .... .... .... | ፵፯ |
| ፻፴፪ | ውሉን፡ የሚመለከቱ፡ መብቶች ፡ በይርጋ ፡ የሚታገዱበት፡ ጊዜ ። | ፵፯ |


### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ጭነት ፡ ኪራይ ፡ ውል ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፻፴፫ | ትርጓሜ ። .... .... .... .... .... .... | ፵፱ |
| ፻፴፬ | በውሉ ፡ የሚገለጸው ፡ አጻጻፍ። .... .... .... .... | ፵፱ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፻፷፭ | ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ ስለ ፡ ማከራየት ። | ፺ |
| ፻፷፮ | ለጭነት ፡ በተከራየው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ተከራዩ ፡ ስለሚጭናቸው ፡ ዕቃዎች ። | ፺ |
| ፻፷፯ | መርከቡን ፡ በተከራዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ስለ፡ ማድረግ ። | ፺ |
| ፻፷፰ | የመርከብ ፡ አከራይ ፡ ግዴታ ። | ፺ |
| ፻፷፱ | አከራዩ ፡ ከአላፊነት ፡ የሚድንበት ፡ ሁኔታ ። | ፺ |
| ፻፸ | የተከራዩ ፡ አላፊነት ። | ፺፩ |
| ፻፸፩ | የመድረሻ ፡ ወደብ ። | ፺፩ |
| ፻፸፪ | በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ መርከቡን ። በተከራዩት ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ስላለማድረግ ። | ፺፩ |
| ፻፸፫ | ለተከራዩ ፡ የሚገባው ፡ ካሣ ። | ፺፪ |
| ፻፸፬ | የጭነት ፡ ውል ፡ የሚሠረዝበት ፡ ሁኔታ ። | ፺፪ |
| ፻፸፭ | የመርከቡ ፡ መሸጥ ። | ፺፪ |
| ፻፸፮ | ስለ፡ ክስ ፡ ይርጋ ። | ፺፪ |


## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፻፸፯ | በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሊከፈል ፡ ስለሚገባው፡ የጭነት ፡ ዋጋ ። | ፺፫ |
| ፻፸፰ | የጭነት ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ። | ፺፫ |
| ፻፸፱ | የሚበላሹ ፡ የንግድ፡ ዕቃዎች ። | ፺፬ |
| ፻፹ | ካፒቴኑ ፡ ከጭነቱ ፡ ዋጋ፡ ሒሳብ ፡ በላይ፡ በተቀዳሚነት ፡ የወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ መልሶ ፡ የሚከፍልበት ፡ ሁኔታ ፡ | ፺፬ |
| ፻፹፩ | በጕዞ ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ መርከብ ፡ | ፺፬ |
| ፻፹፪ | ለመድረሻ ፡ ከተመደበላቸው ፡ ቦታ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ለተሰጡ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የሚከፈል ፡ የጭነት ፡ ሒሳብ ። | ፺፬ |
| ፻፹፫ | በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዕቃዎች ፡ በፍጹም ፡ አሟልቶ ፡ ስላለመጫን ። | ፺፬ |
| ፻፹፬ | የተጫኑትን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ በመልቀቅ ፡ የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ አልከፍልም ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ መከልከል ። | ፺፭ |
| ፻፹፭ | የአከራዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ። | ፺፭ |
| ፻፹፮ | የአከራዩ ፡ ጭነቱን ፡ ለመያዝ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ስለ፡መሆኑ፡ | ፺፭ |

ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡


፻፶፯ ዐይነታቸው ፡ ፍጹም ፡ አንድ ፡ ከሆኑ ፡ ከሌሎች ፡ የንግድ ፡ ዕቃ
ዎች ፡ ጋራ ፡ የተቀላቀሉ ፡ ዕቃዎች ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡
አጠባበቅ ። .... .... .... .... .... .... ፺፭


## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መጫኛና ፡ ማራገፊያ ፡ ጊዜና ፡ ስለ ፡ ተጨ ማሪ ፡ ጊዜ ።


፻፶፰ የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ ( ሌይ ፡ ዲይስ ፡ ) ፺፮
፻፶፱ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ( ዲመረጅ ፡ ) .... .... .... .... .... ፺፮
፻፷ ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ .... .... .... .... .... ፺፮
፻፷፩ የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ ( ሌይ ፡ ዲይስ ፡ ) አቈጣጠር ፡ ፺፮
፻፷፪ የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ የሚጀመርበት ። ፺፮
፻፷፫ ለማራገፊያና ፡ ለመጫኛ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡
ያለው ፡ የካፒቴኑ ፡ መብት ። .... .... .... .... ፺፯
፻፷፬ የመጫኛውንና ፡ የማራገፊያውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ ፺፯
፻፷፭ የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ መቈጠርን ፡ የሚያግዱ ፡ ምክ
ንያቶች ። .. .... .... .... .... .... .... .... ፺፯
፻፷፮ ስለ ፡ ማፍጠን ፡ የሚሰጥ ፡ ጕርሻ ። .... .... .... .... ፺፯
፻፷፯ ማቻቻል ። .... .... .... .... .... .... .... .... ፺፰
፻፷፰ ቀዳሚ ፡ መብትና ፡ ይርጋ ። .... .... .... .... .... ፺፰
፻፷፱ ስምምነት ፡ ያልተደረገባቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜና ፡ ሁለተኛ ፡
ተጨማሪ ፡ ጊዜ ። .... .... .... .... .... .... ፺፰


## ክፍል ፡ ፬ ።

## ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሚደረግ ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ። ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።


፻፸ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸም ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ ፺፰
፻፸፩ የአከራዩ ፡ ግዴታዎች ። .... .... .... .... .... ፺፰
፻፸፪ የተከራዩ ፡ ግዴታዎች ። .. .... .... .... .... .... ፺፰
፻፸፫ የኪራዩ ፡ ዕዳ ። .... .... .... .... .... .... .... ፺፱
፻፸፬ እንደ ፡ ጠፋ ፡ የሚቈጠር ፡ መርከብ ። .... .... .... ... ፺፱

| ቍጥር ፡ | እርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
| --- | --- | --- |
| ፻፷፭ | የመርከቡ ፡ መዘግየት ። .... .... .... .... ... | ፺፱ |
| ፻፷፮ | ሒሳቡ ፡ ያልተከፈለው ፡ አከራይ ፡ መብት ። .... .... | ፺፱ |
| ፻፷፯ | ተከራዩ ፡ የሚፈጽመው ፡ የውል ፡ ማራዘም ፡ ጕዳይ ። | ፺፱ |
| ፻፷፰ | መርከቡን ፡ ስለ ፡ መመለስ ። .... .... .... .... .... | ፻ |
| ፻፷፱ | የመርከቡን ፡ የንግድ ፡ ሥራና ፡ የባሕር ፡ ጕዞውን ፡ ጕዳይ ፡ በመ ምራት ፡ ሥራውን ፡ በአላፊነቱ ፡ የሚያከናውን ፡ ተከራይ ። | ፻ |

ክፍል ፡ ፰ ።

በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ የተረጋገጠ ።

የማመላለሻ ፡ ውልን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።

| ቍጥር ፡ | እርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
| --- | --- | --- |
| ፻፸ | የድንጋጌዎች ፡ ወሰን ። .... .... .... .... .... .... | ፻ |
| ፻፸፩ | የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። .. .... | ፻፩ |
| ፻፸፪ | በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፈው ። | ፻፩ |
| ፻፸፫ | የጭነት ፡ ምልክት ። . .... .... .... .... .... .... | ፻፩ |
| ፻፸፬ | ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ የሰጣቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆኑ ፡ መግለጫዎች ። | ፻፪ |
| ፻፸፭ | ዐውቆ ፡ የተደረገ ፡ አነስተኛ ፡ መግለጫ ። .... .... .. | ፻፪ |
| ፻፸፮ | ዕቃው ፡ ከመጫኑ ፡ በፊት ፡ የተሰጠ ፡ ደረሰኝ ። .... .... | ፻፪ |
| ፻፸፯ | ዋና ፡ የሆኑ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኞች ። .... .... | ፻፪ |
| ፻፸፰ | የተባዛ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ። .... .... ... | ፻፪ |
| ፻፸፱ | የጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ዐይነት ። .... .... .. | ፻፫ |
| ፻፹ | የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ መዘዋወር ። . .... .... | ፻፫ |
| ፻፹፩ | ማስተላለፍ ፡ ስለ ፡ መከልከል ። .... .... .... .... .... | ፻፫ |
| ፻፹፪ | ደረሰኞቹን ፡ በያዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ ፡ ክርክር ። | ፻፫ |
| ፻፹፫ | ቅን ፡ ልቡና ፡ ላለው ፡ ያዥ ፡ ዕቃውን ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ። | ፻፫ |
| ፻፹፬ | በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝና ፡ በመርከቡ ፡ ኪራይ ፡ ውል ። ስምምነት ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ ፡ ክርክር ። .... ... | ፻፫ |
| ፻፹፭ | የማስረከብ ፡ ትእዛዝ ፡ .... .... .... .... .... .... | ፻፬ |
| ፻፹፮ | የአመላላሹ ፡ ግዴታዎች ፡ .... .... .... .... .... ... | ፻፬ |
| ፻፹፯ | የአመላላሹ ፡ አላፊነት ፡ .... .... .... .... .... .... | ፻፬ |
| ፻፹፰ | በሕግ ፡ የሚወሰን ፡ የአላፊነት ፡ ግምት ፡ ... .... .... | ፻፮ |
| ፻፹፱ | ያልተገለጹ ፡ ወይም ፡ በትክክል ፡ ባልሆነ ፡ ዐይነት ፡ የተገ ለጹ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ .... .... .... .... .... | ፻፮ |
| ፻፺ | አደገኛ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ .... .... .... .... .... | ፻፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፩ | ዕቃው ፡ ሲጠፋ ፡ ወይም ፡ ሲበላሽ ፡ ለአመላላሹ ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ። | ፶፯ |
| ፪፻፪ | የማመላለሻውን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ። | ፶፯ |
| ፪፻፫ | ስለ ፡ ይርጋ ። | ፶፯ |
| ፪፻፬ | በቀጥታ ፡ የሆነ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ። | ፶፯ |
| ፪፻፭ | በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ውስጥ ፡ አመላላሹ ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ፡ ተብሎ ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ የማይጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፶፰ |
| ፪፻፮ | ዕቃ ፡ አመላላሽ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ለማብዛት ፡ ነጻነት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፶፰ |
| ፪፻፯ | ስለ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ። | ፶፰ |
| ፪፻፰ | ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። | ፶፱ |
| ፪፻፱ | ጉዳዩን ፡ በሽማግሌ ፡ ዳኛ ፡ በግልግል ፡ ለመፈጸም ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ። | ፶፱ |


## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መንገደኞች ፡ ማመላለስ ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፲ | ትርጓሜ ። | ፶፱ |
| ፪፻፲፩ | የመሳፈሪያውን ፡ ወረቀት ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። | ፶፱ |
| ፪፻፲፪ | የመንገደኛው ፡ የምግብ ፡ ሒሳብ ። | ፶፱ |
| ፪፻፲፫ | የመሳፈሪያ ፡ ወረቀት ፡ የሌለው ፡ መንገደኛ ። | ፷ |
| ፪፻፲፬ | በመንገደኛው ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ ጕዞ ። | ፷ |
| ፪፻፲፭ | ለመነሻ ፡ በተወሰነው ፡ ሰዓት ፡ ያልቀረበ ፡ መንገደኛ ። ... | ፷ |
| ፪፻፲፮ | የውል ፡ መፍረስ ። | ፷ |
| ፪፻፲፯ | በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የጕዞውን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ። | ፷ |
| ፪፻፲፰ | ጕዞው ፡ በመቅረቱ ፡ ምክንያት ፡ ውሉ ፡ ስለ ፡ መፍረሱ ። | ፷፩ |
| ፪፻፲፱ | ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አጋጣሚ ፡ ኀይል ፡ ጕዞውን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ። | ፷፩ |
| ፪፻፳ | ከራሱ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ጕዞውን ፡ ለማቋረጥ ፡ ስለሚገደድ ፡ መንገደኛ ። | ፷፩ |
| ፪፻፳፩ | ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ያዘው ፡ መንገደኛ ። | ፷፪ |
| ፪፻፳፪ | ስለ ፡ ጕዞው ፡ መዘግየት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ ያለመፈጸም ፡ አመላላሹ ፡ ያለበት ፡ አላፊነት ። | ፷፪ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፳፫ | ባንድ ፡ መንገደኛ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስ ፡ አላፊነት ። .... .... .... .... | ፷፪ |
| ፪፻፳፬ | ስለ ፡ መንገደኞቹ ፡ ዕቃ ፡ አጫጫን ። .... .... .... | ፷፪ |
| ፪፻፳፭ | ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ ማመላለሽ ። .... .... .... | ፷፫ |
| ፪፻፳፮ | ከቍጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፪፻፳፭ ፡ የቀነገሩት ፡ ድንጋጌዎች፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ስለ፡ መሆናቸው ። ..... .... | ፷፫ |
| ፪፻፳፯ | በመንገደኞቹ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ አመላላሹ ፡ ያለው ፡ የመያዣ ፡ መብት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፷፫ |
| ፪፻፳፰ | ስለ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ። .... .... .... .... .... .... | ፷፫ |

አንቀጽ ፡ ፭ ።

ስለ ፡ ግጭት ፡ ስለ ፡ ርዳታና ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ከአደጋ ፡ ማዳን ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ግጭት ።

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፳፱ | ግጭት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ደንቦች ። | ፷፬ |
| ፪፻፴ | ድንገተኛ ፡ ግጭት ። .... .... .... .... .... .... | ፷፬ |
| ፪፻፴፩ | ከመርከቦቹ ፡ ባንዱ ፡ ጥፋት ፡ የተደረገ ፡ ግጭት ። | ፷፬ |
| ፪፻፴፪ | የሁለት ፡ ወይም ፡ የብዙ ፡ መርከቦች ፡ የጋራ ፡ ጥፋት ። | ፷፬ |
| ፪፻፴፫ | በነጂ ፡ ጥፋት ፡ የሚደረግ ፡ ግጭት ። ..... .... .... | ፷፭ |
| ፪፻፴፬ | የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ወሰን ። ..... .... .... .... .... | ፷፭ |
| ፪፻፴፭ | የካፒቴኖቹ ፡ ግዴታዎች ። ..... .... .... .... .... | ፷፭ |
| ፪፻፴፮ | ሥነ ፡ ሥርዐት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፷፭ |
| ፪፻፴፯ | ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። | ፷፭ |
| ፪፻፴፰ | ይርጋ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፷፮ |

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ርዳታ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ከአደጋ ፡ ማዳን ።

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፴፱ | በርዳታና ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ በማዳን ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ደንቦች ። ... .... .... .... .... .... .... .... | ፷፮ |
| ፪፻፵ | የሥራ ፡ ዋጋ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፷፮ |
| ፪፻፵፩ | በግድ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የማዳን ፡ ተግባር ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ ሁኔታ ። ..... .... .... | ፷፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፵፪ | ሀብትነታቸው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ በሆኑ ፡ መርከቦች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ መረዳዳት ። ..... .... .... .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፫ | የመጐተትና ፡ የመንዳት ፡ ልዩ ፡ ርዳታ ። .... .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፬ | ሰዎችን ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ማዳን ። ..... .... .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፭ | የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ አወሳሰን ። .. .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፮ | የርዳታ ፡ ስምምነትን ፡ በፍርድ ፡ ስለ ፡ መሻር ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፯ | የሥራ ፡ ዋጋ ፡ አወሳሰን ። .... .... .... .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፰ | በመጥፋት ፡ አደጋ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ የመርዳት ፡ ግዴታ ። ..... .... .... .... .... .... | ፷፯ |
| ፪፻፵፱ | ስለ ፡ አገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ። | ፷፰ |
| ፪፻፶ | በመንግሥት ፡ መርከቦች ፡ ላይ ፡ የርዳታ ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ። | ፷፰ |


## አንቀጽ ፡ ፯ ።

### የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።


| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፶፩ | የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተግባር ። .... .... .... .... ... | ፷፰ |
| ፪፻፶፪ | ኪሣራውን ፡ የሚከፍለው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆን ። .... .... | ፷፰ |
| ፪፻፶፫ | ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተግባር ፡ በቀጥታ ፡ የተገኙ ፡ ኪሣራዎች ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መፈቀዳቸው ። ..... .... .... .... .... .... | ፷፰ |
| ፪፻፶፬ | የማይፈቀዱ ፡ ጉዳቶችና ፡ ኪሣራዎች ። .... .... .... | ፷፰ |
| ፪፻፶፭ | የአንደኛው ፡ ወገን ፡ ጥፋት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ። | ፸ |
| ፪፻፶፮ | የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ማስረጃ ። .... .... .... .... .... | ፸ |
| ፪፻፶፯ | ልዩ ፡ ወጪ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፸ |
| ፪፻፶፰ | ኪሣራንና ፡ መዋጮን ፡ ስለ ፡ ማስተካከል ። | ፸ |
| ፪፻፶፱ | የመርከቡን ፡ ጭነት ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ስለ ፡ መጣል ። | ፸ |
| ፪፻፷ | የመርከቡን ፡ ጭነት ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ በመጣልና ፡ ለጋራ ፡ ደኅንነት ፡ በተደረገ ፡ ሁኔታ ፡ የመጣ ፡ ጉዳት ። .... .... | ፸ |
| ፪፻፷፩ | ቃጠሎን ፡ በማጥፋት ፡ ስለሚደረግ ፡ አደጋ ። .... .... | ፸፩ |
| ፪፻፷፪ | ከአደጋ ፡ የተረፉትን ፡ የመርከቡን ፡ ክፍሎች ፡ በመቍረጥ ፡ ስለ ፡ ማስተካከል ። .... .... .... .... .... | ፸፩ |
| ፪፻፷፫ | ሆን ፡ ብሎ ፡ መርከቡን ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ። | ፸፩ |
| ፪፻፷፬ | ከመጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ የሸራ ፡ መዘርጋት ፡ የሚደርስ ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ። ..... .... .... .... .... .... | ፸፩ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፪፻፷፭ | ስለ ፡ መኪናዎችና ፡ ማፍሊያዎች ፡ መበላሸት ። ..... .... | ፹፪ |
| ፪፻፷፮ | ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ?ወጣውን ፡ መርከብ ፡ ለማራገፍና ፡ መልሶ ፡ ለመጫን ፤ የሚደረግ ፡ ወጪና ፡ ኪሣራ ። .... .... | ፹፪ |
| ፪፻፷፯ | እንደ ፡ ነጻጅ ፡ ሆነው ፡ ለተቃጠሉ ፡ የመርከብ ፡ ዕቃዎችና ፡ ሥንቆች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፹፪ |
| ፪፻፷፰ | ባንድ ፡ መጠጊያ ፡ ወደብ ፡ ለመግባት ፡ የሚደረግ ፡ ወጪ ። | ፹፪ |
| ፪፻፷፱ | መርከቡ ፡ በተጠጋበት ፡ ስፍራ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ወጪና ፡ ስለ ፡ መርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ የኑሮ ፡ ወጪና ፡ ደሞዝ ፡ | ፹፬ |
| ፪፻፸ | ጭነቱ ፡ በሚራገፍበት ፡ ጊዜ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፹፭ |
| ፪፻፸፩ | ከማደስ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ቅናሽ ። .... .... | ፹፭ |
| ፪፻፸፪ | ለጊዜው ፡ የተደረገ ፡ የመርገብ ፡ መታደስ ። .... .... .... | ፹፮ |
| ፪፻፸፫ | ለመርከብ ፡ ኪራይ ፡ የተቈረጠው ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ መጥፋቱ ። | ፹፮ |
| ፪፻፸፬ | በዕቃው ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ የቢዛነት ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መጥፋት ። በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰበው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ። | ፹፮ |
| ፪፻፸፭ | ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሚከፈል ፡ ድርሻ ፡ አወሳሰን ። .... .... | ፹፱ |
| ፪፻፸፮ | መርከቡ ፡ ስለሚያገኘው ፡ ጉዳት ። .... .... .... .... | ፹፱ |
| ፪፻፸፯ | መግለጫ ፡ ያልተደረገባቸው ፡ ወይም ፡ በትክክል ፡ ያልተገለጹ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ። .... .... .... .... .... | ፺ |
| ፪፻፸፰ | በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰብ ፡ ኮሚሲዮን ። .... .... | ፺ |
| ፪፻፸፱ | በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ወጪ ፡ ስለ ፡ ተከፈሉ ፡ ገንዘቦች ፡ ወለድ ። | ፺ |
| ፪፻፹ | የተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ አያያዝ ። .... .... .... .... | ፺ |
| ፪፻፹፩ | ለጋራ ፡ ጉዳትን ፡ በየድርሻው ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ መቻል ። .... | ፺፩ |
| ፪፻፹፪ | ለጋራ፡ ጉዳት፡ መዋጮ ፡ ለማድረግ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ስላለመቀበል ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፺፩ |
| ፪፻፹፫ | ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ ቀዳሚ ፡ መብት ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፺፩ |
| ፪፻፹፬ | የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ አመዳደብ ። .... .... .... | ፺፪ |
| ፪፻፹፭ | አከፋፋዮች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፺፪ |
| ፪፻፹፮ | ወጪዎችና ፡ የሥራ ፡ ዋጋዎች ። .... .... .... | ፺፪ |
| ፪፻፹፯ | ስለ ፡ ድርሻ ፡ አከፋፈል ፡ የሚደረግ ፡ ክስ ፡ ይርጋ። .... .... | ፺፪ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| | **አንቀጽ ፡ ፺ ።** | |
| | **ስለ ፡ ኢንሹራንስ ።** | |
| | **ምዕራፍ ፡ ፩ ።** | |
| | **የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡** | |
| ፪፻፹፰ | የዚህ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ወሰን ። .... .... .... .... | ፹፫ |
| ፪፻፹፱ | የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፎርም ። .... .... .... .... | ፹፫ |
| ፪፻፺ | ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የሚደረግ ፡ ተቀዳሚ ፡ ስምምነት ፡ ( ካበርኖት ፡ ) | ፹፫ |
| ፪፻፺፩ | በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ሊነገር ፡ የሚገባው ። .... .... .... | ፹፫ |
| ፪፻፺፪ | ኢንሹራንስ ፡ ሊደረግላቸው ፡ የሚቻል ፡ ነገሮች ። | ፹፬ |
| ፪፻፺፫ | በኢንሹራንስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ስለ ፡ መግባት ። | ፹፬ |
| ፪፻፺፬ | በመሥራት ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን፡ መርከብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ስለ ፡ ማስገባት ። | ፹፬ |
| ፪፻፺፭ | መርከቡን ፡ በሚመለከት ፡ ሁኔታ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉት ፡ አደጋዎች ፡ አቈጣጠር ፡ መጀመሪያ ። ..... .... .... .... | ፹፬ |
| ፪፻፺፮ | በጕዞ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኘው ፡ መርከብ ። .... .... .... | ፹፬ |
| ፪፻፺፯ | የሸቀጦችን ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ ስለ ፡ መወሰን ።.... .... .... | ፹፭ |
| ፪፻፺፰ | በንግዱ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ አደጋዎች ፡ አቈጣጠር ፡ መጀመር ። . .... .... .... .... .... | ፹፭ |
| ፪፻፺፱ | ውሉን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ። ..... .... .... .... .... | ፹፭ |
| ፫፻ | ስላለመግለጽና ፡ አሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ መስጠት ። | ፹፮ |
| ፫፻፩ | ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ መክበዱ ። | ፹፮ |
| ፫፻፪ | ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ መፍረስ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፹፮ |
| | **ምዕራፍ ፡ ፪ ።** | |
| | **ኢንሹራንስ ፡ የገባውና ፡ የኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።** | |
| ፫፻፫ | የደረሱትን ፡ ጉዳትና ፡ መጥፋት ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ስለ ፡ መቻሉ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፹፮ |
| ፫፻፬ | ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሲባል ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተገባባቸው ፡ ዕቃዎች ። | ፹፮ |
| ፫፻፭ | አስገዳጅ ፡ በሆነ ፡ የመንገድ ፡ መለወጥ ፡ ምክንያት ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውጤት ፡ ስላለመቅረቱ ።.... .... .... .... | ፹፮ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፮ | በአስገዳጅ ፡ ምክንያት ፡ የመንገድ ፡ መለወጥን ፡ የሚመስሉ ፡ ሁኔታዎች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፹፯ |
| ፫፻፯ | ጕዞን ፡ ስለ ፡ ማሳጠር ። .... .... .... .... .... | ፹፯ |
| ፫፻፰ | ሌሎች ፡ የጕዞ ፡ የመንገድ ፡ ወይም ፡ የመርከብ ፡ መለወጥ ፡ ጕዳዮች ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፹፰ |
| ፫፻፱ | ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ጥፋቶች ፡ ስለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ በኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ላይ ፡ አላፊነት ፡ ስለ ፡ አለመኖሩ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፹፰ |
| ፫፻፲ | ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ የራሱ ፡ ጕድለት ። | ፹፰ |
| ፫፻፲፩ | ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ በሌሎች ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚያደርጋቸው ፡ ጉዳቶች ። ..... .... .... .... | ፹፰ |
| ፫፻፲፪ | በጦርነት ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ አደጋዎች ፡ ስለማስወገድ ። | ፹፰ |
| ፫፻፲፫ | ኢንሹንስ ፡ ከተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ ለሚበልጥ ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ የስምምነት ፡ ውል ። | ፹፱ |
| ፫፻፲፬ | ከዕቃው ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ የተደረገ ፡ ኢንሹራንስ ። | ፹፱ |
| ፫፻፲፭ | ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ በብዙ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ የሚጠበቅ ፡ ሲሆን ። | ፹፱ |
| ፫፻፲፮ | ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ ላይ ፡ በመብቶቹ ፡ ስለሚሠራበት ፡ ሁኔታ ። | ፹፱ |
| ፫፻፲፯ | ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ከጠፉ ፡ ወይም ፡ ከቦታው ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ የተደረገ ፡ ውል ። | ፺ |
| ፫፻፲፰ | ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ የሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ። | ፺ |
| ፫፻፲፱ | ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ ጉዳቶች ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ገንዘብ ፡ ( ፕሬሚየም ፡ ) እጅ ፡ ስለማድረጉ ። | ፺፩ |
| ፫፻፳ | ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ። | ፺፩ |
| ፫፻፳፩ | ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ያጠባበቅ ፡ ጥንቃቄዎች ። .... .... .... .... .... .... .... | ፺፩ |
| ፫፻፳፪ | ግዴታዎችን ፡ ባለመፈጸም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ አላፊነት ። . .... .... .... .... .... .... .... | ፺፩ |
| ፫፻፳፫ | ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ መብቶች ፡ የንኢሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መዳረግ ። .... .... .... .... .. | ፺፩ |
| ፫፻፳፬ | ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረጉ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውሎች ። | ፺፩ |

ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡
---|---|---

፫፻፹፭ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጥቅም ፡ ሳይገልጹ ፡ ስለ ፡ መቅረት ። ፺፪
፫፻፹፮ ሀብታቸው ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ የሆኑ ፡ መርከቦች ፡ መጋጨት ፡ ወይም ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ። ..... .... .... .... .... ፺፪

ምራዕፍ ፡ ፫ ።
የጉዳቶች ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡
ክፍል ፡ ፩ ።
ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ።

፫፻፹፯ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ የኪሣራ ፡ ልክ ። ፺፫
፫፻፹፰ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የሚያቀርባቸው ፡ ማስረጃዎች ። ፺፫
፫፻፹፱ ስለ ፡ ካሣ ፡ አከፋፈል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ። ..... .... .... ፺፬

ክፍል ፡ ፪ ።
በደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ መጠን ፡ ኪሣራ ፡ ስለ ፡
መክፈል ።

፫፻፺ በደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ መጠን ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፈልበት ፡ ሁኔታ ። ፺፬
፫፻፺፩ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለትን ፡ ዕቃ ፡ በቀጥታ ፡ ለሚነኩ ፡ ጉዳቶች ፡ የኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ግዴታ ፡ አወሳሰን ። ፺፬
፫፻፺፪ ከአዲሱ ፡ ላይ ፡ አሮጌውን ፡ ስለ ፡ መቀነስ ። .... .... .... ፺፬
፫፻፺፫ የሠራተኞች ፡ ደመወዝና ፡ ጥቅም ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ የማይታሰብ ፡ በመሆኑ ። .... .... .... .... ፺፭
፫፻፺፬ በተጫኑት ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... ፺፭
፫፻፺፭ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የሚከፍለው ፡ ድርሻ ፡ .... .... .... .... .... .... ፺፭

ክፍል ፡ ፫ ።
ስለ ፡ መተው ።

፫፻፺፮ የመተውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ስለ ፡ መወሰን ። .... .... .... ፺፭
፫፻፺፯ መርከብ ፡ ስለሚተውባቸው ፡ ሁኔታዎች ። ..... .... .... ፺፭
፫፻፺፰ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መተው ። .... .... .... .... ፺፮
፫፻፺፱ የመርከብን ፡ ኪራይ ፡ ስለ ፡ መተው ። .... .... .... ፺፮
፫፻፵ በወሬ ፡ መጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የሚደረግ ፡ ተግባር ። .... ... ፺፮
፫፻፵፩ በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ መርከቡን ፡ ወይም ሸቀጦቹን ፡ ስለ ፡ መተው ። .... .... .... .... .... ፺፮

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
| --- | --- | --- |
| ፫፻፷፪ | ተቀባይነት ፡ የሌለው ፡ መተው ። .... .... .... .... | ፺፯ |
| ፫፻፷፫ | የመተውን ፡ ጊዜ ፡ ማለቅ ፡ የሚቃወም ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊ ። | ፺፰ |
| ፫፻፷፬ | ስለ ፡ መርከቡ ፡ ጭነት ፡ ኪራይ ፡ ልዩ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሁኔታዎች ። | ፺፰ |
| ፫፻፷፭ | ስለ ፡ መተው ፡ ዐይነት ። .... .... .... .... .... | ፺፰ |
| ፫፻፷፮ | ያደረጋቸውን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወቅ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ግዴታ ። .... .... .... .... | ፺፰ |
| ፫፻፷፯ | የመተው ፡ ውጤቶች ። .... .... .... .... .... .... | ፺፰ |

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ይርጋ ።

| | | |
| --- | --- | --- |
| ፫፻፷፰ | ከኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ የሚመነጭ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይርጋ ፡ | ፺፰ |
| ፫፻፷፱ | ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ ( ፕሪሚየም ) አከፋፈል ፡ ክስ ፡ | ፺፱ |
| ፫፻፸ | ስለ ፡ መተው ፡ ተግባር ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።.... .... .... | ፺፱ |
| ፫፻፸፩ | ስለ ፡ ደረሰ ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ። .... .... | ፺፱ |
| ፫፻፸፪ | በመርከቡና ፡ በመርከቡ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መነሻ ።.... ... | ፺፱ |
| ፫፻፸፫ | በሸቀጦቹና ፡ በሸቀጦቹ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚያሠጋ ፡ አደጋ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መነሻ ። .... .... | ፺፱ |
| ፫፻፸፬ | ያለ ፡ አግባብ ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ። ..... .... .... .... .... .... | ፻ |
| ፫፻፸፭ | ይርጋው ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻ |
| ፫፻፸፮ | የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ። ..... .... .... .... | ፻ |

አንቀጽ ፡ ፰ ።

የወንጀል ፡ ድንጋጌዎች ።

| | | |
| --- | --- | --- |
| ፫፻፸፯ | በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ መርከቡ ፡ እንዲፈተሽ ፡ በማድረግ ፡ ባለሀብቱን ፡ ስለመጉዳት ። ..... .... .... .... .... | ፻ |
| ፫፻፸፰ | በመጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ምክንያት ፡ በሰው ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ሥጋት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ። | ፻ |
| ፫፻፸፱ | ጠቅላላ ፡ ወንጀሎች ። ..... .... .... .... .... .... | ፻፩ |
| ፫፻፹ | ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ የመርከቡን ፡ ካፒቴን ፡ ሥልጣን ፡ መቀማት ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ እንዳይሠራ ፡ ስለማድረግ ። .... .... .... .... .... .... .... .... | ፻፩ |

| ቍጥር ፡ | አርእስት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፷፩ | ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ መርከብ ፡ መተው ። .... .... .... | ፻፪ |
| ፫፻፷፪ | ከመርከቡ ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ ጥፋቶች ። | ፻፪ |
| ፫፻፷፫ | ግጭት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ግጭቱን ፡ ሳያስተውሉ ፡ ስለ ፡ መቅረት ። .... .... .... .... .... .... .... | ፻፪ |
| ፫፻፷፬ | መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችልበትን ፡ ሁኔታ ፡ ሳያረጋግጥ ፡ የቀረ ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ ካፒቴን ። .... .... ......... .... .... .... .... | ፻፪ |
| ፫፻፷፭ | ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ። ..... .... .... .... .... ..... .... .... | ፻፫ |
| ፫፻፷፮ | በቂ ፡ ችሎታ ፡ ሳይኖረው ፡ የመርከብ ፡ ረዳት ፡ ካፒቴን ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ መሥራት ። .... .... .... .... .... .... | ፻፫ |
| ፫፻፷፯ | ስለ ፡ ዲስፕሊን ፡ ጥፋቶች ። .... .... .... .... .... | ፻፫ |
| ፫፻፷፰ | ስለ ፡ ቅጣቶች ። .... .... .... .... .... .... | ፻፫ |
| ፫፻፷፱ | ሌሎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ። | ፻፫ |

አንቀጽ ፡ ፱ ።

ልዩ ፡ ልዩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ፫፻፸ | ትርጓሜ ። .... .... .... .... .... .... | ፻፫ |
| ፫፻፸፩ | ደንብ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ ሥልጣን ። .... .... .... | ፻፬ |

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

# የባሕር ፡ ሕግ ።

## ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍ ፡ ፩/ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተለይ ፡ የወጣ ።

አዲስ ፡ አበባ ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ በ፴፩ኛው ፡
ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

# መ ቅ ድ ም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፤

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ የጥንቱ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ወደብ ፡ ስለተ መለሰልንና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የባሕር ፡ ኀይላችን ፡ ስለ ፡ ተስፋፋ ፡ የባሕር ፡ ነክ ፡ ለሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ዘመናዊ ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኗል ። የዚህንም ፡ ሥራ ፡ አስቸኳይነት ፡ በመገንዘብ ፡ ከስድስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮናችን ፡ እንዲሰበሰብና ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ፍላጎት ፤ ለወደፊቱም ፡ የወደቦቻችን ፡ መስፋፋት ፡ ለባሕር ፡ አገልግሎት ፡ ጽኑና ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ የሚሆን ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ የሚወጣበትን ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ እንዲያቀርብ ፡ መሪ ፡ ትእዛዛችንን ፡ ሰጥተን ፡ ነበር ።

የፍትሐ፡ ነገሥት፡ ኮሚሲዮንም፡ ይህ፡ የባሕር ፡ ሕጋችን፡ ከሌሎች፡ የባሕር፡ ኀያላን፡ መንግሥታት ፡ ሕጎችና ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠባቂነት ፡ ከተዘጋጀው ፡ ስምምነት ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ እንዲሆን ፡ በሰፊው ፡ ደከሞበታል ። ይህ ፡ ዛሬ ፡ የምናውጀው፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ ግላዊ ፡ የሆነውንና ፡ በጠቅላላውም ፡ የባሕርን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከ

ቱት ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ተደንግገውበታል ። እንደዚሁም ፡ ኑሯቸው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እን ዲሆን ፡ የመረጡ ፡ መርከበኞቻችን ፡ ከሁሉ ፡ በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ የሚተዳደሩበት ፡ ድን ጋጌ ፡ ያለበትን ፡ ሕግ ፡ ስናውጅ ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ።

ፕሮግራማችን ፡ የሆነው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወደቦች ፡ የማሻሻልና ፡ የማስፋ ፋት ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ መውጣት ፡ የተገባ ፡ ነው ። ወደቦቻችን ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያቃልሉበት ፡ ዘመናዊ ፡ ዝግጅት ፡ ስለሚኖራቸው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ጋር ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ ላላቸው ፡ አገሮች ፡ የሚ ሰጠው ፡ የንግድ ፡ ጥቅም ፡ ከግምት ፡ በላይ ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ውስጥ ፡ እየተስፋፋ ፡ የሚሄደውንና ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚላኩ ትን ፡ የኢንዱስትሪና ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ሀብቶች ፡ ለመላክ ፡ የሚያቃልል ፡ ይሆናል ። የኛ ፡ መርከቦችና ፡ ሌሎችም ፡ ለጥቅማቸው ፡ በወደቦቻችን ፡ የሚመዘገቡትን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መርከቦች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ስር ፡ በዓለም ፡ ውቅያኖሶች ፡ ሁሉ ፡ የሚንሳፈፉ ፡ ሲሆኑ ፡ ለኛ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ነው ። እንደ ፡ ጥንቱ ፡ የታሪክ ፡ ዘመናችን ፡ ዳግመኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከቦች ፡ የመንግሥታችንን ፡ ሀብት ፡ ጭነው ፡ በአራቱ ፡ የዓለም ፡ ማዕዘን ፡ ሲጓዙ ፡ የምናይ ፡ ይሆናል ።

ሁሉን ፡ በሚችል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ የንግድ ፡ መርከቦቻችን ፡ እያደጉና ፡ እየተስፋፉ ፡ ይሄዳሉ ። ሰንደቅ ፡ ዓላማችንም ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት፡ ወደቦች ፡ ሁሉ ፡ የታወቀና ፡ የተከበረ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ እር ዳታ ፡ በኛ ፡ ዘመን ፡ ያለው ፡ የምንወደው ፡ ሕዝባችንና ፡ ለወደፊትም ፡ የሚመጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትውልድ ፡ በንግድና ፡ በሀብት ፡ እየተስፋፋ ፡ እያደገ ፡ እንደሚሄድ ፡ እናምናለን ።

የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጉባኤያችን ፡ የደከመበትን ፡ ሥራ ፡ ፓርላሜንታችን ፡ በጥ ንቃቄ ፡ አጥንቶ ፡ የሥራውን ፡ ፍሬ ፡ በማየታችን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ በየጊዜው ፡ እየተሻሻለ ፡ የሚሄደውን ፡ የአገራችንን ፡ ዕድገትና ፡ የሕዝባችንን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ መሻሻል ፡ በቀላሉ ፡ የሚያፋጥን ፡ ይሆናል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሚያዝያ ፡ ሀያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ቍጥር ፡ ፩፻፳፬ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ያ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፤

# ዐዋጅ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን ፡ የባሕር ፡ ወደቦች ፡ ለማስፋፋትና ፡ የንግድ ፡ መርከቦቻችንን ፡ ብዛት ፡ ለማሳደግ ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ታየን ፤

በእኛ ፡ መሪነት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አድርገን ፡ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ ስለ ፡ ተቀበሉት ፤

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፲ተኛውና ፡ በ፻፳፫ተኛው ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፤ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ የመከሩበትን ፡ አይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አውጀናል ።

፩ ፡ ይህ ፡ ዐዋጅ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ ዐዋጅ ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

፪ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ ቍጥር ፡ ፩/፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የታተመው ፡ ከሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

፫ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተመዘገቡትን ፡ መርከቦች ፡ ዜግነት ፡ በማነኛውም ፡ ምክንያት ፡ የሚነካ ፡ አይደለም ።

፬ ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቍጥር፡ ፩፻፵፯ ፡ በወጣው ፡ የባሕር ፡ዐዋጅ፡ ከ፪፡ እስከ፡ ፳፡ አንቀጾች ፡ በ፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ውስጥ፡ ከፊደል ፡ ሰ—ረ—ሠ—ንኡስ፡ቍጥሮች፡ ከ፳፰፡ እስከ፡ ፵፩ ፡ እና ፡ ከ፵፯ ፡ እስከ ፡ ፶፯ ፡አንቀጾች ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ሁሉና፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም. በቍጥር ፡ ፪፻፬ ፡ የወጣው ፡ ማሻሻያ ፡ ዐዋጅ ፡ ጭምር፡ በሙሉ ፡ ተሠርዟል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም

ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አክሊሉ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡

ምክትል ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርና ፡ የጽሕፈት ፡ሚኒስትር ።

BACK

# የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

## የባሕር ፡ ሕግ ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ መርከብ ፤

### ምዕራፍ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፩ ። ስለ ፡ መርከብ ፡ ትርጓሜ ።**

የስሙ ፡ ልዩ ፡ አጠራር ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆንና ፡ የክብደቱም ፡ ልክ ፡ ቢለዋወጥ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለሚውልበት ፡ ጕዳይ ፤ ለዘወትሩ ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ጕዞ ፡ የሚያደርግ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ የተመደበ ፡ ከሆነ ፤ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ የንግድ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኛ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ የባሕር ፡ ሕንጻ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መርከብ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪ ። ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎች ።**

መርከቡም ፡ በሚሰጠው ፡ ሥራ ፡ ለመጠቀም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ የሆኑት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያዎች ፡ እንደ ፡ መርከቡ ፡ አካሎች ፡ ሆነው፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫ ። መርከብ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ተገልጸው ፡ የተመለከቱት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ መርከብ ፡ ሲባል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ውስጥ፡ የሚተዳደር ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ነው ።

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ መርከብ ፡ ዜግነት ።

**ቍ ፡ ፬ ። ለኢትዮጵያዊ ፡ መርከቦች ፡ ባለቤትነት ፡ በቂ ፡ ስለ ፡ መሆን ።**

ከዚህ ፡ በታች ፡ በተገለጹት ፡ ሰዎች ፡ ባለቤትነት ፡ ውስጥ ፡ ያልሆነ ፡ መርከብ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መርከብ ፡ ሊቈጠር ፡ አይችልም ።

(ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፤

(ለ) በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋሙና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤታቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፤

(ሐ) በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤታቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሆኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ።

ቍ ፡ ፫ ። እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ መርከቦች ።

እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩ ፡ መርከቦች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩት ፡ ናቸው ።

(ሀ) በባሕር ፡ ላይ ፡ ተትተው ፡ የተገኙና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ በሚያ ውለበልቡ ፡ መርከቦች ፡ ተለቅመው ፡ የተወሰዱ ፡ መርከቦች ፤

(ለ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በውርስ ፡ የተወሰዱ ፡ መርከቦች ።

ቍ ፡ ፬ ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መርከቦች ።

(፩) የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እያውለበለቡ ፡ መንሳፈፍ ፡ የሚችሉ ፡ የኢት ዮጵያ ፡ መርከቦች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

፪) ዓሣ ፡ በጠረፍ ፡ ለማጥመድና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወደቦች ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ባሕር፡ ላይ ፡ ከወደብ ፡ ወደብ ፡ እየተመላለሱ ፡ ለመነገድና ፡ በነዚህም ፡ ወደቦች ፡ ውስጥ፣ ለሚደረገው ፡ የመርከቦች ፡ መሳብ ፡ (መጐተት) ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽሙ ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ መርከቦች ፡ የሆኑት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መርከብ ፡ ባለሀብትነት ።

ቍ ፡ ፯ ። የመርከብ ፡ ባለሀብትነት ።

(፩) የባለቤትነትን ፡ መብት ፡ ወይም ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ ሌሎችን ፡ ግዙፍ ፡ መብ ቶች ፡ የሚያቋቁሙ ፤ የሚያስተላልፉ ፤ የሚያስቀሩ ፡ ውሎች ፡ በታወቀ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ ፎርም ፡ ካልተደረጉ ፡ በቀር ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ።

(፪) እነዚህም ፡ ውሎች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በተደረጉ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቆንሲል ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ ቆንሲል ፡ በሌለበት ፡ አገር ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፰ ። ስለ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ።

በቍጥር ፡ ፯ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሎች ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ እንዲታወቁ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወ ሚያ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ መርከብ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ።

ቍ ፡ ፱ ። የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ መብት ።

ባንድ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ የአብዛኛዎቹን ፡ ሐሳብ ፡ መከተል ፡ ይገባል ።

BACK



ቍ ፡ ፲ ። የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ግዴታ ።

(፩) ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ እያንዳንዱ ፡ ለመርከቡ ፡ ግዴታ ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆነው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ የጥቅም ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በመርከቡ ፡ ሥራ ፡ ማካሄድ ፡ ጕዳይ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ የማይፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ካስታወቀ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ድርሻ ፡ በመልቀቅ ፤ ይህ ፡ የመርከብ ፡ ሥራ ፡ ማካሄድ ፡ ጕዳይ ፡ ከሚያደርስበት ፡ ግዴታ ፡ ነጻ ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ መብቱን ፡ የለቀቀውን ፡ ሰው ፡ ድርሻ ፡ ገንዘብ ፡ የቀሩት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ይከፋፈሉታል ።

ቍ ፡ ፲፩ ። መርከብ ፡ አከራይ ፡ የሆነው ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ሥልጣን ።

(፩) የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የሾሙት ፡ የመርከብ ፡ አከራይ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ የሥራ ፡ መሪነቱን ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ለማከናወን ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የጽሑፍ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሰጡ ፡ በቀር ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሊቀነስበት ፡ አይችልም ።

(፪) የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ፡ መቀነስ ፡ በመርከብ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ ካልተገለጠ ፡ በቀር ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፪ ። የጋራ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ድርሻ ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

እያንዳንዱ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የጥቅም ፡ ድርሻውን ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላል ። የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ አንዱ ፡ የራሱን ፡ ድርሻ ፡ መያዣ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፫ ። የሌሎቹ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ።

(፩) ከጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ አንዱ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የራሱን ፡ የጥቅም ፡ ድርሻ ፡ የሚሸጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገገርው ፡ መግዛቱን ፡ ለቀሩት ፡ ባለሀብቶች ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ካላስታወቀ ፡ ሽያጩ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) የቀሩት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ በደረሳቸው ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የሽያጩን ፡ ዋጋና ፡ ወጪዎች ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ በመክፈል ፡ በተሸጠው ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ የመግዛት ፡ ቀደምትነት ፡ መብታቸውን ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

(፫) ሁሉም ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ በቀዳሚነት፡መብታቸው፡ለመግዛት፡የፈለጉ ፡ እንደ ሆን ፡ የሻጩን፡ድርሻ ፡ የሚከፋፈሉት ፡ በመርከቡ፡ላይ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ መጠን፡

BACK



ነው ፤ ወይም ፡ እንገዛለን ፡ ያሉት ፡ ገሚሶቹ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ የሻጩን ፡ ድርሻ ፡ የሚካፈሉት ፡ እነዚሁ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፬ ። የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሆነውን ፡ መርከብ ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

(፩) በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሆነ ፡ መርከብ ፡ ሊሸጥ ፡ የሚቻለው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የሆኑት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሲስማሙ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ሽያጭ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ የሚደረግ ፡ ሽያጭ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡ ይፈጸማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## መርከቡን ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግና ፡ በሱም ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ልዩ ፡ መብት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ልዩ ፡ መብቶች ።

ቍ ፡ ፲፭ ። ልዩ ፡ መብቶች ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ዝርዝር ፡ ተራ ።

ቀዳሚነት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስጡ ፡ መብቶች ፡ ተራቸው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ተዘረዘረው ፡ የተመለከቱት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፩) ሕጋዊ ፡ ወጪዎችን ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ የጋራ ፡ ጥቅምና ፡ መርከቡን ፡ ለመጠበቅ ፡ ለመሸጥና ፡ ዋጋውንም ፡ ለማከፋፈል ፡ የተደረጉ ፡ ሌሎች ፡ ወጪዎች ፡ የክብደት ፤ የፋናና ፡ የወደብ ፡ ቀረጦች ፤ እንዲሁም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፤ የመርከቡ ፡ መንጃ ፡ ወጪና ፡ እንዲሁም ፡ መርከቡ ፡ እመጨረሻ ፡ ማረፊያ ፡ ጣቢያው ፡ ከገባበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ለመጠበቅና ፡ በደኅና ፡ ለማቈየት ፡ የተደረጉ ፡ ወጪዎች ።

(፪) ከካፒቴኑ ፤ ከመርከበኞቹና ፡ ለመርከቡ ፡ አገልግሎት ፡ ከተቀጠሩት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ የተነሣ ፡ ያሉት ፡ ዕዳዎች ።

(፫) መርከቡን ፡ ለመርዳትና ፡ ለማዳን ፡ ለተደረጉት ፡ አገልግሎቶች ፡ የሥራ ፡ ዋጋና ፡ በመርከቡም ፡ ለደረሱት ፡ የጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆንባቸው ፡ ዕዳዎች ፤

(፬) በመጋጨትና ፡ በሌላም ፡ በባሕር ፡ ጕዞ ፡ ስለሚደርሱት ፡ መሰናክሎች ፤ እንዲሁም ፡ በወደብ ፡ የጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ (በዶክ) ፡ በመቆሚያ ፡ ስፍራዎች ፡ በባሕር ፡ ጐዳናዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ፡ የሚከፈል ፡ ኪሣራና ፡ ካሣ ፤ በመርከቡ ፡ ምክንያት ፤ በባሕር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አዋኪ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለማንሣት ፡ የሚደረጉ ፡ ወጪዎች ፡ በመንገደኞችና ፡ በመርከበኞቹ ፡ ላይ ፡ ለሚ

BACK



ደርሰው ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፤ በጭነቶቹና ፡ በመንገደኞቹ ፡ ዕቃ ፡ ላይም ፡ ለሚደ ርሰው ፡ መጥፋትና ፡ መበላሸት ፡ የሚከፈሉ ፡ ኪሣራዎች ፤

(፭) ካፒቴኑ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ላለመሆኑ ፡ ልዩነት ፡ ሳይ ደረግና ፡ የሚጠየቀውም ፡ ገንዘብ ፡ የራሱ ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ አቅራቢዎቹ ፡ ወይም፥ የአዳሾቹ ፡ ወይም ፡ የአበዳሪዎቹ፡ ወይም ፡ የሌሎቹ ፡ ተዋዋዮች ፡ መሆኑ ፡ ሳይ ታይ ፡ መርከቡን ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ጉዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ በርግጥ ፡ አስፈ ላጊ ፡ በሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ ከመርከቡ ፡ ማረፊያ ፡ ጣቢያ ፡ ወደብ ፡ ውጭ ፡ በሕግ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣኑ ፡ መሠረት ፡ ካፒቴኑ ፡ ካደረጋቸው ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ከፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ የተነሣ ፡ የሚከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፤

(፮) ለዕቃ ፡ ጫኚዎች ፡ የሚከፈሉት ፡ ኪሣራዎች ፤

(፯) ኢንሹራንስ ፡ የተደረገው ፡ በየጉዞው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመጨረሻው ፡ ኢንሹራ ንስ ፡ ለተደረገበት ፡ ጉዞው ፡ በመርከቡ ፡ አካል ፡ መሣሪያዎችና ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የሚ ከፈለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንሱ ፡ የተደረገው ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ፡ ሲሆን ፤ ለመጨረሻው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለተደረገለት ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈለው ፡ የኢንሹራ ንስ ፡ ዋጋ ፡ ቢሆንም ፡ በሁለቱም ፡ ጊዜ ፡ ቢበዛ ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ከሚከፈለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ዋጋ ፡ የማይበልጥ ፡ ወጪ ፤

(፰) በጭነቱ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ መግ ለጫ ፡ በመስጠት ፡ የተነሣ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ።

<u>ቍ ፡ ፲፯ ። ልዩ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በየመርከቡ ፡ ጉዞ ፡ ተራ ፡ ስለ መስጠት ።</u>

ገንዘባቸውን ፡ በቀዳሚነት ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ባለገንዘቦች ፡ ለገ ንዘባቸው ፡ አከፋፈል ፡ የሚሰጣቸው ፡ ተራ ፡ በየመርከቡ ፡ ጉዞ ፡ መሆን ፡ አለበት ። በመጨረሻው ፡ ጉዞ ፡ ቀዳሚነት ፡ ያላቸው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ የማ ንኛውም ፡ ክፍል ፡ ቢሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ጉዞ ፡ በፊት ፡ ካሉት ፡ መብቶች ፡ ቀዳሚነት ፡ ይሰጣቸዋል ፤ ቢሆንም ፡ መርከበኞቹ ፡ ከተቀጠሩበት ፡ ካንዱ ፡ ውል ፡ ብቻ ፡ የሚገኙ፡ መብቶች ፡ ለፊተኛው ፡ ጉዞ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ ከመጨረሻው ፡ ጉዞ ፡ እንደ ፡ ተገኙ ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

<u>ቍ ፡ ፲፰ ። ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ጉዞ ፡ የሚመለከቱ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ተራ ፡ አሰጣጥ ።</u>

(፩) አንዱን ፡ ጉዞ ፡ ብቻ ፡ የሚመለከቱ ፡ ዕዳዎች ፡ የአከፋፈላቸው ፡ ቅደም ፡ ተከ ተል ፡ ተራ ፡ የሚመደበው ፡ በቍጥር ፲፭ ፡ በተመለከተው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) የገንዘቡ ፡ ማነስ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ ሲሆን ፤ አን ዱን ፡ ጉዞ ፡ ብቻ ፡ የሚመለከቱ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ባንድ ፡ ተራ፡

BACK



እንዳሉ ፤ ገንዘቡን ፡ እንደ ፡ ድርሻቸው ፡ መጠን ፡ ይከፋፈላሉ ።

(፫) ለመርከቡ ፡ ርዳታ ፡ ላደረጉት ፡ ወገኖች ፡ የሚከፈለው ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፤ ለመርከቡ፡ለቀረበው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ለተጠገነበት ፡ ወጪ ፡ ስለ ፡ ሆነው ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ የቅደም ፡ ተከተሉ ፡ ደረጃ ፡ የሚመደበው ፡ ይህ ፡ ዕዳ ፡ የተገኘበትን ፡ ቀን ፡ ተከታታይነት ፡ በማዛወር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፰ ። ካንዱ ፡ የባሕር ፡ አደጋ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ቀን ፡ አቈጣጠር ።**

ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ከደረሰው ፡ የባሕር ፡ አደጋ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተገኙ ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ፲፱ ። ስለ ፡ ማስረጃ ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ላይ ፡ የተገለጹት ፡ የቀዳሚነት ፡ መብቶች ፡ ገንዘቡን ፡ የመጠየቅ፡መብት ፡ እንደ፡ተረጋገጠ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዳሉ ፡ ሆነው፡ ይታሰባሉ ። ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፤ የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ ካልተነገረ ፡ በቀር ፤ ስለ፡ ገንዘቡ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ መኖር ፡ ማናቸውም ፡ አሠራር ፡ወይም ፡ ልዩ ፡ የማስረጃ፡ ሁኔታ ፡ አያስፈልገውም ።

**ቍ ፡ ፳ ። መያዣ ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራ ።**

በመርከቡ ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ያላቸው ፡ ለመሆኑ ፡ የተመዘገቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለመካፈል ፡ የሚችሉት ፤ በቍጥር ፡ ፲፭ ፡ ከንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፰ ፡ ከተመለከቱት ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ካላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በኋላ ፡ መዝገብ ፡ እንደ ፡ መግባታቸው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፳፩ ። በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ።**

(፩) የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ የሚሰጠውም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ መብቱ ፡ ከተገኘበት ፡ ጊዜ ፡ የተነሣ ፤ ለጕዞ ፡ በተጫነው ፡ ዕቃ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ለመርከቡ ፡ ተጨማሪ ፡ በሆኑት ፡ መጣሪያዎችና ፡ ጕዞውም ፡ ከተጀመረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በተጫነው ፡ ዕቃ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) ባ፲፭ኛው ፡ ቍጥር ፡ በ፪ኛው ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ የቀዳሚነት፡ መብት ፡ ባንድ ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረጉት ፡ ጕዞዎች ፡ በተጫኑት ፡ ዕቃዎች ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፳፪ ። የመርከብ ፡ ተጨማሪ ፡ መጣሪያና ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ ትርጓሜ ።**

ለቀደምትነት ፡ መብት ፡ አሠራር ፡ እንደ ፡ መርከቡ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገሮችና ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ ሆነው ፡ የሚቈጠሩት ።

(፩) መርከቡ ፡ በደረሰበት ፡ ግዙፍ ፡ አደጋ ፡ ምክንያትና ፡ ሳይታደስ ፡ በቀረው ፡ መሰናከል ፤ ወይም ፡ መርከቡ ፡ ኪራይ ፡ በማጣቱ ፡ ምክንያት ፡ ለባለሀብቶች ፡ የሚከፈለው ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፤

(፪) የጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሆኑት ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የደረሱት ፡ ግዙፍ ፡ ጉዳቶችና ፡ ሳይታደሱ ፡ የቀሩት ፡ ወይም ፡ መርከብ ፡ ኪራይ ፡ በማጣቱ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ ስለ ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ለባለሀብቶቹ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባው ፡ ኪሣራ ፤

(፫) ለካፒቴኑና ፡ ለመርከበኞቹ ፡ ለሌሎቹም ፡ የመርከብ ፡ ሠራተኞች ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፤ እስከ ፡ ጉዞው ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ መርከቡን ፡ ለመርዳት ፡ ወይም ፡ ከአደጋ ፡ ለማዳን ፡ ላደረጉት ፡ ርዳታ ፡ ሊከፈላቸው ፡ የሚገባ ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፳፫ ። እንደ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወይም ፡ ከመርከቡ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎችና ፡ ከጭነቱ ፡ ኪራይ ፡ ውጭ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ያህል ፡ የሚቈጠሩ ፡ ገንዘቦች ።

(፩) የመንገደኞች ፡ ዋጋና ፡ ተገቢም ፡ ሲሆን ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ስላለበት ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ጉዳይ ፡ የተመደበው ፡ ቍርጥ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ለባለሀብቱ ፡ የሚከፈሉት ፡ ኪሣራዎች ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ የሚሰጣቸው ፡ ርዳታ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ስጦታ ፡ በቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አጠያየቅ ፡ እረገድ ፡ እንደ ፡ መርከቡ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎችና ፡ እንደ ፡ ጭነቱ ፡ ገቢ ፡ አይቈጠሩም ።

ቊ ፡ ፳፬ ። በመርከቡ ፡ የጭነት ፡ ዋጋዎችና ፡ በተጨማሪ ፡ መሣሪያዎች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የተቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ እስከ ፡ ተከፈለ ፡ ወይም ፡ የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ሒሳብ ፡ በካፒቴኑ ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ እንደራሴ ፡ እጅ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ እንዳለ ፡ ይቈያል ። እንዲሁም ፡ በመርከቡ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎች ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የቀዳሚነት ፡ መብቶች ፡ እንዳሉ ፡ ይቈያሉ ።

ቊ ፡ ፳፭ ። መርከቡን ፡ የሚከተል ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ።

የቀዳሚነት ፡ መብቶች ፡ መርከቡ ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ቢገባ ፡ መርከቡን ፡ የሚከተሉ ፡ ናቸው ።

ቊ ፡ ፳፮ ። ስለ ፡ ይርጋ ።

(፩) ከዕቃ ፡ ማቅረብ ፡ የተነሣ ፡ ለሚገኙት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብቶች ፡ በ፯ ፡ ወር ፡ ይርጋ ፡ ከሚታገደው ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሆን ፡ ከተሰጠው ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፲፰ ፡ የተዘረዘሩት ፡ የቀደምትነት ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ በ፩ ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳሉ ።

(፪) ለመርከቡ ፡ ርዳታ ፡ ለመስጠትና ፡ መርከቡን ፡ ከአደጋ ፡ ለማዳን ፡ ለተደረገው ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ልዩ፡ መብቶች ፡ የይርጋው ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ይህ፡ የአገልግሎት፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ለመርከብ ፡ ግጭት ፡ ወይም ፡ ለሌሎች ፡ አደጋዎችና ፡ ስለ ፡ አካል ፡ ጉዳቶች ፡ የሚከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፡ የሚያረጋግጠው ፡ የልዩ ፡ መብት ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ጉዳቱ ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ለጭነት ፡ ወይም ፡ ለተሳፋሪዎቹ ፡ የመንገድ ፡ ዕቃ ፡ መጥፋት ፡ መበላሸት ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለሚያረጋግጠው ፡ የልዩ ፡ መብት ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ጭነቱ ፡ ወይም ፡ የመንገደኞቹ ፡ ዕቃ ፡ ለባለሀብቶቹ፡ ከተሰጡበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ሊሰጡ ፡ ይገባ፡ከነበረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው።

ለመርከቡ ፡ ማደሻና ፡ ለሌሎችም ፡ ለቀረቡት ፡ ሥንቆች ፡ ወይም ፡ በቍጥር፡ ፲፰ ፡ ፪ኛ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ለተመለከቱት ፡ ጕዳዮች ፡ ለሚከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፡ የልዩ፡ መብት ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው፡ የገንዘቡ ፡ መብት ፡ ከተገኘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) ለሌሎቹ ፡ ጕዳዮች ፡ ሁሉ ፡ የይርጋው ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ገንዘቡ ፡ ተከፋይ ፡ ከሆነበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፬) መርከቡ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ከገንዘባቸው ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ቢኖራቸውም ፡ ባ፲፰ኛው ፡ ቍጥር፡ በ፪ኛው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የተመለከተው ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ ለተቀጠሩት ፡ ሠራተኞች ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ተከፋይ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ በጕዞው ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው ።

(፭) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠሪያ ፡ ጊዜ ፡ ዕዳ ፡ ያለበት ፡ መርከብ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራው ፡ ወይም ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ፡የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከቡ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ባሕሮች ፡ ውስጥ ፡ እስኪያዝ ፡ ድረስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ አይጀመርም ። ስለሆነም ፡ የገንዘቡ ፡ መብት ፡ ከተገኘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የይርጋው ፡ ዘመን ፡ ከ፫ ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፳፯ ። የቀደምትነት ፡ መብት ፡ የሚቀርበት ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ።

(፩) ግዴታዎች ፡ ከሚቀሩበት ፡ ከሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ፡ በቀር ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ የሚሆነው ፤

በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተደነገገው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የታዘዘ ፡ የሽያጭ ፡ ሥርዐት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከተው ፡ ሥርዐት ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ መርከቡን ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የሸጠ ፡ (ያስተላለፈ) ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሀ) የንብረቱ ፡ ማዘዋወር ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ የንብረት ፡ ማዛወር ፡ ጉዳይ ፡ በኦፊሴል ፡ የንግድ ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ በመግባትና ፡ መርከቡ ፡ በተመዘገበበት ፡ የባሕር ፡ ወደብ ፡ ቦታ ፡ በየዕለቱ ፡ በሚታተም ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ በማስታወቂያ ፡ የወጣና ፡ እንዲሁም ፡ የመርከቡ ፡ መመዝገቢያ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በሆነው ፡ ቢሮ ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ ማስታወቂያው ፡ በመለጠፉ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የመጻፍና ፡ የሚለጠፈው ፡ ማስታወቂያ ፡ በግዴታ ፡ የገዢውን ፡ ደንበኛ ፡ የመኖሪያ ፡ ሰፍራ ፡ ስም ፡ የሚገልጽ ፡ ሆኖ ፤

(ሐ) ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ በወጣበት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ከገዢው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ለገዢው ፡ ምንም ፡ መቃወሚያ ፡ ያላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

(፪) ይህ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የመርከቡ ፡ ዋጋ ፡ ያልተከፈለ ፡ እስከ፡ሆንተበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፤ ገንዘቡ ፡ ከመከፈሉ ፡ በፊት ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂው ፡ መርከቡን ፡ ለገዛው ፡ ሰው ፡ መቃወሚያ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብቱ ፡ እንዳለ ፡ ይቈያል ፡፡

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በ፪ኛው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ የመቃወሚያ፡ ጥያቄ ፡ ለባለዕዳው ፡ ሊገለጽለት ፡ ይገባዋል ፡፡

<u>ቍ ፡ ፳፰ ፡፡ የቀዳሚነትን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ፡፡</u>

ገንዘብ ፡ ለመጠየቅ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ አበዳሪዎች ፡ መርከቡ ፡ በመዝገብ ፡ በሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብታቸውንም ፡ አብረው ፡ ለማስመዝገብ ፡ ይችላሉ ፡፡ ይህም ፡ የማስመዝገብ ፡ ጉዳይ ፡ በቀዳሚነት ፡ ገንዘብ ፡ ለመጠየቅ ፡ ስላላቸው ፡ መብት፡ ያላቸውን ፡ ተራ ፡ የማይነካ ፡ ነው ፡፡

<u>ቍ ፡ ፳፱ ፡፡ መርከቡን ፡ የሚያካሂደው ፡ ባለሀብቱ ፡ ባልሆነበት ፡ ጊዜ ፡፡</u>

መርከቡን ፡ የሚያካሂደው ፡ ባለሀብት ፡ ያልሆነ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ ዋናው ፡ ተከራይ ፡ (ቻርተረር) ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ የባለይዞታነቱን ፡ መብት ፡ ያጣው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ካልሆነና ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂውም በክፉ ፡ ልቡና ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ፡፡

## ክፍል ፡ ፪ ፡፡

## <u>መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡፡</u>

<u>ቍ ፡ ፴ ፡፡ መያዣ ፡ የማድረጉ ፡ ወሰን ፡፡</u>

ጠቅላላ ፡ ክብደታቸው ፡ ሁለት ፡ ቶንና ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የሆኑ ፡ መርከቦች ፡

መያዣ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፴፩ ። መያዣ ፡ ሰጪ ።

(፩) በአንድ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የመያዣ ፡ መስጠት ፡ ጕዳይ ፡ ባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ ከባለሀብቱ ፡ ልዩ ፡ ወኪልነት ፡ ለመኖሩ ፡ ማስረጃ ፡ በሚያቀርበው ፡ ወኪል ፡ ካልሆነ ፡ ሊፈቀድ ፡ አይቻልም ።

(፪) የመርከቡ ፡ ባለሀብቶች ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከነዚሁ ፡ በአብዛ ኞቹ ፡ ፈቃድ ፡ ለመርከቡ ፡ መሣሪያዎች ፡ ማሟያ ፡ ወይም ፡ ለጕዞው ፡ ማደራጃ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ በአከራዩ ፡ ሥልጣን ፡ መር ከቡ ፡ መያዣ ፡ ሊሆን ፡ ይቻላል ። ቢሆንም ፡ ፈቃድ ፡ ያሰጡት ፡ ባለሀብቶች ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ከሆኑት ፡ ጥቅሞች ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈል ጋል ፤ ሦስት ፡ አራተኛው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሊገኝ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጋራ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ በሚሻለው ፡ አኳኋን ፡ ነገሩን ፡ እንዲወስን ላቸው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ፤ ከጋራ ፡ ባለሀ ብቶቹ ፡ አንዱ፡በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ያልተከፋፈለውን ፡ የራሱን ፡ ድርሻ ፡ መያዣ ፡ ለማድረግ ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አብዛኞቹ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብ ቶች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ካልፈቀዱለት ፡ በቀር ፡ ለማስያዝ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፴፪ ። መያዣ ፡ ስለሚሆኑት ፡ ንብረቶች ።

(፩) ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በመርከቡ ፡ ወይም ፡ ከመርከቡ ፡ ሀብት ነት ፡ ባንዱ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ መያዣ ፡ በመላው ፡ በመርከቡ ፡ ገላ ፡ በብረታብረቶቹ ፡ በመለወጫ ፡ ዕቃዎቹ ፡ በመኪናዎቹና ፡ በሌሎቹ ፡ ተጨማሪ ፡ መሣሪያዎች ፡ እንዲሁም ፡ በስብርባሪ ፡ ዕቃዎቹም ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ በጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ላይም ፡ ሆነ ፡ መንግሥት ፡ በሚሰጠው ፡ ርዳታና ፡ ጕርሻ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ መያዣው ፡ አይጸናም ።

(፫) የተከፈለው ፡ የአደጋ ፡ ማሻሻያ ፡ ኪሣራ ፡ መርከቡን ፡ ለማደስ ፡ ወይም ፡ በደ ንብ ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆነው ፡ ጕዳይ ፡ ካልዋለ ፡ በቀር ፡ መርከቡ ፡ ለደ ረሰበት ፡ አደጋ ፡ በተከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ ላይ ፡ መያዣው ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

(፬) ኢንሹራንሱ ፡ በሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ አይጸናም ፤ ቢሆንም ፡ የመያዣው ፡ መቋቋሚያ ፡ ውል ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የመብት ፡ ማስተላለፍ ፡ የኢሹራንሱን ፡ ገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ለተሰጣቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚተላለፍ ፡ ለማድረግ፡ ይችላል ፤ ይኸውም ፡ የመብት ፡ መተላለፍ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ያደረጉትን ፡ ሰዎች ፡ መከራከሪያ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ የመብቱን ፡ መተላለፍ ፡ በጽሑፍ ፡ ተቀብለ

ውት ፡ ወይም ፡ ማስታወቂያ ፡ ተልከላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፴፫ ። ገና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መርከብ ፡ መያዝ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) በባሕር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ መያዣ ፡ የማድረግ ፡ ጉዳይ ፡ ገና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ መርከብ ፡ ላይም ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መያዣው ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ መርከቡ ፡ በሚሠራበት ፡ የባሕር ፡ ወደብ ፡ አዛዥ ፡ ለሆነው ፡ ባለሥልጣን ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) ይህም ፡ መግለጫ ፡ የመርከቡን ፡ ስይፍ ፡ ጠርዝ ፡ ( ኪል ) ፡ ርዝመት ፡ በግምትና ፡ ሌሎቹንም ፡ መጠኖቹን ፡ እንዲሁም ፡ ሊኖረው ፡ የታቀደውን ፡ ጠቅላላ ፡ ክብደት ፡ ማመልከት ፡ አለበት ፤ መርከቡ ፡ እንዲሠራ ፡ የታቀደበትን ፡ ልዩ ፡ ቦታ ፡ ጭምር ፡ መግለጫው ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፴፬ ። የአፈጻጸሙ ፡ ፎርም ።**

(፩) የባሕር ፡ ንብረትን ፡ የማስያዝ ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ በግል ፡ ጽሕፈትም ፡ ውል ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) መያዣውን ፡ የሚያቋቁመው ፡ ሰነድም ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚችል ፡ ይሆናል ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በመጻፍ ፡ የሚደረግ ፡ ማስተላለፍ ፡ የመያዣውንም ፡ መብት ፡ ያስተላልፋል ።

**ቍ ፡ ፴፭ ። የወለድን ፡ ልክ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

አንድ ፡ መርከብ ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ ገንዘብ ፡ የመበደር ፡ ስምምነት ፡ በተደረገ፡ ጊዜ ፤ የብድሩ ፡ ወለድ ፡ ከመቶው ፡ 12% በላይ ፡ ማለፍ ፡ አይገባውም ።

**ቍ ፡ ፴፮ ። የአመዘጋገቡ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) የአመዘጋገቡ ፡ ሥርዐት ፡ የሚፈጸመው ፡ ለመርከቡ ፡ የመለያ ፡ ቍጥር ፡ በተሰጠበት ፡ ወደብ ፡ በሚገኘው ፡ የመርከብ ፡ መመዝገቢያ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ነው ። መያዣ ፡ የተደረገው ፡ ገና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመያዣው ፡ ውል ፡ የሚመዘገበው ፡ መርከቡ ፡ በሚሠራበት ፡ ወደብ ፡ ባለው ፡ የወደብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መስጫ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) የአመዘጋገቡ ፡ ሥርዐት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ትክክለኛነቱ ፡ የተመሰከረለት ፡ የመያዣው ፡ ውል ፡ ግልባጭ ፡ ለመርከብ ፡ መመዝገቢያ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

ከውሉም ፡ ጋራ ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢው ፡ የፈረመባቸውና ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩት ፡ መግለጫዎች ፡ የተጻፈባቸው ፡ ሁለት ፡ ዝርዝሮች ፡ መያያዝ ፡ አለባቸው ።

(ሀ) የአበዳሪውና ፡ የባለዕዳው ፡ ስምና ፡ የአባት ፡ ስም ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታና ፡ ሥራቸው ።

(ለ) የውሉ ፡ ዐይነት ፡ ቀኑና ፡ ዓመት ፡ ምሕረቱ ፤

(ሐ) በውሉ ፡ ላይ ፡ ስምምነት ፡ የተደረገበት ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፤

(መ) የወለዱንና ፡ የዕዳውን ፡ አከፋፈል ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁኔታዎች ፤

(ሠ) መያዣ ፡ የሆነው ፡ መርከብ ፡ ስምና ፡ ዝርዝር ፡ የተመዘገበበት ፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ ቀንና ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መርከቡ ፡ አሠራር ፡ የተሰጠው ፡ መግለጫ ፤

(ረ) መርከቡ ፡ በተመዘገበበት ፡ ግዛት ፡ ውስጥና ፡ ውሉ ፡ በተመዘገበበት ፡ ስፍራ ፡ ባለዕዳው ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበልበት ፡ አድራሻ ፤

(፫) የመርከቡ ፡ መመዝገቢያ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በሁለቱ ፡ ዝርዝሮች ፡ ላይ ፡ የተጻፉትን ፡ መግለጫዎች ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።
ከሁለቱ ፡ ዝርዝሮች ፡ አንደኛውን፡መርከቡ ፡ ስለ ፡ መመዝገቡ፡የተመሰከረበትን ፡ ማረጋገጫና ፡ የመመዝገቡን፡ሥርዐት ፡ የፈጸመ ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠበትን ፡ አንደኛውን ፡ ዝርዝር ፡ ለጠያቂው፡መልሶ ፡ መስጠት፡አለበት ፤ እንዲሁም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በመርከቡ ፡ መመዝገቢያ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መመዝገቡ ፡ ምልክት ፡ ይደረጋል ።

<u>ቊ ፡ ፴፪</u> ። <u>የመመዝገቡ ፡ ሥርዐት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።</u>

(፩) የመያዣው ፡ ውል ፡ መመዝገብ ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ መያዣውን ፡ አጽንቶ ፡ ያቈየዋል ፤ ይህ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ስምምነቱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ካልታደሰ ፡ በቀር ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ።

(፪) መርከቡ ፡ በተሸጠበት ፡ ዓመት ፡ ከሚገኙት ፡ ወለዶች ፡ በላይ ፤ የመያዣው ፡ ውል ፡ መመዝገብ ፤ እንደዋናው ፡ ገንዘብ ፡ በቀዳሚነት ፡ የሚከፈል ፡ መብት ፡ የሚኖረው ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ወለድን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ዋስትና ፡ ነው ።

<u>ቊ ፡ ፴፫</u> ። <u>መያዣ ፡ የሆነውን ፡ መርከብ ፡ ስለ ፡ ማስያዝና ፡ ስለ ፡ ማሸጥ ።</u>

(፩) በአንድ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ በአጋማሹ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብታቸውን ፡ ያስመዘገቡ ፡ ባለሀብቶች ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራቸው ፡ ገንዘባቸው ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ እንዲችሉ ፡ ይህ ፡ በዕዳ ፡ የያዙት ፡ መርከብ ፡ በማንም ፡ እጅ ፡ ቢተላለፍ ፡ እንኳ ፡ የመከታተል ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

(፪) መያዣ ፡ የተደረገው ፡ የመርከቡ ፡ አጋማሽ ፡ ሀብት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ለማስያዝና ፡ ለማሸጥ ፡ የሚችለው ፡ የሚደርሰውን ፡ አጋማሽ ፡ ሀብት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከመርከቡ ፡ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ከግማሽ ፡ የበለጠው ፡ መያዣ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶቹን ፡ በሽያጩ ፡ ጊዜ ፡ አስጠርቶ ፡ መርከቡን ፡ ካስያዘ ፡ በኋላ ፡ በሙላው ፡ ሊያሸጠው ፡ ይችላል ።

(፫) መርከቡ ፡ ሐራጅ ፡ ሲባል ፡ ለአንድ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ተሸጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

ወይም ፡ ክፍያው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ድርሻ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ይህ ፡ ባለሀብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የመርከቡ ፡ ሀብት ፡ የጋራ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ድርሻውን ፡ በመያዣ ፡ የሰጠው ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ባይሆንም ፡ ሀብቱ ፡ ከተከፈለ ፡ ወይም ፡ በሐራጅ ፡ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ የመያዣው ፡ መብት ፡ እንዳለ ፡ ይቈያል።

(፬) መርከቡ ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በሐራጅ ፡ ሲሸጥ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ ላልሆነ ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ከመርከቡ ፡ ሀብት ፡ በከፊሉ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሽያጩ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ የሚኖራቸው ፡ በመያዣቸው ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፭) እንዲሁም ፡ በያንዳንዱ ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብቶች ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ከመርከቡ ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ለጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ በሚደርሳቸው ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ በግምታቸው ፡ ልክ ፡ የሚተላለፉ ፡ ይሆናሉ ።

## ቍ ፡ ፴፱ ። መያዣዎቹን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፴፰ ፡ የተፈቀደው ፡ ክስ ፡ እንዳይቀርብበት ፡ የሚፈልግ ፤ መርከቡን፡ ወይም ፡ የመርከቡን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ ክስ ፡ ሳይቀርብበት ፡ በዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የመግዛቱን ፡ ሥርዐት ፡ ካስመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ለመርከቡ ፡ በሆነ ፡ የመዝገብ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ለተመለከቱት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ የዚህኑ፡ገጽ ፡ ግልባጭ ፡ በመያዣ ፡ ማቋቋሚያ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ፡ መጥሪ፡ በሚቀበሉበት ፡ አድራሻ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

(፪) በዚህም ፡ በግዢው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ መርከቡን ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ መያዣ ፡ የተሰጠባቸውን ፡ ዕዳዎች ፡ የመክፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ ቢደርስም ፡ ባይደርስም ፡ መርከቡ ፡ በተሸጠበት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለዕዳ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ወዲያውኑ ፡ የሚከፍል ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፵ ። ከዋጋው ፡ በላይ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ስለ ፡ መጨመር ።

(፩) ከዋጋው ፡ በላይ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ በመጨመር ፡ ይህንኑ ፡ ዋጋና ፡ ያሉትን ፡ ዕዳዎች ፡ ለመክፈል ፡ ዋስትና ፡ በመስጠት ፡ ማንኛውም ፡ መዝገብ ፡ የገባ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ሁሉ ፡ መያዣ ፡ የሆነው ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ ክፍል ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ጥያቄ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ፈርሞበት ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለገዢው ፡ መተላለፍ ፡ አለበት ።

መግለጫውም ፡ መርከቡ ፡ በሚገኝበት ፡ አገር ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ በተመዘገበበት ፡ ወደብ ፤ መርከቡ ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ መታዘዙን ፡ እንዲያዩ ፡ የመቅረቢያ ፡ ጥሪ ፡ ይጻፍበታል ።

BACK



**ቊ ፡ ፵፩ ። ሐራጅ ፡ የሚጠይቅ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋውን ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።**

ማንኛውም ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መርከቡ ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ ጥያቄ ፡ ያላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዢው ፡ ዋጋውን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በማኖር ፡ ከነ በረበት ፡ መያዣነት ፡ መርከቡን ፡ ነጻ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ መርከቡ ፡ በዕዳ ፡ የተያዘበት ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፵፪ ። ስለ ፡ ሐራጅ ፡ ሽያጭ ።**

በሐራጅ ፡ የመሸጡ ፡ ጕዳይ ፡ ሐራጅ ፡ እንዲፈጸም ፡ በጠየቀው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ አመልካችነት ፡ ወይም ፡ በገዢው ፡ ጥያቄ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ በተደነገገው ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

**ቊ ፡ ፵፫ ። መርከቡ ፡ መያዣ ፡ የሆነበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያመለክት ፡ አጭር ፡ ሰሌዳ ።**

ማንኛውም ፡ መርከብ ፡ ሁሉ ፤ ሊገኙ ፡ ከሚገባቸው ፡ ወረቀቶች ፡ መካከል ፡ ለጕዞ ፡ በተነሣበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በሚጻፈው ፡ ሰነድ ፡ ውስጥ ፡ መርከቡ ፡ መያዣ ፡ የሆነበትን ፡ ሁኔታ ፡ መያዣዎቹ ፡ የተመዘገቡበትን ፡ ቀን ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ስምና ፡ መያዣ ፡ የተደረገበትን ፡ የገንዘቡን ፡ ልክ ፡ የሚገልጽ ፡ የዝርዝር ፡ መጻፊያ ፡ ሰሌዳ ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ።

**ቊ ፡ ፵፬ ። በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ መያዣ ፡ የሆነው ፡ መርከብ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ እንዳይሸጥ ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) በመርከቡ ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ መያዣ ፡ የሆነ ፡ መርከብ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ እንዳይሸጥ ፡ ክልክል ፡ ነው ። ይህን ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የተፈጸመ ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ መርከቡ ፡ በተመዘገበበት ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ሊጻፍ ፡ አይችልም ።

(፪) በመርከቡ ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ሳያስፈቅድ ፡ ይህን ፡ መያዣ ፡ የሆነውን ፡ መርከብ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ወስዶ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የሸጠ ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፵፩ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ መርከቡ ፡ አመዘጋገብና ፡ መርከቡን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ግዙፍ ፡ መብቶች ፡ አጻጻፍ ።

**ቊ ፡ ፵፭ ። ስለ ፡ መዝገቦቹ ።**

(፩) የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በመረጣቸው ፡ በየአንዳንዶቹ ፡

ወደቦች ፡ ውስጥ ፤ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ለመሆናቸው ፡ መተማመኛና ፡ መግለጫ ፡ እንዲሆኑ ፡ የተመደቡና ፡ እነዚሁ ፡ መርከቦች ፡ የሚመለከተው ፡ ግዙፍ፡ መብት ፡ የሚገለጽባቸው ፡ መዝገቦች ፡ ይከፈታሉ ።

(፪) ለነዚህም ፡ መዝገቦች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ገጽ ፡ ተራ ፡ ቊጥር ፡ ተሰጥቶ ፡ በየገጹ ፡ ላይ ፡ የመዝጋቢው ፡ ፊርማ ፡ ምልክት ፡ ይደረግበታል ። ይህ ፡ ቊጥርና ፡ መርከቡ ፡ የተመዘገበበት ፡ ቊጥር ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፫) ማንኛውም ፡ መርከብ ፡ የሚመዘገበው ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያው ፡ ወይም ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበልበት ፡ አድራሻ ፡ ባለበት ፡ ወደብ ፡ ነው ።

(፬) የመዛግብቱ ፡ አያያዝና ፡ አጻጻፍ ፡ የአመዘጋገባቸውም ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በልዩ፡ ደንቦች ፡ ይወሰናል ።

**ቊ ፡ ፵፪ ። የመርከቡ ፡ መለያ ፡ ምልክት ።**

(፩) ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ሁሉ ፡ በአማርኛና ፡ በላቲን ፡ ፊደል ፡ የተጻፈና ፡ በግልጽ ፡ የሚነበብ ፡ በደንብ ፡ የተወሰነ ፡ የመለያ ፡ ምልክት ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ፤ ይህም ፡ ምልክት ፡ በተለይ ፡ የመርከቡን ፡ ስምና ፡ መርከቡ ፡ የተመዘገበበትን ፡ የወደብ ፡ ስም ፡ ለይቶ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) በደንቡ ፡ መሠረት ፡ የተሰጡትን ፡ ቊጥሮች ፡ ወይም ፡ ጽሑፎችና ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ በደንብ ፡ መጠበቅ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብትና ፡ የመርከቡ ፡ ሹም ፡ ኀላፊነት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ አድራጎትና ፡ ዘዴ ፡ ማጥፋት ፡ መሸፈንና ፡ መሰረዝ ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ያልሆነውን ፡ መልክት ፡ ማድረግ ፡ በመርከቡ ፡ ባለሀብትና ፡ በካፒቴኑ ፡ ላይ ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ያስከትልባቸዋል ።

**ቊ ፡ ፵፫ ። የኢትዮጵያ ፡ መርከቦች ፡ አመዘጋገብ ።**

ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ በደንብ ፡ በተወሰነለት ፡ ቀንና ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ይመዘገባል ።

**ቊ ፡ ፵፬ ። የመርከቡ ፡ መመዝገብ ፡ የሚሰረዝበት ፡ ሁኔታ ።**

መርከቡ ፡ ላንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የተሸጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጠላት ፡ እጅ፡ የወደቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የተቃጠለ ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የጠፋ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከቡ ፡ በስሙ ፡ የተመዘገበበት ፡ ባለሀብት ፡ መርከቡ ፡ በተመዘገበበት ፡ ወደብ፡ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለመርከቡ ፡ መመዝገብ ፡ የተሰጠውን ፡ የመርከቡን፡ ዜግነት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ለማሰረዝ ፡ ለጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፵፭ ። ያልተመዘገበ ፡ መርከብ ፡ የሚያዝበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ማናቸውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ሁሉ ፡ መመዝገብ ፡ የሚገባው ፡ ሆኖ ፡ በሚገባ ፡ ሳይመዘገብ ፡ ሲገኝ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጀመሪያ ፡ በደረሰበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ ይያዛል ። በኢትዮጵያ ፡ የባሕር ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡

BACK



ሲጓዝ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአቅራቢያው ፡ ወደሚገኘው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደብ ፡ ከተመራ ፡ በኋላ ፡ በወደቡ ፡ አዛዥ ፡ እጅ ፡ ይያዛል ። ይህም ፡ የወደብ ፡ አዛዥ ፡ አንድ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ያዘጋጃል ። ይህም ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ለክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ። የፕሮሴቬርባሉም ፡ ግልባጭ ፡ ለሚኒስትሩ ፡ ይላካል ።

(፪) የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የመርከብ ፡ ማስመዝገብን ፡ ሥርዐት ፡ በደንብ ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመፈለግ ፡ ዐውቆ ፡ በፈቃዱ ፡ ሳያስመዘግብ ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፳፰ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጥፋት ፡ የተሠራው ፡ በቸልተኛነት ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፶፰ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፶ ። የመርከቡ ፡ መመዝገብ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) በሕይወት ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ የተደረገ ፡ ስምምነትና ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ አሠራር ፡ መጨረሻ ፡ የሆነ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፤ በጠቅላላውም ፡ በደንብ ፡ በተመዘገበ ፡ ባንድ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ግዙፍ ፡ መብት ፡ ለማቋቋም ፤ ለማስታወቅ ፤ ለሌላ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ ሲባል ፡ የተደረገ ፡ አሠራር ፡ ሁሉ ፡ ውጤት ፡ የሚያገኘው ፡ በመርከብ ፡ የመለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) በመርከብ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ግዙፍ ፡ የሆኑትን ፡ መብቶች ፡ የማስመዝገብ ፡ መብት ፡ የሚገኘው ፡ በስምምነት ፤ በአሠራሮች ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፤ ወይም ፡ ባ፩ኛው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከቱት ፡ የተሠሩ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ። ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ይህን ፡ ሥርዐት ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተበደለው ፡ ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱ ፡ ሳይነካ ፡ መብቱ ፡ በመለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ እንዲጻፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፶፩ ። የአመዘጋገቡ ፡ ፍጹም ፡ አስረጂነት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በመርከቡ ፡ የመለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘረውን ፡ ማስረጃና ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በተመዘገበው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ አንድ ፡ መብት ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያገኘው ፡ መብት ፡ ይጸናለታል ።

ቍ ፡ ፶፪ ። የአመዘጋገቡን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መሰረዝና ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ በመዝገብ ፡ መጻፍ ፤ በጽሑፍ ፡ መለዋወጥ ፡ ወይም ፡ መሰረዝ ፡ በመብቱ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በተዋዋ

ዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ፈቃድነት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የተጸፈው ፡ የተለዋወ ጠው ፡ ወይም ፡ የተሰረዘው ፡ ቀሪ ፡ እንዲሆን ፡ ወይም ፡ እንዲለዋወጥ ፡ ለመጠ የቅ ፡ ይችላል ።

(፪) መዝገቡ ፡ ከመሰረዙ ፡ ወይም ፡ ከመታረሙ ፡ በፊት ፡ ባንድ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያስመዘገቡትን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የመ ዝገቡ ፡ መታረም ፡ ወይም ፡ መሰረዝ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

<u>ስለ ፡ መርከቡ ፡ መያዝ ።</u>

ክፍል ፡ ፩ ።

<u>ለመጠባበቂያ ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።</u>

<u>ቍ ፡ ፶፫ ። ሁኔታዎች ።</u>

(፩) መርከቡ ፡ ስላለበት ፡ ዕዳ ፡ ለመጠባበቂያ ፡ እንዲያዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ውሳኔ ፡ በመርከቡ፡በማረፊያ ፡ ወይም ፡ በመተላለፊያ ፡ ወደብ ፡ ውስጥ ፡ ቢሆንም ፡ ወይም ፡ ካፒቴኑ ፡ ለጉዞው ፡ ፈቃድ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

<u>ቍ ፡ ፶፬ ። ዋስትናዎችን ፡ ስለ ፡ መስጠት ፤ መያዣዎችን ፡ ስለ ፡ ማስለቀቅ ።</u>

(፩) መርከቡ ፡ እንዲያዝ ፡ የጠየቀው ፡ ወገን ፡ የመያዙ ፡ ጉዳይ ፡ ሊያስከትል ፡ ስለ ሚችለው ፡ ጉዳት ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ የሚችል ፡ ለመ ሆኑ ፡ በቂ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ጠያቂውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያስገ ድደው ፡ ይችላል ።

(፪) አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ የተያዘው ፡ መርከብ ፡ እንዲለቀቅለት ፡ ተከላካዩ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ በቂ ፡ የሆነና ፡ እር ግጠኛ ፡ ዋስትና ፡ ከተሰጠ ፡ የተያዘው ፡ መርከብ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ይታዘዛል ።

<u>ቍ ፡ ፶፭ ። መርከቡ ፡ እንዲያዝ ፡ የታዘዘበትን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።</u>

(፩) መርከቡ ፡ እንዲያዝ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የታዘዘበት ፡ ጽሑፍ ፡ አንድ ፡ ግልባጭ ፡ ለካ ፒቴኑ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ስለእሱ ፡ ሆኖ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ለሚገ ኘው ፡ ተተኪ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) የመያዙንም ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽመው ፡ ሠራተኛ ፡ የተያዘው ፡ መርከብ ፡ ይታገ ድልኝ ፡ ከሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ጋራ ፡ መርከቡ ፡ ከተያዘበት ፡ ወደብ ፡ አዛዥ ፡ ወዲ ያውኑ ፡ የማዘዣውን ፡ ግልባጭ ፡ ይሰጣል ።

BACK



(፫) መርከቡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መዝጋቢው ፡ ይህ ፡ መር ከብ ፡ የተያዘ ፡ መሆኑን ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ያመለ ክታል ።

ቍ ፡ ፶፫ ። የመቅረቢያ ፡ ጥሪ ።

(፩) የመጠበቂያ ፡ መያዣ ፡ በተደረገበት ፡ ፕሮሲቬርባል ፡ ውስጥ ፡ የመርከቡ ፡ ካፒ ቴን ፡ ሥልጣን ፡ ወዳለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚል ፡ ትእ ዛዝ ፡ ይኖርበታል ። ጉዳዩ ፡ የሚታይበት ፡ ቀጠሮ ፡ መርከቡ ፡ ከተያዘበት ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ የመያዙ ፡ ጉዳይ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ ከሠላሳ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ሊዘገይ ፡ አይገባውም ።

(፪) ይህም ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሻሻል ፡ ወይም ፡ ሊራዘም ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፶፬ ፡ የማጽናት ፡ ፍርድ ።

(፩) የመያዙን ፡ ውሳኔ ፡ የሚያጸናው ፡ ፍርድ ፡ የመሸጥ ፡ ትእዛዝ ፡ የሽያጩን ፡ ዋጋ ፡ የሽያጩን ፡ ሁኔታዎች ፤ የሽያጩንና ፡ ሐራጅ ፡ የሚባልበትን ፡ ቀን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ የሚነገርበትን ፡ ጭምር ፡ ያዛል ። የፍርዱን ፡ ውሳኔ ፡ ለመቃወም ፡ አይቻልም ።

(፪) የሚጠየቀው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ቢሆንም ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ። ይግባኙም ፡ ፍርዱ ፡ በተሰጠ ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለ በት ።

ለይግባኝ ፡ የተወሰነው ፡ የ፲፭ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍና ፡ ይግባኙም ፡ በፍርድ፡ እስኪወሰን ፡ የፍርዱ ፡ መፈጸም ፡ ይታገዳል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ፍርድን ፡ ስለ ፡ ማስፈጸም ።

ቍ ፡ ፶፭ ። ፍርድን ፡ ለማስፈጸም ፡ እንዲጠበቅ ፡ የተወሰነ ፡ አነስተኛ ፡ ጊዜ ።

ስለ ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችለው ፡ የዕዳ ፡ መክፈል ፡ ጥያቄ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሐያ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፶፬ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ሊፈጸም ፡ የማይቻልበት ፡ ሁኔታ ።

ለሚሰናዳው ፡ ጉዞ ፡ ለገባባቸው ፡ ዕዳ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማረፊያ ፡ ወደብ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ካፒቴኑ ፡ ለጕዞው ፡ ፈቃድ ፡ ከተቀ በለ ፡ በኋላ ፡ መርከቡን ፡ አሲዞ ፡ የማሸጥ ፡ ተግባር ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፷ ። የመክፈል ፡ ጥያቄ ።

(፩) የመክፈል ፡ ጥያቄ ፡ ለባለሀብቱ ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበልበት ፡ አድራሻ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

(፪) ባለሀብቱ ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚጠየቀው ፡ ዕዳ ፡ ለመርከቡ ፡ ወይም ፡ ለጉዞው ፡ ጉዳይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመክፈሉ ፡ ጥያቄ ፡ ለካፒቴኑ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፷፩ ። ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ እንዲጠበቅ ፡ የተወሰነ ፡ ከፍተኛ ፡ ጊዜ ።**

የመክፈሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርዱን ፡ ከማስፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ትእዛዙን ፡ ማደስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፷፪ ። በፍርድ ፡ ማስፈጸሚያው ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ መረጃዎች ።**

የፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ ሠራተኛ ፡ በፕሮሴቬርባል ፡ ውስጥ ፡ ሊዘረዝረው ፡ የሚገባው ።

(ሀ) ወኪል ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራለትን ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ስም ፡ የሞያ ፡ ሥራውንና ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራውን ፤

(ለ) ይገባኛል ፡ በማለት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ የተመሠረተበትን ፡ ጉዳይና ፡ መጠኑ፤

(ሐ) ሽያጩ፡እንዲፈጸም ፡ ክስ ፡ በቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን፡ውስጥና ፡ የተያዘው ፡ መርከብ ፡ መልሕቅ ፡ ጥሎ ፡ በቆመበት ፡ ስፍራ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የመረጠውን ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበልበት ፡ አድራሻ ።

(መ) የመርከቡን ፡ ባለሀብትና ፡ የካፒቴኑን ፡ ስም ፤

(ሠ) የመርከቡን ፡ ስም ፤ ዐይነቱን ፡ ክብደቱንና ፡ ዜግነቱን ፡ ነው ።

(ረ) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከመርከቡ ፡ ጋራ ፡ ያሉትን ፡ ባለሞተር ፡ ጀልባዎች ፤ ትንንሽ ፡ ጀልባዎች ፤ ተጨማሪ ፡ ዕቃዎች ፤ መሣሪያዎች ፡ ሥንቆች ፡ መዘርዘርና፡ መጻፍ ፡ አለበት ፤ ጠባቂም ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፷፫ ። ማስታወቂያና ፡ ጥሪ ።**

(፩) የመያዙ ፡ ጉዳይ ፡ በተፈጸመ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መርከቡን ፡ ያስያዘው ፡ ሰው ፡ የመዠመሪያውን ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ግልባጭ ፡ ለባለሀብቱ ፡ መላክና ፡ የተያዙትም ፡ ዕቃዎች ፡ ሊሸጡ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰማ ፤ መርከቡ ፡ ከተያዘበት ፡ ቦታ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሀብቱን ፡ ማስጠራት ፡ አለበት ።

(፪) የባለሀብቱ ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ የፍርዱን ፡ ውሳኔ፡በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማስታወቂያዎቹና ፡ የመጥሪያው ፡ ትእዛዞች ፡ ለተያዘው ፡ መርከብ ፡ ካፒቴን ፡ እሱም ፡ ከሌለ ፡ ለባለሀብቱ ፡ ወይም ፡ የካፒቴኑ ፡ እንደራሴ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሊሰጣቸው ፡ ይገባል ።

(፫) የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡ ውስጥ ፡ ደንበኛ ፡ የመኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ መቀመጫ ፡ ቦታ ፡ የሌለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ እንደራሴም ፡ ያልኖረው ፡ ሲሆን ፡ የማስታወቂያው ፡

BACK



(የጥሪው) ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፳፬ ፡፡ ፕሮሴቬርባሉን ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ፡፡**

(፩) የመያዙ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ መርከቡ ፡ በተመዘገበበት ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ወደብ ፡ ባለው ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ፡፡

(፪) ይህም ፡ የመመዝገብ ፡ ጉዳይ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ መርከቡ ፡ የተያዘበት ፡ ባለዕዳ ፡ መርከቡን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ መያዥ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ፡፡

**ቍ ፡ ፳፭ ፡፡ በመዝገብ ፡ ለተጻፉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ፡፡**

(፩) ይህ ፡ ጉዳይ ፡ መዝገብ ፡ ከገባበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መርከቡን ፡ ለመመዝገብ ፡ የተሾመው ፡ መዝጋቢ ፡ የጽሑፉን ፡ አመዘጋገብ ፡ ዐይነት ፡ መግለጫ ፡ በመዝገብ ፡ ለተጻፉት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይሰጣል ፡፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ መግለጫ ፡ ከተሰጠ ፡ አንሥቶ ፡ በሚከተለው ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለእነዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በተመዘገቡት ፡ ላይ ፡ በተመረጠው ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበሉበት ፡ አድራሻቸው ፡ በ፳፫ኛው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ ጥሪ ፡ መርከቡ ፡ ይያዝልኝ ፡ ባዩ ፡ ያስታውቃቸዋል ፡፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ጥሪው ፡ ከደረሳቸው ፡ ጀምሮ ፡ በጉዳዩ ፡ ለመግባት ፡ የ፲፭ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ አላቸው ፡፡

(፪) መርከቡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቆንስሉ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የተሰጡትን ፡ መያዣዎች ፡ የሚገልጽ ፡ ዝርዝር ፡ በሰጠ ፡ በ፰ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ ዝርዝር ፡ ለተመዘገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ማስታወቂያ ፡ ይላክላቸዋል ፡፡ እነዚህም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በጉዳዩ ፡ ለመግባት ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ አላቸው ፡፡ ይህንኑም ፡ ጊዜ ፡ ለማራዘም ፡ ይቻላል ፡፡

**ቍ ፡ ፳፮ ፡፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡፡**

(፩) የሽያጩ ፡ ጉዳይ ፡ የሚታዘዘው ፡ የመያዙን ፡ ትእዛዝ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ሆኖ ፡ ይህም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ የሚሸጥበትን ፡ ቀንና ፡ የሐራጁን ፡ መነሻ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሁም ፡ ያዢው ፡ በሚያመለክተው ፡ መሠረት ፡ የሽያጩን ፡ ሁኔታ ፡ ይወስናል ፡፡

(፪) ለሽያጩ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ገዢ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ወስኖት ፡ ከነበረው ፡ የሽያጭ ፡ መነሻ ፡ ዋጋ ፡ ያነሰ ፡ አዲስ ፡ ዋጋና ፡ እንዲሁም ፡ ወደፊት ፡ ጨረታ ፡ የሚደረግበትን ፡ ቀን ፡ ይወስናል ፡፡

**ቍ ፡ ፹፪ ። ሐራጅ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ማመልከት።**

(፩) ሐራጅ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ለማስታወቅ ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ የጨረታ ፡ ሽያጭ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበው ፡ የሐራጅ ፡ ጕዳይ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሽያጩ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይከፈል ፡ ለማሳገድ ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ መቃወሚያዎች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ናቸው ።

(፫) እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ማመልከቻዎች ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ ለመቀበል ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፹፫ ። በቍጥር ፡ ፹፪ ፡ ለተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አፈጻጸም ፡ የማመልከቻዎቹ ፡ አቀራረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ወይም ፡ ሐራጁን ፡ የሚቃወመው ፡ ሰው ፡ የሚቃወምበትን ፡ ምክንያት ፡ ለማቅረብ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ አለው ። ተከሳሹም ፡ መከራከሪያውን ፡ ለማቅረብ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ጕዳዩም ፡ ጥሪ ፡ በመላክ ፡ ብቻ ፡ በችሎት ፡ ይታያል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲታገድ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ የሐራጁ ፡ መፈጸም ፡ አይታገድም ።

**ቍ ፡ ፹፬ ። የተያዘ ፡ መርከብ ፡ ሽያጭ ።**

በቍጥር ፡ ፹፭ ፡ በተዘረዘረው ፡ መሠረት ፡ የተጻፉት ፡ ተለጣፊ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ተጽፈው ፡ ከተገለጹና ፡ በሁለት ፡ ጋዜጣዎች ፡ የሚወጣው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከታወጀ ፡ ሌሎችም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያዛቸው ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ከተፈጸሙና ፡ ታትመው ፡ ከወጡበት ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሽያጩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊፈጸም ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፹፭ ። የመግለጫዎቹና ፡ የተለጣፊ ፡ ማስታወቂያዎቹ ፡ አገላለጽ ።**

መግለጫዎቹና ፡ ተለጣፊዎች ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ጕዳዮች ፡ ማመልከት ፡ አለባቸው ።

(ሀ) የከሳሹን ፡ ስም ፤ ሥራውንና ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፤ ስፍራውን ፤

(ለ) ይገባኛል ፡ በማለት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ የተመሠረተበትን ፡ ጕዳይ ፤

(ሐ) ሊከፈለው ፡ የሚገባውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፤

(መ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚያስችልበት ፡ ስፍራና ፡ የተያዘው ፡ መርከብ ፡ መልሕቅ ፡ ጥሎ ፡ በቆመበት ፡ ስፍራ ፡ ከሳሹ ፡ የመረጠውን ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበልበት ፡ አድራሻ ፤

(ሠ) ለተያዘው ፡ መርከብ ፡ የባለሀብቱ ፡ ስም ፡ ሥራውንና ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራውን ፤

(ረ) በመርከብ ፡ የመለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የመርከቡን ፡ ዝር ዝር ፡ ዐይነት ፡ ሁኔታ ፤

(ሰ) የካፒቴኑን ፡ ስም ፤

(ሸ) መርከቡ ፡ የሚገኝበትን ፡ ስፍራ ፤

(ቀ) ለሽያጩ ፡ መነሻ ፡ የሆነውን ፡ ዋጋና ፡ ሁኔታዎች ፤

(በ) ጨረታው ፡ የሚደረግበትን ፡ ቀን ፡ ሰዓትና ፡ ስፍራ ።

ቍ ፡ ፸፩ ። የዋጋ ፡ ማበላለጥ ፡ ጨረታ ፡ ማድረግን ፡ ጒዳይ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

ሽያጩ ፡ በፍርድ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የዋጋ ፡ ማበላለጥ ፡ ጨረታ ፡ ማድረግ ፡ ክልክል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፸፪ ። የጨረታውን ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

በጨረታ ፡ ገዥ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የገዛበትን ፡ ዋጋ ፡ ያለ ፡ ኪሣራ ፡ ጨረታው ፡ በተደረገ ፡ በሐያ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ መንግሥት ፡ ለፈቀደላቸው ፡ ባንኮች ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ። ይህን ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ለጨረታ ፡ የቀረበው ፡ መርከብ ፡ በተገኘ ፡ ዋጋ ፡ እንዳወጣ ፡ ይሸጣል ።

ቍ ፡ ፸፫ ። በተገኘ ፡ ዋጋ ፡ በሐራጅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

ገንዘቡን ፡ ሳያስረክብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በ፷፱ኛው ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ መግለጫዎቹ ፡ ተለጣፊዎቹ ፡ ማስታወቂያዎቹ ፡ በታወጁ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በተጫራቹ ፡ ሒሳብና ፡ ከሣራ ፡ ለሐራጅ ፡ የቀረበው ፡ መርከብ ፡ እንዳወጣ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለጨረታ ፡ ይቀርባል ፤ ገንዘቡን ፡ ሳያስረክብ ፡ የቀረው ፡ ተጫራችም ፡ የሚጐድለውን ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፸፬ ። የአቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ።

በቍጥር ፡ ፸፫ ፡ መሠረት ፡ በተፈጸመ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ በቍጥር ፡ ፷፯ ፡ (፪) መሠረት ፡ መቃወሚያ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

ስለ ፡ ሆነም ፡ ሽያጩ ፡ በተፈጸመ ፡ በ፰ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በፍርዱ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዐት ፡ ጒድለት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ለበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ። ይግባኙም ፡ የሚሰማበት ፡ ቀን ፡ መጥሪያው ፡ ከወጣበት ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መሆኑ ፡ በመጥሪያው ፡ ውስጥ ፡ ይገለጻል ።

ቍ ፡ ፸፭ ። የሐራጅ ፡ ጨረታውን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።

ፍርዱ ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ስለ ፡ ሐራጁ ፡ ሽያጭ ፡ የተሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ጠያቂነት ፡ በመርከብ ፡ መለያ ፡ ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፺፮ ፡ የሐራጁ ፡ ሽያጭ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

የመርከቡ ፡ በሐራጅ ፡ መሸጥ ፡ በእሱ ፡ ላይ ፡ ከተሰጡት ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ መያዣዎች ፡ ወይም ፡ በ፫፻ኛው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ማስታወቂያ ፡ የደረሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ካላቸው ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ መርከቡን ፡ ነጻ ፡ ያደርገዋል ። እንዚህንም ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ መያዣዎችና ፡ የተባሉትንም ፡ የክስ ፡ መብቶች ፡ ለማሰረዝ ፡ የሚቻለው ፤ በጨረታ ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ የጨረታውን ፡ ፍርድና ፡ ፍርዱንም ፡ የሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ፍርዱ ፡ የመጨረሻ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጸውን ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ለመርከቡ ፡ መመዝገቢያ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፺፯ ። የገንዘቡ ፡ መከፋፈል ።

ከጨረታው ፡ ሽያጭ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፋፈለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

አንቀጽ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ መርከቡ ፡ ባለሀብቶች ፤ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ ስለ ፡ ካፒቴኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ስለመርከቡ ፡ ባለመብቶችና ፡ ስለሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ኀላፊነት ።

ቍ ፡ ፻፺፰ ። የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ትርጓሜ ።

ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ማለት ፡ የመርከቡን ፡ ሥራ ፡ የሚያከናውነው ፡ ነው ። ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ባለሀብቱ ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፻፺፱ ። በባለሀብቱ ፡ ላይ ፡ አላፊነት ፡ የሚያስከትሉ ፡ ነገሮች ።

ካፒቴኑ ፡ የመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፤ መርከብ ፡ ነጂው ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ማንኛቸውም ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥፋት ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ረገድ ፡ በአላፊነት ፡ ተጠያቂ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ መርከቡንና ፡ ጕዞውን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ካፒቴኑ ፡ የሚገባበትን ፡ ግዴታዎች ፡ ባለሀብቱ ፡ ለመፈጸም ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፪፻ ። የኀላፊነት ፡ ወሰን ።

(፩) ባለሀብቱ ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፮ ፡ በተወሰነው ፡ መጠን ፡ ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ካንዱ ፡ ወይም ፡ ከሌላው ፡ ለሚመነጩ ፡ ዕዳዎች ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(ሀ) በመርከብ ፡ ላይ ፡ በተሳፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደርስ ፡ የሕይወት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳትና ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ዕቃዎች ፡ ለሚደርስ ፡ ጥፋትና ፡ ጕድለት ፤

(ሰ) በማንኛቸውም ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ አጥፊነት ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመሬት ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደርስ ፡ የሕይወት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ በማንኛቸው ፡ ዕቃዎችና ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ለሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ የመብት ፡ መነካትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሆነውና ፡ እነዚህም ፡ የተባሉት ፡ ተግባሮች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ወይም ፡ ከመርከቡ ፡ ውጭ ፡ በሆኑ ፡ ባለሀብቱ ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆንባቸው ፡ የማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አጥፊነት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ሲሆን ፤

ስለ ፡ ሆነም ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ አጥፊነት ፡ ለተደረገው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆነው ፡ በመርከቡ ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ በያዛቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ መጫን ፤ ማውረድ ፤ ማመላለስ ፡ ወይም ፡ ተሳፋሪዎችን ፡ ማሳፈርንና ፡ ማውረድን ፡ የሚመለከቱ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(ሐ) ጉዳት ፡ የደረሰበትን ፡ መርከብ ፡ ለማውጣትና ፡ የሰጠመውን ፡ የተጣለውን ፡ ወይም ፡ የተተወውን ፡ መርከብ ፡ ከመርከቡም ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ጭምር ፡ ለማውጣት ፡ ለማንሣት ፡ ወይም ፡ ለማፈራረስ ፡ በማንኛውም ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠ ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ ኀላፊነትና ፡ የወደብ ፡ ሥራዎች ፡ የባሕር ፡ ግድቦችና ፡ በመርከብ ፡ መተላለፊያ ፡ የውሃ ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ በሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ፡ ምክንያት ፡ ለሚመጣው ፡ ማናቸውም ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ ኀላፊነት ፤

(፪) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ አካል ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ የሚደረገው ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ማለት ፡ በሕይወት ፡ ወይም ፡ በአካል ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ የሚደረግ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ስለ ፡ ንብረት ፡ የሚደረግ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሌሎች ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄዎች ፡ ይጠቀልላል ።

## ቍ ፡ ፹፩ ። የመርከቡ ፡ ባለቤት ፤ ባለይዞታ ፤ ጠባቂ ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪ ፡ በመሆን ፡ የሚመጣ ፡ ኀላፊነት ።

ባለቤቱ ፡ በበኩሉ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ሳይገኝበት ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ባለይዞታ ፡ ጠባቂ ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጥፋት ፡ ኀላፊ ፡ ከሚሆንላቸው ፡ ሰዎች ፡ ቸልተኛነት ፡ የተነሣ ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ሳያሻ ፡ ቀጥታ ፡ ኀላፊ ፡ ስለሚሆንባቸው ፡ ጕዳዮችም ፡ ቢሆን ፡ በቍጥር ፡ ፹ ፡ ስለ ፡ ተዘረዘሩት ፡ ብቻ ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆን ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ መወሰን ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፺፪ ፡፡ ኀላፊነትን ፡ መወሰን ፡ የማይቻልበት ፡ ሁኔታ ፡፡

በቊጥር ፡ ፺ ፡ እና ፡ ፺፩ ፡ የተገለጹት ፡ ማንኛዎችም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ጕዳዮች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ፡፡

(ሀ) ስለ ፡ ጉዳት ፡ በሚደረግ ፡ መዋጮና ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማዳን ፡ በሚደረጉ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄዎች ፡ ላይ ፤

(ለ) የመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ አባሎች ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ማንኛ ውም ፡ የባለሀብቱ ፡ አሽከር ፡ ወይም ፡ ከመርከቡ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ በመ ርከቡ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ማንኛዎችም ፡ የባለመርከቡ ፡ አሽከሮችና ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ በነሱ ፡ ጥግ ፡ የሚተዳደሩት ፡ ስለሚያደርጉት ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፤

(ሐ) ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ለጥያቄው ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ዕዳ ፡ በባለቤቱ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ዕዳው ፡ መድረሱን ፡ እያወቀ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

ቊ ፡ ፺፫ ፡፡ ስለ ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ፡፡

የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚያስችል ፡ በዚያው ፡ እርሱ ፡ እንዲከፍል ፡ በተጠየቀበት ፡ ሁኔታ ፡ የመጣ ፡ ሌላ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ሒሳብ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይቻቻ ላል ፡፡ ስለ ፡ ተራፊውም ፡ ሒሳብ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ፡፡

ቊ ፡ ፺፬ ፡፡ ኀላፊነትን ፡ ስለ ፡ አለመቀበል ፡፡

የተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ መኖሩን ፡ የመግለጽ ፡ ተግባር ፡ ኀላፊነትን ፡ እንደ ፡ መቀ በል ፡ አያስቈጥርም ፡፡

ቊ ፡ ፺፭ ፡፡ የተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ አወሳሰን ፡፡

(፩) በቊጥር ፡ ፺፮ ፡ የተወሰነው ፡ የኀላፊነት ፡ ልክ ፡ በሌላ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ የሚመ ጡት ፡ ወይም ፡ የመጡ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ባለመመልከት ፡ በማንኛዎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ በጠቅላላውም ፡ በሰውነትና ፡ በንብ ረት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ደረሱ ፡ ጉዳቶች ፡ በሚደረግ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ተፈ ጻሚ ፡ ይሆናል ፡፡

(፪) በማንኛውም ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ የተጠየቀው ፡ ገንዘብ ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ በቊጥር ፡ ፺፮ ፡ ከተወሰነው ፡ የኀላፊነት ፡ ልክ ፡ የሚበልጥ ፡ ሲሆን ፡ ለዚህ ፡ ኀላፊነት ፡ የተመደበው ፡ ጠቅላላው ፡ ሒሳብ ፡ በተለይ ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡ ሆኖ ፡ ይቋቋማል ፡፡

(፫) ይህ ፡ የተቋቋመ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈለው ፡ ኀላፊነቱ ፡ ተወስኗል ፡ ለሚባልበት ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡

(፬) ይህ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ ከተቋቋመ ፡ በኋላ ፡ እና ፡ የኀላፊነቱ ፡ ገንዘብ ፡ ለገ

ንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ጥቅም ፡ የሚውል ፡ ከሆነ ፡ በተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያቀርብ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ ከመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ ማድረግ ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፹፯ ። ለተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ የሚከፈል ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ።</u>

(፩) አንድ ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብት ፡ በቍጥር ፡ ፹ ፡ እና ፡ ፹፩ ፡ መሠረት ፡ ከሚደር ስበት ፡ አላፊነት ፡ ገንዘብ ፡ በመክፈል ፡ ለመወሰን ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) የተደረገው ፡ ጉዳት ፡ የደረሰው ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ሲሆንና ፡ የሚጠየቀውም ፡ ካሣ ፡ ከመርከቡ ፡ ጠቅላላ ፡ ክብደት ፡ በያንዳንዱ ፡ ቶን ፡ ፻፷ ፡ የኢት/ ብር ፡ የሚያስከፍል ፡ ሲሆን ፤

(ለ) የተደረገው ፡ ጉዳት ፡ የደረሰው ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ሲሆንና ፡ የሚጠየቀ ውም ፡ ካሣ ፡ ከመርከቡ ፡ ጠቅላላ ፡ ክብደት ፡ በያንዳንዱ ፡ ቶን ፡ ፭፻፲፮ ፡ የኢት/ ብር ፡ የሚያስከፍል ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) የተደረገው ፡ ጉዳት ፡ የደረሰው ፡ በሰው ፡ አካልና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ሆኖ የሚጠየቀውም ፡ ጠቅላላ ፡ ካሣ ፡ በመርከቡ ፡ ክብደት ፡ በያንዳንዱ ፡ ቶን ፡ ፭፻፲፮ ፡ የኢት/ ብር ፡ ሲሆን ፡ ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ታስቦ ፡ የመጀመሪያው ፡ ድርሻ ፡ ፫፻፶፮ ፡ ብር ፡ በመርከቡ ፡ ክብደት ፡ በያንዳንዱ ፡ ቶን ፡ ታስቦ ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ለሚደርስ ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ይመደብና ፡ ሁለተኛው ፡ ድርሻ ፡ ፻፷ ፡ —ደግሞ ፡ በያንዳንዱ ፡ የመርከብ ፡ ክብደት ፡ ቶን ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ይመደባል ።

ስለ ፡ ሆነም ፡ ይህ ፡ የተመደበው ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ አካል ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ የሚ ጠየቀውን ፡ በሙሉ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀሪውን ፡ ሒሳብ ፡ ከሁለተኛው ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ለመክፈል ፡ እንዲቻል ፡ ስለ ፡ ንብረት ፡ ከሚጠየቀው ፡ ካሣ ፡ ጋራ ፡ በመጠኑ ፡ ደረጃ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) የተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ እያንዳንዱ ፡ ድርሻ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የሚከፈለው ፡ እነዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በይገባኛል ፡ ጠይቀው ፡ በማስረጃ ፡ ባረጋገጡት ፡ መጠን ፡ ነው ።

(፫) ተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ ከመከፋፈሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ በቍ ጥር ፡ ፹ ፡ የተገለጸውን ፡ ማንኛውንም ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ከፍሎ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሱ ፡ ላይ ፡ ዕዳውን ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ በተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ይኖረው ፡ የነበረውን ፡ መብት ፡ ይዞ ፡ መተካት ፡ ይችላል ። ስለ ሆነም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ መጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ እሱ ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ በክስ ፡ ጠይቆ ፡ ማግኘት ፡ ይችል ፡ እስከ ፡ ነበረው ፡ መጠን ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፬) የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ በቍጥር ፡ ፻ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄዎች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመክፈል ፡ የምገደደው ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የመርከብ ፡ ባለቤት ፡ በዚያው ፡ እንዲከፍል ፡ በሚፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ እንዲችልና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ ማረጋገጥ ፡ እንዲችል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተቀማጩ ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ በተለይ ፡ እንዲከበርለት ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፻፯ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።</u>

ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ መወሰኛ ፡ ገንዘብ ፡ አቋቋምና ፡ አከፋፈል ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ደንቦችና ፡ ሥነ ፡ ሥርዐቶች ፡ በድንጋጌ ፡ ይወሰናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፻፰ ። የመርከቡ ፡ ክብደት ፡ የሚታሰብበት ፡ ሁኔታ ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የመርከቡ ፡ የክብደት ፡ መጠን ፡ የሚታሰበው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

በእንፋሎት ፡ ኀይል ፡ ለሚንቀሳቀሱ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ በሜካኒዝም ፡ ለሚንቀሳቀሱ ፡ መርከቦች ፡ ካልተጣራው ፡ ክብደት ፡ የተጣራውን ፡ (ወረጋ) ፡ ክብደት ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ሞተሮች ፡ ስለ ፡ ያዙት ፡ ቦታ ፡ የተቀነሰውን ፡ ክብደት ፡ በተጣራው ፡ ክብደት ፡ ላይ ፡ በመደመር ፡ ነው ።

ለሌሎች ፡ መርከቦች ፡ ሲሆን ፡ የተጣራው ፡ ክብደት ፡ ብቻ ፡ ይታሰባል ።

<u>ቍ ፡ ፻፱ ። ስለ ፡ መርከቡ ፡ መያዝ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ።</u>

(፩) ማንኛውም ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ ኀላፊነቱን ፡ ለመወሰን ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብት ፡ ሁሉ ፡ መርከቡ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ በዚያው ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ የተያዘበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ መታሰርን ፡ ለማስወገድ ፡ ሲባል ፡ ሌላ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ በሚደርስበት ፡ ኀላፊነት ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመስጠቱ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ካቀረበና ፡ ይህም ፡ የተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ በመብቱ ፡ መሠረት ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ጥቅም ፡ የሚውል ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መርከቡ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) አስቀድሞ ፡ የሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማረጋገጫ ፡ ባለቤቱ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ ከሚደርስበት ፡ ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ልክ ፡ ያነሰ ፡ ቢሆንም ፡ ለቀሪው ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ማረጋገጫ ፡ ከሰጠ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተደነገገው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ ለሚደርስበት ፡ ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ልክ ፡ የሰጣቸው ፡ ዋስትናዎችና ፡ ሌሎችም ፡ ማረጋገጫዎች ፡ በተባሉት ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ለሚመጡ ፡ ዕዳዎችና ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ኀላፊነቱን ፡ ለወሰነባቸው ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሁሉ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፺ ። ስለ ፡ መርከቡ ፡ ኀላፊነት ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የባለመርከቡ ፡ ኀላፊነት ፡ የተባለ ፡ ኀላፊነት ፡ ሁሉ ፡ የመርከቡን ፡ የራሱን ፡ ኀላፊነት ፡ ይጨምራል ።

ቍ ፡ ፺፩ ። የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ባልሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ።

በቍጥር ፡ ፺፪ ፡ የተደነገገው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመርከቡ ፡ ተከራይ ፤ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ኦፔራተርና ፡ በካፒቴኑ ፡ በአባሎቹ ፡ ላይና ፡ እንዲሁም ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ በባለቤቱ ፤ በተከራዩ ፤ በሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ወይም ፡ በኦፔራተሩ ፡ አሽከሮች ፡ ላይም ፡ በመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ላይ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡ ይፈጸማሉ ።

ስለ ፡ ሆነም ፡ በተገለጹት ፡ ሁኔታዎች ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤትና ፡ የነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ኀላፊነት ፡ በቍጥር ፡ ፹፯ ፡ መሠረት ፡ ከተወሰነው ፡ ልክ ፡ ሊያልፍ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፺፪ ። በመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።

ለዕዳው ፡ መምጣት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ የደረሰው ፡ በካፒቴኑ ፡ ወይም ፡ ከአባሎቹ ፡ ባንደኛቸው ፡ የግል ፡ ጥፋት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ በመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ በአባሎቹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ኀላፊነታቸውን ፡ የተወሰነ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ራሱ ፡ የመርከቡ ፡ ተከራይ ፡ የመርከቡ ፡ የጋራ ፡ ባለቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ ኦፔራተር ፡ ወይም ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የሠራተኞቹ ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ሲፈጸምበት ፡ ለተደረገው ፡ ተግባር ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ኀላፊ ፡ እንዲሆን ፡ የሚወሰነው ፡ የመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፺፫ ። የጭነታቸው ፡ ክብደት ፡ ከ፫፻ ፡ ቶን ፡ ያነሱ ፡ መርከቦች ።

የጭነታቸው ፡ ክብደት ፡ ከ፫፻ ፡ ቶን ፡ ያነሱ ፡ መርከቦች ፡ ባለቤት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፹፯ ፡ ከተመለከተው ፡ ኀላፊነት ፡ በማይበልጥ ፡ ወይም ፡ ለዕዳው ፡ መጠየቅ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ ከነበረው ፡ ዋጋ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሆነ ፡ ግምት ፡ ኀላፊነቱን ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ካፒቴኑ ።

### ቍ ፡ ፺፬ ። የካፒቴኑ ፡ ሹመትና ፡ ተግባር ።

(፩) ካፒቴኑን ፡ የሚሾመው ፡ የመርከቡ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ አከራይ ፡ ነው ። መርከቡ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ ጕዞ ፡ የሚመራው ፡ ካፒቴኑ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ካፒቴኑ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ሥራውን ፡ ለመቀጠል ፡ የማያስችለው ፡ ነገር ፡ ያጋጠመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ምትክ ፡ የሚሆነው ፡ በማዕርግ ፡ ደረጃ ፡ ተከታታይነት ፡ ከሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ተከታይ ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ መኰንን ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ካፒቴን ፡ ለመተካት ፡ እንዲቻል ፡ ካፒቴኑን ፡ ለቀጠረው ፡ ሰው ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባል ።

### ቍ ፡ ፺፭ ። የካፒቴኑ ፡ ሹመት ፡ የሚያልቅበት ፡ ሁኔታ ።

ካፒቴኑን ፡ የቀጠረው ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የካፒቴኑ ፡ ሹመት ፡ እንዲቀር ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፺፮ ። የካፒቴኑ ፡ ሥልጣን ።

(፩) በቍጥር ፡ ፺፯ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ካፒቴኑ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ወኪል ፡ ነው ።

(፪) በፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሆኖ ፡ ይቀርባል ።

(፫) በመርከቡና ፡ በጭነቱ ፡ ጥቅም ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ በሕግ ፡ የተፈቀዱለትን ፡ ሥልጣኖቹን ፡ ይሠራባቸዋል ።

### ቍ ፡ ፺፯ ። የካፒቴኑ ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ።

(፩) ካፒቴኑ ፡ ለሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሌላ ፡ እንደራሴ ፡ በሌለው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ለመርከቡ ፡ መልካም ፡ አጠባበቅና ፡ ለጕዞው ፡ ድርጅት ፡ አስፈላጊ ፡ በሚሆንበት ፡ ረገድ ፡ ሁሉ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፪) የመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ የተዋዋላቸው ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ በቍጥር ፡ ፲፭ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በመርከቡና ፡ በጭነቱ ፡ ኪራይ ፡

BACK



ላይ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ። እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ ጭነቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ በማለት ፡ የተሠሩ ፡ እንደሆን ፡ በተጨማሪ ፡ በቍጥር ፡ ፴፱ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) ፡ እና ፡ በ፪፻፹፫ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ቀጥሎ ፡ ደረጃ ፡ የሚሰጠው ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ይፈጥራሉ ።

(፫) ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ራሱ ፡ በሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ተተኪው ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ካፒቴኑ ፡ የመርከቡን ፡ የዕለት ፡ ሥራዎች ፡ ከመምራትና ፡ እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ትንንሽ ፡ የማደስ፡ ጉዳዮች ፡ ከማከናወን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም።ቢሆንም ፡ ለመርከቡ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ሠራተኞች ፡ ለመቅጠርም ፡ ቢሆን ፡ ለማሰናበት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(፬) ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ መኖር ፡ ወይም ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ወኪሉ ፡ የተተካ ፡ መሆኑን ፡ አስቀድመው ፡ ካላወቁ ፡ በቀር ፡ የነዚህ ፡ መኖር ፡ መከራከሪያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፺፰ ። የካፒቴኑ ፡ ኀላፊነት ።</u>

(፩) ካፒቴኑ ፡ ለሚያደርጋቸው ፡ ስሕተቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ እንዲጭን ፡ ለተረከባቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

(፪) የካፒቴኑ ፡ ኀላፊነት ፡ በሕግ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

<u>ቍ ፡ ፺፱ ። የካፒቴኑ ፡ ግዴታዎች ።</u>

መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ከጀመረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ባሕር ፡ ወደብ ፡ እስከሚደርስበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ካፒቴኑ ፡ ከመርከቡ ፡ ሳይለይ ፡ የተወሰኑትን ፡ ተግባሮች ፡ ይፈጽማል ።

<u>ቍ ፡ ፻ ። በመርከቡ ፡ አንዳድ ፡ እረገድ ፡ ካፒቴኑ ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ።</u>

ካፒቴኑ ፡ አንድ ፡ የመርከብ ፡ ነጂ ፡ እንዲኖረው ፡ የሚያስገድድ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ካፒቴኑ ፡ ለመርከቡ ፡ አካሄድ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፻፩ ። ስለ ፡ መርከቡ ፡ መንዳት ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ።</u>

በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ከመርከብ ፡ ነጂው ፡ ቸልተኛነት ፡ የተነሣ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ለደረሰው ፡ አደጋና ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆነው ፡ መርከቡ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፻፪ ። የመርከብ ፡ ሰነዶች ።</u>

መርከቡ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ፡ ካፒቴኑ ፡ የመርከቡን ፡ ሁኔታ ፤ የመርከበኞቹንና፡ የሠራተኞቹን ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የሚጓዙትን ፡ መንገደኞችና ፡ መርከቡ ፡ የሚጭነውን ፡ የዕቃ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስረዳ ፡ የመርከብ ፡ ሰነድ ፡ ሌሎችንም ፡ አስፈላጊ ፡ ሰነዶች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የማኖር ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፻፫ ። የመርከቡ ፡ የዕለት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብና ፡ የመርከቡ ፡ ሞተር ፡ መዝገብ ።

የመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ የታዘዙት ፡ የዕለት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገቦች ፡ እዲኖሩትና ፡ በተወሰነው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ እንዲጠበቁ ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፻፬ ። መርከቡ ፡ ከወደብ ፡ ሲደርስ ፡ በመዝገቦቹ ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

መርከቡ ፡ እመድረሻ ፡ ወደቡ ፡ ጣቢያ ፡ ወይም ፡ በሚያልፍበት ፡ ወደብ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ካፒቴኑ ፡ የመርከቡን ፡ የዕለት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብ ፡ በስፍራው ፡ ለሚገኘው ፡ የባሕር ፡ ጕዞ ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ የቆመው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ለሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ቆንሲል ፤ ቆንሲል ፡ የሌለበት ፡ አገር ፡ ሲሆን ፡ በክፍሉ ፡ ለሚገኙት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አቅርቦ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ማሳ ተም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፭ ። የባሕር ፡ ዴክላራሲዮን ።

የተወሰነ ፡ ልዩ ፡ ድንገተኛ ፡ ሁኔታ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካፒቴኑ ፡ የሚገባውን ፡ ዴክላራሲዮን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፮ ። የባሕር ፡ ዴክላራሲዮን ፡ ምርመራ ።

ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የተመደበው ፡ ባለሥልጣን ፡ ዴክለራሲዮን ፡ እንደ፡ተቀበለ ፡ የተሰጠውን ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፯ ። አስቸኳይ ፡ ነገር ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ካፒቴኑ ፡ ስለሚያደርገው ፡ የጭነቱን ፡ ዕቃ ፡ አሲዞ ፡ መበደር ፡ ወይም ፡ መሸጥ ።

(፩) በጕዞው ፡ ጊዜ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ አጋጣሚ ፡ ጕዳይ ፡ ያገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካፒቴኑ ፡ በስፍራው ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፤ ይህም ፡ ባይኖር ፡ በክፍሉ ፡ ያለውን ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ አስቸኳዩ ፡ ነገር ፡ የደረሰበት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ቆንሲል ፡ ይህም ፡ ባይኖር ፡ በስፍራው ፡ የሚገኘውን ፡ የክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ አስፈቅዶ ፤ መርከቡን ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ባልበቃ ፡ ጊዜ ፡ ጭነቱን ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፡ ገንዘብ ፡ ሊበደር ፡ ይችላል ።

(፪) ብድሩን ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ይህንኑ ፡ ከዚሁ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ፈቃድ ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ በታወቀው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የጫነውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፫) ይህን ፡ የፈጸሙት ፡ ሥራ፡አስኪያጁ ፡ ወይም ፡ ካፒቴኑ ፡ መርከቡ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጭነቱ ፡ በተራገፈበት ፡ ቦታ ፡ ይህን ፡ የተሸጠውን ፡ ዕቃ ፡ በዐይነቱና ፡ በተፈጥሮው ፡ የሚመስሉት ፡ ዕቃዎች ፡ በተሸጡበት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ የተሸጠ ፡ መሆኑን ፡ ለባህብቱ ፡ ማስረዳት ፡ አለባቸው ።

(፬) ዕቃ ፡ ጫኞቹ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጫኞቹ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ከከፈሉ ፡ ዕቃው ፡ በመያዣ ፡ እንዳይሰጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይሸጥ ፡

BACK



ለመቃወም ፡ ጭነቱም ፡ እንዳይራገፍ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፻፳ ። መርከቡ ፡ የባሕር ፡ ጕዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ካፒቴኑ ፡ ሊሸጠው ፡ የሚችልበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) መርከቡ ፡ ጕዞ ፡ ለመቀጠል ፡ አለመቻሉ ፡ በደንብ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ካፒቴኑ ፡ መርከቡን ፡ መሸጥ ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ካፒቴኑ ፡ ከባለ ፡ ሀብቱ ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይቀበል፡ መርከቡን ፡ የሸጠው ፡ እንደሆነ ፡ ባለሀብቱ ፡ ሽያጩን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) በጭራሽ ፡ መርከቡ ፡ ጕዞ ፡ ለመቀጠል ፡ አለመቻሉ ፡ የሚረጋገጠው ፡ የፍርድ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳን ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ በሌለበት ፡ ስፍራ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሲሆን ፡ በክፍሉ ፡ የሚገኙት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መርጠው ፡ ባዘዟቸው ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ በሰጡ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ባላቸው ፡ (ኤክስፔርቶች) ፡ በተዘጋጀ ፡ የምርመራ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ነው ።

(፫) ጕዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ በጭራሽ ፡ ካለመቻሉ ፡ የተነሣ ፡ የሚደረገው ፡ የመርከብ ፡ ሽያጭ ፡ የሚፈጸመው ፡ በሐራጅ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፳፩ ። ለጋራ ፡ ጥቅም ፡ በባሕር ፡ የሚጓዝ ፡ ካፒቴን ።**

በመርከቡ ፡ ላይ ፡ በተጫነው ፡ ዕቃ ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ የመርከብ ፡ ጕዞ ፡ የሚያደርግ ፡ ካፒቴን ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በተመደበው ፡ ጕዞ ፡ ለራሱ ፡ ሲል ፡ ሌላ ፡ የንግድ ፡ ጕዞ ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ።

ይህንንም ፡ ደንብ ፡ ተቃውሞ ፡ ቢገኝ ፡ ይህ ፡ አድራጎቱ ፡ ባስከተለው ፡ ጉዳት ፡ ከማራና ፡ ካሣ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከመክፈሉ ፡ በላይ ፡ የሚገባውን ፡ የትርፍ ፡ ክፍያ ፡ ድርሻውን ፡ የማግኘት ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

**ቍ ፡ ፻፳፪ ። የመርከቡ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ የሆነውን ፡ ካፒቴን ፡ ከሥራው ፡ ስለ፡ማሰናበት ፡**

ከሥራው ፡ የታገደው ፡ ካፒቴን ፡ የመርከቡ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመርከቡ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የሀብቱን ፡ ድርሻ ፡ ለመተውና ፡ ልኩም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የተመረጠ ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ (ኤክስፔርት) ፡ በሚወስነው ፡ መሠረት ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ድርሻው ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

በዚህ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ የድርሻ ፡ መልቀቅ ፡ መብቱ ፡ ሌሎቹ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ አሳቡን ፡ እንዲገልጽላቸው ፡ ከጠየቁት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ካለፈ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

በዚህ ፡ በድርሻ ፡ መልቀቅ ፡ መብቱ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሠርቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀሩት ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ ሊከፍሉት ፡ የሚገባቸውን ፡ የለቃቂውን ፡ ድርሻ ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ ግምቱን ፡ ከወሰነበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## የባሕር ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንበት ፡ ደንብ ።

### ቍ ፡ ፻፲፩ ። የመርከበኛ ፡ ትርጓሜ ።

በባሕር ፡ ጕዞ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ ለማገልገል ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ (ከካፒቴኑ ፡ ከነጂውና ፡ ከተመዘገቡት ፡ ረዳቶች ፡ በተቀር) ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መርከበኛ ፡ ይቈጠራል ።

### ቍ ፡ ፻፲፪ ። መርከበኛ ፡ የሚቀጠርበት ፡ ውል ።

ጠቅላላ ፡ ክብደታቸው ፡ ከአምስት ፡ ቶን ፡ በታች ፡ የሆኑትን ፡ መርከቦች ፡ በሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በአከራዩ ፡ ወይም ፡ በእንደራሴውና ፡ በመርከበኛው ፡ መካከል ፡ የሚደረገው ፡ የሠራተኛ ፡ መቅጠሪያ ፡ ውል ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ አጻጻፎች ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ለባሕር ፡ ጕዞ ፡ ሥራ ፡ አገልግሎት ፡ መቅጠሪያ ፡ በሆነው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ዝርዝር ፡ መጻፊያ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ይመዘገባል ። የውሉም ፡ ሁኔታና ፡ ስምምነት ፡ ለመርከበኛው ፡ ተነቦለት ፡ ውሉን ፡ መቀበሉን ፡ በዚሁ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ በሚያደርገው ፡ በጽሕፈት ፡ ወይም ፡ በጣት ፡ ፊርማው ፡ ያረጋግጣል።መርከቡም ፡ ለጕዞው ፡ ከመነሣቱ ፡ በፊት ፡ የባሕርን ፡ ጕዞ ፡ እንዲመረምሩ ፡ የታዘዙት ፡ የባሕር ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የተሳፈሩት ፡ መርከበኞች ፡ ሁሉ ፡ በውል ፡ የተቀጠሩ ፡ ለመሆናቸው ፡ የመርከበኞቹ ፡ ዝርዝር ፡ የተጻፈበትን ፡ መዝገብ ፡ ይመረምራሉ ።

### ቍ ፡ ፻፲፫ ፡ የመቀጠሪያው ፡ ውል ፡ አገላለጽ ።

የመቀጠሪያው ፡ ውል ፡ ማመልከት ፡ ያለበት ፡-

(ሀ) ውሉ ፡ የተደረገው ፡ ለተወሰነ ፡ ወይም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለጕዞ ፡ መሆኑን ፤

(ለ) የመርከበኛውን ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፤

(ሐ) አገልግሎት ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ የሚጀመርበትን ፡ ቀን ፤

(መ) በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ደመወዝ ፡ አከፋፈል ፡ የተደረገውን ፡ የስምምነት ፡ ዐይነት ፤

(ሠ) የተመደበለትን ፡ ደሞዝ ፡ ወይም ፡ የጥቅም ፡ አወሳሰን ፡ መሠረት ፤

(ረ) ውሉ ፡ የተደረገበትን ፡ ስፍራና ፡ ቀን ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፻፲፬ ። ከትርፉ ፡ ገቢ ፡ ወይም ፡ ከጭነቱ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ የሚከፈል ፡ የአገልግሎት፡ ዋጋ ።

(፩) የመርከበኛው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሚከፈለው፡ ከመርከቡ ፡ ከሚገኘው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ነው ፡

BACK



የሚል ፡ የመቅጠሪያ ፡ ውል ፡ የተጣራውን ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ካልተጣራው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ የሆኑትን ፡ ወጪዎች ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) የመርከቡ ፡ ጕዞ ፡ በመቋረጡ ፤ በመቀነሱ ፡ ወይም ፡ በመራዘሙ ፡ ወይም ፡ ትርፍ፡ በመታጣቱ ፡ ወይም ፡ ጭነቱ ፡ በመበላሸቱ ፡ የሚከፈለው ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ባልተጣራው ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

(፫) መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ከጀመረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ መርከበኛው ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ያወጣ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በኢንሹራንስ ፡ በሚገኙት ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘቦች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ አይጸናም ።

(፬) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ መንግሥት ፡ የሚሰጣቸው ፡ የርዳታና ፡ የጕርሻ ፡ ገንዘቦች ፡ መርከቡ ፡ ካፈራቸው ፡ ተከፋፋይ ፡ ከሆኑት ፡ ትርፎችና ፡ ጥቅሞች ፡ ጋራ ፡ አይታሰቡም ።

(፭) ለመርከበኞች ፡ የሚከፈለው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ከመርከቡ ፡ ጥቅም ፡ መርከቡ ፡ ከሚያገኘው ፡ ፍሬ ፡ ወይም ፡ ከጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዐቅም፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ ባለመቻሉ፡ መንገዱን ላቋረጠበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለመድረሻ ፡ የተወሰነለትን ፡ ጊዜ ፡ ላሳጠረበት ፡ ወይም ፡ ላስረዘመበት ፡ ጕዳይ ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ለመርከበኞቹ ፡ ኪሣራ ፡ አይታሰብላቸውም ።

**ቍ ፡ ፪፻፭ ። በየጕዞው ፡ የሚታሰብ ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ።**

ለመርከበኞች ፡ የሚከፈላቸው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ በጕዞ ፡ ሒሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ጕዞውን ፡ ማሳጠር ፡ ሊከፈላቸው ፡ የሚገባውን ፡ የደመወዝ ፡ ሒሳብ ፡ አያስቀንስባቸውም ።

**ቍ ፡ ፪፻፮ ። የመርከበኛው ፡ ግዴታ ።**

መርከበኛው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ እንዲሳፈር ፡ ካፒቴኑ ፡ በሚያደርግለት ፡ የመጀመሪያ ፡ ጥሪ ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ አለበት ። የመርከቡንም ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ሁሉ ፡ በየብስም ፡ ሆነ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ለቀጥተኛ ፡ የበላይ ፡ አለቆች ፡ እንዲታዘዝ ፡ ይገደዳል ።

**ቍ ፡ ፪፻፯ ። በራሱ ፡ ሒሳብ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ እንዳይጭን ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የመርከቡ፡ባለሀብት፡ካልፈቀደላቸው፡በቀር፡ካፒቴኑና ፡ መርከበኞቹ ፡ ለግል ፡ ጥቅማቸው ፡ ማንኛውንም ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ለመጫን ፡ አይችሉም ።

ይህንንም ፡ ደንብ ፡ አፍርሰው ፡ ሲገኙ ፡ የጫኑት ፡ ዕቃ ፡ ስላደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፍሉ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ ለጫኑት ፡ ዕቃ ፡ ዕቃውን ፡ በጫኑበት ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፡ ለጭነት ፡ የሚከፈለውን ፡ ከፍተኛ ፡

ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ።

(፪) ያለ ፡ አገባብ ፡ የተጫኑት ፡ ዕቃዎች ፡ በመርከቡ ፡ ጸጥታ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያ ደርሱ ፡ ወይም ፡ ወጪና ፡ መቀጫ ፡ የሚያስከትሉ ፡ ነገሮች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካፒቴኑ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይጠይቅ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እንዲጣሉ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፲፰ ። ከደመወዝ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።**

ለመርከበኞች ፡ ከደመወዝ ፡ አስቀድሞ ፡ የተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ጕዞው ፡ ከመ ጀመሩ ፡ በፊት ፡ ተከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመርከብ ፡ ሠራተኞች ፡ ዝርዝር ፡ መዝ ገብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ የተከፈለው ፡ መርከቡ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በመርከቡ ፡ የዕለት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ፤ መርከበኛውም ፡ ገንዘቡን ፡ ሲቀበል ፡ በጽሕፈት ፡ ወይም ፡ በጣቱ ፡ መፈረም ፡ አለበት ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ሥርዐት ፡ ካልተፈጸመ ፡ በቀር ፡ ደመወዝ ፡ በቅድሚያ ፡ መስጠት ፡ አይችልም ። ከደመወዝ ፡ ላይ ፡ በቅድሚያ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ጥያ ቄው ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ተከፋዩ ፡ ከሆነው ፡ ከጠቅላላው ፡ ደመወዝ ፡ ከአምስት ፡ አንድ ፡ የበለጠ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፻፲፱ ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አበል ።**

ለቤተ ፡ ሰብ ፡ አበል ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጠው ፤ ለመርከበኛው ፡ ሚስት ፡ ልጆችና ፡ ወላጆች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፳ ። አስቀድሞ ፡ ከደመወዝ ፡ ላይ ፡ የተወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መመለስ ።**

(፩) ለቤተ ፡ ሰብ ፡ አበል ፡ እንዲከፈሉ ፡ ያልተደረጉ ፡ ተቀዳሚ ፡ የደመወዝ ፡ ሒሳቦች ፡ ከሒሳብ ፡ ላይ ፡ የሚከፈሉ ፡ ገንዘቦችና ፡ የመቀጠሪያ ፡ ዋጋዎች ፡ በመርከበኛው ፡ በኩል ፡ በተደረገው ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ የመቀጠሪያው ፡ ውል ፡ ካልፈረሰ ፡ በቀር ፡ ለዚሁም ፡ በመርከበኛው ፡ ላይ፡የሚወሰንበት ፡ የሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ጕድለት ፡ መቀጫና ፡ ላደረገው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ የሚከፈልበት ፡ ደንብ ፡ መጽናት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ለመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ተመላሽ ፡ አይሆኑም ።

(፪) ምንም ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፤ ለቤተ ፡ ሰብ ፡ አበል፡ ከደመወዝ ፡ አስ ቀድሞ ፡ የተወሰደ ፡ ገንዘብ ፡ መቼውንም ፡ ተመላሽ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፻፳፩ ። ደመወዝን ፡ ስለ ፡ መያዝ ።**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶችና ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ በተደነገጉት፡ ውሳ ኔዎች ፡ መጠን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለመርከበኛ ፡ የሚከፈለው ፡ ደመወዝና ፡ ትርፍ ፡ የማይያዝና ፡ የማይተላለፍ ፡ ነው ።

(፩) ከደመወዙ ፡ ከአራት ፡ አንዱን ፡ ለመያዝ ፡ የሚቻለው ፡—

(ሀ) ለመንግሥት ፡ በሚከፈል ፡ ዕዳ ፡ ወይም ፡ ለመጠባበቂያ ፡ ተቀማጭ ፡ ገን ዘብ ፡ ለሚከፈል ፡ ሒሳብ ፤

BACK



(ለ) ለተሰጠው ፡ ምንቅ ፤ ልብስ ፤ ወይም ፡ ለመኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ዕዳ ፤
(ሐ) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባደረገው ፡ ጕዞ ፡ ከሚከፈለው ፡ ደመወዝ ፡ በላይ ፡ አብ ልጦ ፡ ያላገባብ ፡ ለወሰደው ፤ ሊከፈለው ፡ የማይገባው ፡ ተቀዳሚ ፡ የደመወዝ ፡ ዕዳ ፡ ወይም ፡ ለመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ለሚከፈል ፡ ኪራይ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለዕዳነቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ ተፈርዶበት ፡ የፍ ርዱ ፡ ማስፈጸም ፡ ሥርዐት ፡ በተጀመረበት ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ ከደመወዙ ፡ አንድ ፡ አራተኛው ፡ ሊያዝ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፪ ። ከመቀጠር ፡ በፊት ፡ የሚደረግ ፡ የሐኪም ፡ ምርመራ ።**

(፩) በወደቡ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተመርጦ ፡ በተመደበ ፡ በአንዱ ፡ ሐኪም ፡ ፊት ፡ ደን በኛ ፡ ምርመራ ፡ ተደርጎለት ፡ ለሥራ ፡ ተስማሚ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ መርከበኛ ፡ ሊቀጠር ፡ አይቻልም ።

ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ የያዛቸውን ፡ መርከበኞች ፡ መቅጠር ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተገለጸው ፡ ሥርዐት ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ የመርከቡ ፡ ካፒቴን ፡ በመርከብ ፡ ሠራተኞች ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) የዚህን ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ያልፈጸመ ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፰፻፲፬ ፡ (መ) ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፫።በመርከብ ፡ አገልግሎት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ መታመም ፡ ወይም ፡ስለ፡መቍሰል።**

(፩) በመርከብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የቈሰሉ ፡ ወይም ፡ የታመሙ ፡ መርከበኞች ፡ የሚታከሙት ፡ በመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ሒሳብ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ሕመሙ ፡ ወይም ፡ የቍስሉ ፡ ጕዳይ ፡ በመርከበኛው ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ባለመፈጸም ፡ ወይም ፡ ይቅርታ ፡ በማይ ደረግለት ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በስካር ፡ ወይም ፡ ሕመሙ ፡ ከበሽተኛው ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ የተወለደ ፡ እንደ ፡ እብደት ፡ እንደ ፡ አእምሮ ፡ መናወጽ ፡ ወይም፡ ሥረ ፡ መሠረቱ ፡በዝሙት ፡ የመጣ ፡ የአካል ፡ ውስጥ ፡ በሽታ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሽተኛውን ፡ ለማሳከም ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ወጪ ዎች ፡ ለቈሰለው ፡ ወይም ፡ ለታመመው ፡ መርከበኛ ፡ ከሚደርሰው ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ የሚቀነሱ ፡ ናቸው ።

(፪) ሕመሙ ፡ ወይም ፡ ቍስሉ ፡ ለመታከምና ፡ ለመዳን ፡ የማይችል ፡ ጠባይ ፡ ያሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሕክምና ፡ ሒሳብ ፡ መከፈሉ ፡ ይቋረጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፬ ። ለታመመው ፡ ወይም ፡ ለቈሰለው ፡ መርከበኛ ፡ የሚከፈል ፡ ደመወዝ ፡ ወይም ፡ ዳረጎት ።**

(፩) በመርከቡ ፡ ሥራ ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ የታመመ ፡ ወይም ፡ የቈ

BACK



ሰለ ፡ መርከበኛ ፡ እመርከቡ ፡ ላይ ፡ እስካለበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ደመወዙን ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በየብስ ፡ ላይ ፡ ከወረደ ፡ በኋላ ፤ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ የአራት ፡ ወር ፡ ደመወዙን ፡ እንደ ፡ ዳረጎት ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ። በየብስ ፡ የወረደው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአራት ፡ ወር ፡ ደመወዝ ፡ መክፈያ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቆንሲል ፡ እጅ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

(፫) ደመወዝ ፡ ወይም ፡ ድርጎ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የማይተላለፍ ፡ የግል ፡ ነው ። ተጠቃሚው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፤ በዳነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ አራት ፡ ወር ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ይቋረጣል ።

(፬) ሕመሙ ፡ ወይም ፡ መቍሰሉ ፡ የደረሰበት ፡ በመርከበኛው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ማጓደል ፡ ወይም ፡ በስካር ፡ ወይም ፡ የበሽታው ፡ ሥረ ፡ መሠረት ፡ ከሰውነቱ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ የተዋሐደ ፡ ወይም ፡ በዝሙት ፡ የመጣ ፡ በሽታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከበኛው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ እስካለበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የመታከምና ፡ የመመገብ ፡ መብት ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ደሞዙን ፡ ወይም ፡ ድርጎ ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፭) በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ መርከበኛው ፡ በመርከብ ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ በበሽታ ፡ ወይም ፡ በቍስል ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመቃብሩ ፡ ወጪ ፡ የሚሆነውን ፡ ሒሳብ ፡ የሚከፍለው ፡ መርከቡ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፭ ። ወደ ፡ አገሩ ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

(፩) ከየብስ ፡ የወረዱትን ፡ መርከበኞች ፡ ሁሉ ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ መመለስ ፡ አለበት ። በሁለቱ ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነት ፡ የመርከበኛው ፡ መቅጠሪያ ፡ ውል ፡ እንዲቀር ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከበኛው ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ የሚመለስበትን ፡ ኪሣራ ፡ የሚችለው ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ወገን ፡ ነው ።

(፪) ወደ ፡ አገሩ ፡ የመመለስ ፡ መብት ፡ ለመጓዣ ፡ ከሚከፈለውም ፡ ሒሳብ ፡ በቀር ፡ የምግብንና ፡ የማደሪያን ፡ ሒሳብ ፡ ይጨምራል ።

## አንቀጽ ፡ ፬ ።

## በመርከብ ፡ ለመገልገል ፡ ስለሚደረጉ ፡ ውሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ባዶ ፡ መርከብ ፡ ስለ ፡ ማከራየት ።

ቍ ፡ ፫፻፮ ። ትርጓሜ ።

(፩) ባዶ ፡ መርከብ ፡ ማከራየት ፡ ማለት ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በመርከቡ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ኪራይ ፡ በመቀበል ፡ የሚገባበት ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) አፈጻጸሙም ፡ የሚመራው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ልዩ፡ድን ጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፺፯ ። አሳልፎ ፡ ማከራየት ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

አከራዩ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በቀር ፡ ተከራዩ ፡ አሳልፎ ፡ መርከቡን ፡ ለሌላ ፡ ማከራ የት ፡ ወይም ፡ ከውሉ ፡ የሚገኙትን ፡ መብቶች ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፺፰ ። የአከራዩ ፡ ግዴታ ።

አከራዩ ፡ መርከቡን ፡ ከተጨማሪዎች ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ ለመጓዝ ፡ በሚቻልበት ፡ መልካም ፡ ሁኔታ ፡ አድርጎና ፡ ለጕዞውም ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ፡ማስ ረከብ ፡ አለበት ።እንዲሁም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ በውሉ፡ለተመ ለከተው ፡ መርከቡ ፡ ሲያገለግል ፡ ለደረሰበት ፡ ማለት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የማ ደስ ፡ ሥራዎች ፡ አከራዩ ፡ ማስደረግ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። የአከራዩ ፡ ኀላፊነት ።

መሰናከሉን ፡ ያደረሰው ፡ ጕድለት ፡ የተደበቀ ፡ ጕድለትና ፡ ጥንቁቅ ፡ የሆነ ፡ አከ ራይ ፡ ሊገነዘበው ፡ ወይም ፡ ሊከለክለው ፡ በማይችለው ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ካላ ስረዳ ፡ በቀር ፡ መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ለማድረግ ፡ ባለመቻሉ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጕድ ለት ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆነው ፡ አከራዩ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻ ። የተከራዩ ፡ ግዴታዎች ።

ተከራዩ ፡ በመርከቡ ፡ አገልግሎት ፡ ሊጠቀም ፡ የሚገባው ፡ ስለ ፡ ባሕር ፡ ጕዞ ፡ ችሎታ ፡ በተሰጠው ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ የቴክኒክ ፡ ጠባዩ ፡ መሠረትና ፡ በውሉ ፡ በተመለከተው ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፩ ። ውሉ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) አከራዩ ፡ በግልጽ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ የውሉ ፡ ዘመን ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ መርከቡ ፡ በተከራዩ ፡ እጅ ፡ ቢገኝም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ የውሉን ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ተራዘመ ፡ አያስቈጥረውም ።

(፪) የኪራዩ ፡ ዘመን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ መርከቡ ፡ ለአከራዩ ፡ ያልተመለሰው ፡ በተከ ራዩ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ ላሳለ ፈው ፡ ጊዜ፡ ተከራዩ፡ ለአከራዩ ፡ በውሉ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ኪራይ ፡ በእጠ ፌታ ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፫፻፪ ። ውሉን ፡ የሚመለከቱ ፡ መብቶች ፡ በይርጋ ፡ የሚታገዱበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ባዶ ፡ መርከብን ፡ ከማከራየት ፡ ውል ፡ የሚገኙት ፡ መብቶች ፡ በይርጋ ፡ የሚታ ገዱት ፡ ለውሉ ፡ መቈያ ፡ የተወሰነው ፡ ዘመን ፡ ካለቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡

BACK



ወይም ፡ በላይኛው ፡ ቍጥር ፡ የተገለጸው ፡ ጕዳይ ፡ ሲሆን ፡ መርከቡ ፡ ለአከራዩ ፡ ከተመለሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) መርከቡ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ በሚቈጠርበት ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ የጊዜው ፡ ውሳኔ ፡ መቈጠሩን ፡ የሚጀምረው ፡ መርከቡ ፡ ከመርከቡ ፡ መመዝገቢያ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ከተሰረዘበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ጭነት ፡ ኪራይ ፡ ውል ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

### ቍ ፡ ፪፻፫ ። ትርጓሜ ።

(፩) የመጫን ፡ ውል ፡ ሲባል ፡ አከራዩ ፡ የመጫን ፡ ኪራይ ፡ ከተከራዩ ፡ ተቀብሎ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ መርከብ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ጕዞዎች ፡ (በጕዞ ፡ የተወሰነ ፡ የመጫን ፡ ኪራይ) ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የተከራዩ ፡ (ዕቃ ፡ አስጫኙ) ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጕዞ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ልማዳዊ ፡ ደንብ ፡ (ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የመጫን ፡ ኪራይ ) ፡ እንዲፈጽም ፡ አከራዩ ፡ ለተከራዩ ፡ የሚገባለት ፡ ግዴታ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) የመጫን ፡ ውል ፡ ማለት ፡ በማመላለሻ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ የሙብት ፡ ሰነድ ፡ የተጫነውን ፡ ዕቃ ፡ ስለሚመለከት ፡ ነገር ፡ የሚገለገሉበትና ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በክፍል ፡ ፫ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሚሠራበት ፡ ስምምነት ፡ ማለት ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፪፻፬ ። በውሉ ፡ የሚገለጸው ፡ አጻጻፍ ።

የመጫን ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መደረግ ፡ ይገባዋል ፤ ይህ ፡ የወገኖች ፡ ስምምነት ፡ (ቻርተር ፡ ፓርቲ) ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ቃሎች ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

ሀ/ የመርከቡን ፡ ስም ፤ ክብደቱንና ፡ ዜግነቱን ፤

ለ/ የካፒቴኑን ፡ ስም ፤

ሐ/ የአከራዩንና ፡ የተከራዩን ፡ ስምና ፡ የመኖሪያውን ፡ ስፍራ ፤ የሚሠራበት ፡ ሥልጣን ፤

መ/ የጭነቱ ፡ ዐይነትና ፡ ጭነቱን ፡ ለመለየት ፡ በቂ ፡ የሆኑትን ፡ መግለጫዎች ፤

ሠ/ ለጭነቱ ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ እንደሚታሰብ ፤
ረ/ ውሉ ፡ የሚጸናበትን ፡ ዘመን ፤ ወይም ፡ ስንት ፡ ጉዞ ፡ እንደሚደረግ ፤

ቍ ፡ ፪፻፷ ። ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ ስለ ፡ ማከራየት ።

(፩) ለጭነት ፡ ተከራይ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ያለ ፡ አከራዩ ፡ ፈቃድ ፡ ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ ለማከራየት ፡ ወይም ፡ ከጭነቱ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ የተገኙትን ፡ መብቶች ፡ በሙሉ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

(፪) የማስጫኑን ፡ ኪራይ ፡ ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ወይም ፡ ከውሉ ፡ የሚገኙትን ፡ መብቶች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለሌላ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዋናው ፡ ተከራዩ ፡ በመጫን ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ለገባባቸው ፡ ግዴታዎች ፡ ለአከራዩ ፡ አላፊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቈያል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። ለጭነት ፡ በተከራየው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ አከራዩ ፡ ስለሚጭናቸው ፡ ዕቃዎች ።

አከራዩ ፡ ተከራዩን ፡ ካላስፈቀደ ፡ ባከራየው ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ የመርከብ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ዕቃ ፡ ለመጫን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። መርከቡን ፡ በተከራዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

አከራዩ፡ለጭነት፡ያከራየውን፡መርከብ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ ለተከራዩ ፡ ማቅረብና ፡ በእሱ ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ እንዲሆን ፡ ማስረከብ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፷፫ ፡ የመርከብ ፡ አከራዩ ፡ ግዴታ ።

መርከቡ ፡ ለጕዞው ፡ ከመነሣቱ ፡ አስቀድሞና ፡ ጕዞ ፡ በሚጀምርበት ፡ ጊዜ ፡ አከራዩ ፡ ደንበኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ ያለበት ።

(ሀ) መርከቡ ፡ የባሕር ፡ ጕዞውን ፡ ለማድረግ ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲዘጋጅ ፤
(ለ) መርከቡን ፡ በሚገባ ፡ መሣሪያውን ፡ ማሟላት ፤ የመለወጫ ፡ ዕቃዎችና ፡ ሥንቆችን ፡ ማዘጋጀት ፤
(ሐ) የውሃ ፡ መያዣውን ፤ የማቀዝቀዣ ፡ ክፍሉንና ፡ የበረዶ ፡ ሣጥኑን ፡ እንዲሁም ፡ ማንኛውንም ፡ የመርከብ ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎቹ ፡ የሚጫኑበት ፡ ቦታና ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ተጠብቀው ፡ የሚቀመጡበትንና ፡ የሚጓዙበትን ፡ ክፍል ፡ በሚገባ ፡ ለማደራጀት ፡ ለማዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፬ ። አከራዩ ፡ ከአላፊነት ፡ የሚድንበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) መጥፋቱ ፡ ወይም ፡ የጉዳቱ ፡ አደጋ ፡ የደረሰው ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፷፫ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ ባለመፈጸም ፡ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጥንቁቅ ፡ የሆነ ፡ አከራይ ፡ ሊያገኘው፥ በማይችለው ፡ በተደበቀ ፡ ጕድለት ፡ ከሆነ ፤ አከራዩ ፡ መር

BACK



ከቡ ፡ ለጕዞው ፡ አፈጻጸም ፡ ሙሉ ፡ ድርጅት ፡ ለማግኘት ፡ ባለመቻሉ ፡ የተ ነሣ ፡ ለደረሱት ፡ ኪሣራዎችና ፡ ጉዳቶች ፡ አከራዩ ፡ ኀላፊ ፡ አይደለም ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳት ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ አከራዩ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ከአላፊነት ፡ ውጭ ፡ ልሁን ፡ ብሎ ፡ የሚጠይቀው ፡ ወገን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፵ ። የተከራዩ ፡ አላፊነት ።

ተከራዩ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ በእንደራሴዎቹ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ከጫነው ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ ከተደበቀ ፡ ጕድለት ፡ የተነሣ ፡ በመርከቡ ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ጭነት ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፵፩ ። የመድረሻ ፡ ወደብ ።

(፩) መርከቡ ፡ የጫነውን ፡ ዕቃ ፡ ለማስረከብ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ተመለከ ተው ፡ ወደብ ፡ መሄድ ፡ አለበት ። ወደ ፡ ተመደበለት ፡ ወደብ ፡ ለመድረስ ፡ ያል ቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአቅራቢያው ፡ ወደሚገኘው ፡ ወደብ ፡ ሄዶ ፡ አከራዩ ፡ መር ከቡን ፡ ከቆመበት ፡ ለዕቃ ፡ ማድረሻ ፡ እስከ ፡ ተወሰነበት ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ የማ ድረሻውን ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ።

(፪) መርከቡ ፡ እተወሰነለት ፡ ወደብ ፡ ለመድረስ ፡ ያልቻለው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ ወጪ ፡ የሚችለው ፡ ተከራዩ ፡ ነው ።

(፫) ተከራዩ ፡ መርከቡ ፡ የሚደርስበትን ፡ ወደብ ፡ ወደፊት ፡ ለማስታወቅ ፡ በስም ምነቱ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በሚያመለክተ ውም ፡ ወደብ ፡ መርከቡ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ለመግባት ፡ የማይችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሚደርስበት ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፵፪ ። በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ መርከቡን ፡ በተከራዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ስላለማድረግ ።

(፩) ተከራዩ ፡ ለመርከቡ ፡ መረከብ ፡ ጕዳይ ፡ በተደረገው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ በተወሰነው ፡ ስፍራ ፡ ጊዜ ፡ አከራዩ ፡ መርከቡን ፡ ሳይረከበው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ላንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከሰጠ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተከራዩ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በመ ርከቡ ፡ ላይ ፡ መጫን ፡ ያልጀመረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አከራዩ ፡ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

(፫) የመጫኛና ፡ የማራገፊያው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ የመጫኛው ፡ ጊዜ ፡ እንዳለፈ ፡ ይቈ ጠራል ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፫ ። ለተከራዩ ፡ የሚገባው ፡ ካሣ ።

የጊዜው ፡ መዘግየት ፡ ጕዳይ ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ አለመሆኑን ፡ አከራዩ ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፪ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ለተመለከተው ፡ ጕድለት ፡ ተከራዩ ፡ ምንም ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሳይገደድ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

ቍ ፡ ፪፻፬ ። የጭነት ፡ ውል ፡ የሚሰረዝበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ አፈጻጸሙን ፡ የሚከለክል ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ለሌላው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ሳይገደድ ፡ የጭነቱ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ኀይል ፡ የደረሰው ፡ መርከቡ ፡ ለጕዞው ፡ የተዘጋጀ ፡ ሆኖ ፡ ግን ፤ ጕዞውን ፡ ሳይጀምር ፡ እንደሆነ ፤ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ይደረግና ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ ኪሣራም ፡ ይከፍላል ።

(፫) ይህ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ኀይል ፡ የመርከቡን ፡ ጕዞ ፡ የሚያግደው ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ሳይጨመር ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፈል ፡ ውሉ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይቈያል ።

በሆንም ፡ የጊዜው ፡ መዘግየት ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ ለመፈጸም ፡ የገቡበትን ፡ የንግድ ፡ ግዴታ ፡ የሚያፈርስ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፭ ። የመርከቡ ፡ መሸጥ ።

(፩) መርከቡን ፡ የገዛው ፡ ሰው ፤ ይህ ፡ መርከብ ፡ ከመሸጡ ፡ በፊት ፡ ሻጩ ፡ መርከቡን ፡ ለጭነት ፡ ያከራየው ፡ መሆኑን ፡ ካወቀ ፤ የመርከቡ ፡ መሸጥ ፡ የጭነቱን ፡ ውል ፡ መፍረስ ፡ አያስከትልም ።

(፪) ሻጪው ፡ የመርከቡን ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ መርከብ ፡ ለጭነት ፡ ያከራየው ፡ መሆኑን ፡ ለገዢው ፡ ካስታወቀ ፤ ገዢው ፡ የገዛው ፡ መርከብ ፡ ለጭነት ፡ የተከራየ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቆ ፡ እንደ ፡ ተቀበለው ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፪፻፮ ። ስለ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ።

(፩) ከጭነት ፡ ውል ፡ የመነጩ ፡ መብቶች ፡ በይርጋ ፡ የሚታገዱት ፡ የተጫነው ፡ ዕቃ ፡ ከተረከበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ በሙሉ ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕቃውን ፡ ማስረከብ ፡ ከነበረበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ከ፩ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ከተመለከተው ፡ ውጭ ፡ ለሆነው ፡ አጋ ጣሚ ፡ ጕዳይ ፡ የይርጋው ፡ ውሳኔ ፡ የሚታሰበው ፤

BACK



(ሀ) የጭነቱ ፡ ኪራይ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ካለቀበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፯ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ጕዞው ፡ ተራዝሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጨረሻው ፡ ጕዞ ፡ ካለቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፤

(ለ) የጭነቱ ፡ ውል ፡ የተደረገው ፡ በጕዞ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ጕዞ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፤

(ሐ) ብዙ ፡ ጕዞ ፡ የሚደረግ ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ ጕዞ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፫) ጕዞው ፡ ሳይጀመር ፡ ወይም ፡ ሳይፈጸም ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ይርጋው ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ መታሰብ ፡ የሚጀምረው ፡ የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ ወይም ፡ የጕዞውን ፡ መቀጠል ፡ ያሰናከለው ፡ ነገር ፡ ካጋጠመበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። መርከቡ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ የሚያስቈጥር ፡ ጉዳይ ፡ ያጋጠመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጊዜው ፡ መታሰቡን ፡ የሚጀምረው ፡ መርከቡ ፡ ከመርከብ ፡ መመዝገቢያ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ ከተሰረዘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ይሆናል ።

(፬) ሊከፈል ፡ የማይገባው ፡ ሒሳብ ፡ በመከፈሉ ፡ ምክንያት ፡ እንዲመለስ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ይርጋው ፡ መታሰቡን ፡ የሚጀምረው ፡ ገንዘቡ ፡ ከተከፈለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ደግሞ ፡ ዋናው ፡ ክስ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሊታሰብ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፯ ። በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሊከፈል ፡ ስለሚገባው ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ።**

የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ሊከፈል ፡ ይገባል ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ ለተቀባዩ ፡ ላልደረሱ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችና ፡ ወይም ፡ ሊደርሱበት ፡ እተመደበው ፡ ወደብ ፡ ደርሰው ፡ በተቀባዩ ፡ እጅ ፡ ላልገቡ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ አይከፍልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፰ ። የጭነት ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ።**

የጭነት ፡ ዋጋ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባው ፡ —

(፩) የጭነቱ ፡ ማስረከብ ፡ ጉዳይ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ በተከራዩ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(፪) የንግድ ፡ ዕቃዎቹ ፡ በራሳቸው ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ተበላሽተው ፡ የጠፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(፫) አደገኛ ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ የሚጎዱ ፡ ወይም ፡ የተከለከሉ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ በተጫኑ ፡ ጊዜ ፡ ዐይነታቸውና ፡ ጠባያቸው ፡ ለአከራዩ ፡ ሳይ ገለጽለት ፡ ቀርቶ ፡ እንዲጣሉ ፡ ወይም ፡ እንዲጠፉ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው።

ቍ ፡ ፻፺፱ ። የሚበላሹ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ።

(፩) የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በራሳቸው ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባይ ፡ የሚበላሹ ፡ በመሆናቸው ፡ በጕዞው ፡ ላይ ፡ ተበላሽተው ፡ ቢጠፉም ፡ እንኳ ፡ የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ በአመላላሹ ፡ (ጫኙ) ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ተጭነው ፡ በሚጓዙበት ፡ ጊዜ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ለሞቱ፡ ከብቶች ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻ ። ካፒቴኑ ፡ ከጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ በተቀዳሚነት ፡ የወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ መልሶ ፡ የሚከፍልበት ፡ ሁኔታ ።

የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ ሊከፈል ፡ የማይገባው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከዚሁ ፡ ከጭነት ፡ ዋጋ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ በተቀዳሚነት ፡ ለካፒቴኑ ፡ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ካፒቴኑ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፩ ። በጕዞ ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ መርከብ ።

በአከራዩ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ አቋርጦ ፡ ለጊዜው ፡ የቆመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስምምነቱ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ። ይህም ፡ ምክንያት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈልን ፡ ወይም ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ መጨመርን ፡ አያስከትልም ።

ቍ ፡ ፪፻፪ ። ለመድረሻ ፡ ከተመደበላቸው ፡ ቦታ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ለተሰጡ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የሚከፈል ፡ የጭነት ፡ ሒሳብ ።

ለመድረሻ ፡ ከተወሰነላቸው ፡ ስፍራ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ተከራዩ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ለመረከብ ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሙሉውን ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፫ ። በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዕቃዎች ፡ በፍጹም ፡ አሟልቶ ፡ ስላለመጫን ።

በስምምነት ፡ ላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በፍጹም ፡ አሟልቶ ፡ ያልጫነ ፡ ተከራይ ፡ ሙሉውን ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ቢሆንም ፡ ለመርከቡ ፡ ወጪ ፡ መሆን ፡ ይገባው ፡ ከነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ስላተረፈ ፡

የሚታሰብለት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ እሱ ፡ ሊያቀርብ ፡ በሚገባውና ፡ በጐደለው ፡ ጭነት ፡ ምትክ ፡ ለተጫኑት ፡ ዕቃዎች ፡ የተከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ሦስቱ ፡ ሩብ ፡ ከዕዳው ፡ ላይ ፡ ይቀነስለታል ።

**ቍ ፡ ፻፶፬ ። የተጫኑትን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ባለሀብትነት ፡ መብት ፡ በመልቀቅ ፡ የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ አልከፍልም ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በጕዞው ፡ ላይ ፡ ባለዋጋነታቸውን ፡ ወይም ፡ ብዛታቸውን ፡ ቢቀንሱ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ጕዞ ፡ ላይ ፡ ቢበላሹ ፡ እንኳ ፡ ተከራዩ ፡ የዕቃዎቹን ፡ ባለሀብትነት ፡ በመልቀቅ ፡ የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ ከመክፈል ፡ ነጻ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፻፶፭ ። የአከራዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ።**

(፩) የተጫኑትን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ተቀባዩ ፡ ከተረከበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ እጅ ፡ ካልተላለፉ ፡ በቀር ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ እስኪከፈለው ፡ አከራዩ ፡ የተቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ይህ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ በቍጥር ፡ ፺፯ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር (፪) ፪፻፺፱ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) እና ፡ ፪፻፹፫ ፡ ከተመለከቱት ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ ቀጥሎ ፡ ተቀዳሚነት ፡ ይኖረዋል ።

**ቍ ፡ ፻፶፮ ። አከራዩ ፡ ጭነቱን ፡ ለመያዝ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈለው ፡ መሆኑን ፡ በማረጋገጥ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የሚገመት ፡ ዋስትና ፡ ማረጋገጫ ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ የንግዱ ፡ ዕቃ ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ አከራዩ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ለመድረሻ ፡ እየተመደበላቸው ፡ ወደብ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ ይዞ ፡ ለማቈየት ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ ለመክፈል ፡ እስከሚበቃው ፡ ተመዛዛኝ ፡ ገንዘብ ፡ ድረስ ፡ የንግዱ ፡ ዕቃ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፶፯ ። ዐይነታቸው ፡ ፍጹም ፡ አንድ ፡ ከሆኑ ፡ ከሌሎች ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ጋራ ፡ የተቀላቀሉ ፡ ዕቃዎች ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አጠባበቅ ።**

የጭነትና ፡ የተጨማሪ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈል ፡ ለማድረግ ፡ የሚኖረው ፡ ዋስትና ፡ አጠባበቅ ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ የሚፈለግባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ዐይነታቸው ፡ አንድ ፡ ከሆነ ፡ ከሌላ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ጋራ ፡ ተደባልቀው ፡ ቢገኙም ፡ እንኳ ፡ እንዳሉ ፡ ይቈያሉ ።

BACK



## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መጫኛና ፡ ማራገፊያ ፡ ጊዜና ፡ ስለተጨማሪ ፡ ጊዜ ።

**ቍ ፡ ፻፶፰ ። የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ (ሌይ ፡ ዴይስ) ፡**

(፩) በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ለመጫንና ፡ ለማራገፍ ፡ የተፈቀዱት ፡ ቀኖች ፡ የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ ( ሌይ ፡ ዴይስ ) ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ።

(፪) ይህም ፡ ጊዜ ፡ የሚወሰነው ፡ በስምምነት ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ ያልተደረገ ፡ ሲሆን ፡ በወደቡ ፡ ባለው ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፶፱ ። ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ( ዲመረጅ ) ።**

ለመጫኛውና ፡ ለማራገፊያው ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ የተሠራበት ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ( ዲመረጅ ) ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ይህም ፡ ጊዜ ፡ ለመጫኛና ፡ ለማራገፊያ ፡ ( ሌይ ፡ ዴይስ ) ፡ ከሚወስደው ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በተከራዩ ፡ ላይ ፡ የሚታሰብ ፡ ኪሣራ ፡ ከተከራይ ፡ ላይ ፡ አከራዩ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

የዚህ ፡ የካሣ ፡ ልክ ፡ የሚወሰነው ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ ያልተደረገ ፡ ሲሆን ፡ በወደቦች ፡ በሚሠራበት ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፷ ። ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ።**

የተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሚቀጥለው ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ( ዲቴንሽን ) ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በቍጥር ፡ ፻፶፱ ፡ የተመደበው ፡ ካሣ ፡ ግማሹ ፡ ይጨመራል ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተከራዩ ፡ ጥፋት ፡ ለሚደርሰው ፡ ልዩ ፡ ጉዳት ፡ ተከራዩ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ።

**ቍ ፡ ፻፷፩ ። የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ (ሌይ ፡ ዴይስ) ፡ አቈጣጠር ።**

መርከብ ፡ በመጫንና ፡ በማራገፍ ፡ የሚያልፈው ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ በዕለትና ፡ በሰዓት ፡ ሒሳብ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፷፪ ። የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ የሚጀመርበት ።**

(፩) ለመጫን ፡ ወይም ፡ ለማራገፍ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ካፒቴኑ ፡ መርከቡ ፡ ሊጫን ፡ ወይም ፡ ሊራገፍ ፡ ተዘጋጅቷል ፡ ብሎ ፡ ካስታወቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፪) የሚታሰበውም ፡ ካፒቴኑ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ ሥራው ፡ ከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፷፫ ። ለማራገፊያና ፡ ለመጫኛ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ የካፒቴኑ ፡ መብት ።**

ለመጫኛና ፡ ለማራገፊያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በተከራዩ ፡ ሒሳብና ፡ ኪሣራ ፡ ካፒቴን ፡ ጭነቱ ፡ እንዲራገፍ ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ አለው ። ካፒቴኑ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ መልካም ፡ አጠባበቅ ፡ አስፈላጊውን ፡ ድርጅትና ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፷፬ ። የመጫኛውንና ፡ የማራገፊያውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።**

ልዩ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለመጫኛ ፡ የተመደበውን ፡ ጊዜ ፡ ለማራገፊያው ፡ በተመደበው ፡ ጊዜ ፡ ለውጦ ፡ ማቻቻል ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፻፷፭ ። የመጫኛና ፡ የማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ መቈጠርን ፡ የሚያግዱ ፡ ምክንያቶች ።**

(፩) በመርከቡ ፡ ማሳፈር ፡ ወይም ፡ የማራገፍ ፡ ሥራ ፡ ካልተሠራባቸው ፡ በቀር ፡ በወደቡ ፡ ባለው ፡ ልማዳዊ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ በበዓልና ፡ ለዕረፍት ፡ በተመደቡት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ለጭነት ፡ ወይም ፡ ለማራገፍ ፡ የተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ አይታሰቡም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ለማሳፈርና ፡ ለማራገፍ ፡ የተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ መቈጠራቸው ፡ ይታገዳል ።

(፫) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ ቢያጋጥምም ፡ እንኳ ፡ መስናክሉ ፡ ተራዝሞ ፡ የሚቈይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዳኛው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜን ፡ (ዲመረጅ) ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ መቀነስ ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ለመጫኛውና ፡ ለማራገፊያው ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜና ፡ ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ጭማሪዎች ፡ መታሰባቸው ፡ አይታገድም ።

**ቍ ፡ ፻፷፮ ። ስለ ፡ ማፋጠን ፡ የሚሰጥ ፡ ጕርሻ ።**

(፩) ለመጫኛና ፡ ለማራገፊያ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ መርከቡ ፡ ነጻ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገ ፡ ተከራይ ፡ ለዚሁ ፡ ለተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከሚከፈለው ፡ ሒሳብ ፡ መጠን ፡ የሥራ ፡ ማፋጠን ፡ ጕርሻ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ለሚሰጠውም ፡ የሥራ ፡ ማፋጠን ፡ ጕርሻ ፡ አቈጣጠር ፡ የመጫኑ ፡ ወይም ፡ የማራገፉ ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ መታሰቡን ፡ የሚያግዱትም ፡ ቀኖች ፡ ተጨምረው ፡ ይታሰባሉ ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ የሁለቱ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ስምምነት ፡ ሊወገዱ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። ማቻቻል ።**

ለመጫኛና ፡ ለማራገፊያ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ለመጫን ፡ ወይም ፡ ለማራገፍ ፡ በተደረገው ፡ የሥራ ፡ ማፋጠን ፡ ምክንያት ፡ በተሰጠው ፡ ጉርሻ ፡ መካከል ፡ የሚሆነው ፡ መቻቻል ፡ በገንዘብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጊዜ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። ቀዳሚ ፡ መብትና ፡ ይርጋ ።**

ስለ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ የተደነገጉት ፡ የቀዳሚ ፡ መብትና ፡ የይርጋ ፡ አቈጣጠር ፡ ደንቦች ፡ ለመጫኛና ፡ ለማራገፊያ ፡ ጊዜ ፡ ከተወሰኑት ፡ በላይ ፡ ላሉት ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜና ፡ (ዲመረጅ) ፡ ለሁለተኛው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ (ዳሜጅ ፎር ፡ ዲቴንሽን ) ፡ ተፈጻሚ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ስምምነት ፡ ያልተደረገባቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜና ፡ ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ።**

በማመላለሻ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብቶች ፡ መቅረቱ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ ጭነቱ ፡ በሚጫንበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለተፈጸሙት ፡ የተጨማሪ ፡ ጊዜና ፡ ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ኪሣራዎች ፡ የቀዳሚነት ፡ መብታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይቀራሉ ።

## ክልፍ ፡ ፬ ።

## ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሚደረግ ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፸ ። ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸም ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ።**

ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ በመላው ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ በተወሰነው ፡ ባንዱ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፩ ። የአከራዩ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) መርከቡን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ለማካሄድ ፡ ካለው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ለተያያዙት ፡ ግዴታዎች ፡ አላፊው ፡ አከራዩ ፡ ነው ።

(፪) አከራዩ ፡ ለመርከቡ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ማቅረብ ፡ አሟልቶ ፡ ማደራጀት ፤ ለመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ መቅጠር ፡ መመገብ ፤ ደመወዛቸውን ፡ መክፈል ፡ ሥንቅ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፪ ። የተከራዩ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ተከራዩ ፡ ለመርከቡ ፡ የንግድ ፡ አመራር ፡ ጉዳይ ፡ ላሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

(፪) ለመርከቡ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ነዳጅ ፡ ለማፍያው ፡ ጥሩ ፡ ውሃ ፡ ቅባት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። በራሱ ፡ ጥያቄ ፡ የመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ ከተወ

ሰነው ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ ውጭ ፡ ላደረጉት ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈላቸውን ፡ ሒሳብና ፡ እንዲሁም ፡ ለወደብ ፡ ኪራይ ፡ ለመርከብ ፡ መምራት ፡ መርከቡን ፡ ለማስነተትና ፡ መርከቡ ፡ ለሚሰጠው ፡ የንግድ ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈሉትንም ፡ ሌሎች ፡ ወጪዎች ፡ የሚችል ፡ ራሱ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፫ ። የኪራይ ፡ ዕዳ ።**

መርከቡ ፡ በሱ ፡ ይዞታ ፡ ውስጥ ፡ እስከሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የመርከብ ፡ ኪራይ ፡ የሚከፍል ፡ ተከራዩ ፡ ነው ። መርከቡ ፡ ባንድ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት፡ የቆመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቅጣት ፡ የተወረሰ ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኪራዩ ፡ የሚከፈለው ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ እስከ ፡ ደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ሒሳብ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፬ ። እንደ ፡ ጠፋ ፡ የሚቈጠር ፡ መርከብ ።**

መርከቡ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ የሚቈጠር ፡ ሲሆን ፡ የመጨረሻው ፡ ወሬ ፡ እስከተሰማበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ኪራይ ፡ በሙሉ ፡ ተከፋይ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ የተጀመረው ፡ ጒዞ ፡ ሊፈጸም ፡ ይገባበት ፡ በነበረውና ፡ ይህ፡ የመጨረሻው፡ ወሬ ፡ እስከ ፡ ተሰማበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ላለው ፡ ጊዜ ፡ ግማሽ ፡ ኪራይ ፡ ይከፈላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፭ ። የመርከቡ ፡ መዘግየት ።**

(፩) በባሕር ፡ ጒዞ ፡ ላይ ፡ በሚደርሱት ፡ ችግሮች ፡ ምክንያት ፡ መርከቡ ፡ ጒዞውን ፡ በማቋረጡ ፡ ምክንያት ፡ ቢዘገይም ፡ እንኳ ፡ ኪራዩ ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

(፪) ከመርከቡ ፡ የራሱ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ከሠራተኞቹ ፡ ተግባር ፡ የተነሣ ፡ መርከቡ፡ የቆመው ፡ ሳያቋርጥ ፡ ከ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ በላይ ፡ የበለጠ ፡ ከሆነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቆሞ ፡ ላሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ኪራይ ፡ አይከፈለውም ።

**ቍ ፡ ፯፻፮ ። ሒሳቡ ፡ ያልተከፈለው ፡ አከራይ ፡ መብት ።**

(፩) ለሒሳቡ ፡ መክፈያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ የመርከቡ ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ ያልተከፈለው ፡ አከራይ ፤ ለከፋዩ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ፍሬ ፡ ሳያስገኝ ፡ ከቀረበት ፡ ካንድ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የኪሣራ ፡ መጠየቅ ፡ መብቱ ፡ ሳይቀር ፡ መርከቡን ፡ መልሶ ፡ ለመሰውድ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለመድረሻ ፡ እተወሰነበት ፡ ስፍራ ፡ አድርሶ ፡ የተባለውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ መያዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፯ ። ተከራዩ ፡ የሚፈጽመው ፡ የውል ፡ ማራዘም ፡ ጒዳይ ።**

(፩) መርከቡን ፡ ለባለቤቱ ፡ እንዲመልስ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ለማስረከብ ፡ ያልቻለ ፡ ተከራይ ፤ ይህን ፡ መርከብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ለመመለስ ፡ ያልቻለው ፡ መርከቡ ፡ በጒዞ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

እንዲመልስ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፋቸው ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀኖች ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ከፍሎ ፡ ከእነዚሁ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ለሚከፈል ፡ ኪሣራ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) ለመርከቡ ፡ መመለሻ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ መርከቡን ፡ የመለሰ ፡ ተከራይ ፡ ለኪራይ ፡ የተወሰነው ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ እንዲቀነስለት ፡ ሊጠይቅ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፰ ። መርከቡን ፡ ስለ ፡ መመለስ ።**

ለኪራዩ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ተከራዩ ፡ መርከቡን ፡ ለአከራዩ ፡ የሚመልሰው ፡ በስምምነት ፡ በወሰኑት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፱ ። የመርከቡን ፡ የንግድ ፡ ሥራና ፡ የባሕር ፡ ጕዞውን ፡ ጕዳይ ፡ በመምራት ፡ ሥራውን ፡ በኣላፊነቱ ፡ የሚያከናውን ፡ ተከራይ ።**

(፩) የመርከቡን ፡ የንግድና ፡ የባሕር ፡ ጕዞ ፡ ሥራ ፡ አጠቃሎ ፡ ለሚመራው ፡ ተከራይ ፡ አከራዩ ፡ መርከቡን ፡ ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከነመርከበኞቹ ፡ ለማስረከብ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ስምምነት ፡ ጕዳይ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፫ ፣ ፪፻፬ ፣ ፪፻፭ ፣ ፪፻፮ ፣ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ፪፻፯ ፡ እና ፡ ፪፻፰ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ የተረጋገጠ ፡ የማመላለሻ ፡ ውልን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፲ ። የድንጋጌዎች ፡ ወሰን ።**

(፩) በዚህ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚጸኑት ፡ በተለይ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ በተጫኑት ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ሰነድ ፡ በተረጋገጡ ፡ የጭነት ፡ ማመላለሻ ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የመርከብ ፡ መከራየት ፡ ውል ፡ ሰነድ ፡ ባለው ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ። ነገር ፡ ግን ፡ መርከቡ ፡ የተከራየው ፡ በኪራይ ፡ ሰነድ ፡ (በቻርተር ፡ ፓርቲ) ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚሰጠው ፡ የጭነት ፡ የማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ በአመላላሹና ፡ በሰነድ ፡ አምጪው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ከሚመራበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በዚሁ ፡ በሚሰጠው ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ ድንጋጌዎቹ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) የሚጸኑትም ፡ ዕቃዎቹ ፡ ከመርከቡ ፡ ላይ ፡ ከተጫኑበት ፡ አንሥቶ ፡ እስከሚራገፉበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

BACK



(፩) በመርከቡ ፡ ደጅ ፡ (ዴክ ፡) ላይ ፡ ስለ ፡ ተጫኑት ፡ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ እንስሶች ፡ እነዚሁ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አይፈጸሙባቸውም ።

(፫) በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አመላላሽ ፡ (ትራንስፖርተር) ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ከጫኚው ፡ ጋራ ፡ በአንድ ፡ የማመላለሻ ፡ ውል ፡ ተካፋይ ፡ የሆነው ፡ ተከራይ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፻፹፩ ። የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

የንግድ ፡ ዕቃውን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ አመላላሹ ፡ ወይም ፡ የእሱ ፡ እንደራሴ ፡ ለጫኙ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፻፹፪ ። በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፈው ።

በጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ አመላላሹ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ቀኑን ፡ መጻፍና ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

ይኸውም ፡ የሚያመለክተው ፡—

(ሀ) የአመላላሹን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ለ) የጫኙ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) የመርከቡ ፡ ስምና ፡ ዜግነቱ ፤

(መ) ለዕቃው ፡ መድረሻ ፡ የተመደበውን ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያው ፡ ደረሰኝ ፡ በሰው ፡ ስም ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዕቃ ፡ ተቀባዩን ፡ ስም ፤

(ሠ) አመላላሹ ፡ የተረከባቸውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፤

(ረ) ዕቃው ፡ የተጫነበትን ፡ ስፍራና ፡ ቀን ፤

(ሰ) የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፻፹፫ ። የጭነት ፡ ምልክት ።

እንዲሁም ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያው ፡ ደረሰኝ ፡ የጭነቱን ፡ ምልክትና ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ዕቃው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ከመሳፈሩ ፡ በፊት ፡ ዕቃ ፡ ጫኙ ፡ በሰጠው ፡ የጽሑፍ ፡ መግለጫ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የዕቃዎቹን ፡ የጥቅሎችን ፡ ቊጥር ፤ የዕቃውን ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ ክብደት ፡ እንዲሁም ፡ የሚታየውን ፡ የዕቃዎቹን ፡ ሁኔታና ፡ አደረጃጀት ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) ምልክቶቹም ፡ ዕቃውን ፡ ለመለየት ፡ በሚቻልበት ፡ ሁኔታና ፡ እስከ ፡ ማስረከቢያው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለማንበብ ፡ በሚቻልበት ፡ አኳኋን ፡ መጻፍ ፡ አለባቸው ።

(፫) አመላላሹ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ የዕቃዎቹን ፡ ምልክት ፡ ቊጥር ፡ ብዛት ፡ ዐይነት ፤ ወይም ፡ ክብደት ፡ በሚገባ ፡ ለመመርመር ፡ በቂ ፡ ዘዴ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ የሰጣቸውን ፡ መግለጫ ፡ ትክክለኛነት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ኖሮት ፡ የሚጠራጠር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ መግለጫ ፡ በጭነቱ ፡

BACK



ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ አልጽፍም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፬ ። ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ የሰጣቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆኑ ፡ መግለጫዎች ።**

የተጫኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ ምልክታቸውን ፤ ቍጥራቸውን ፤ ዐይነታቸውን ፡ ወይም ፡ ክብደታቸውን ፡ ትክክል ፡ ባልሆነ ፡ ዐይነት ፡ ለአመላላሹ ፡ የሚሰጥ ፡ ዕቃ ፡ አስጫኝ ፡ ይህ ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሊያደርሰው ፡ በሚችለው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራና ፡ ወጪ ፡ ለአመላላሹ ፡ አላፊ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አመላላሹ ፡ ጫኝ ውን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በተሰጠው ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ በሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መከራከሪያ ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፭ ። ዐውቆ ፡ የተደረገ ፡ አሰተኛ ፡ መግለጫ ።**

ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በዕቃው ፡ ዐይነት ፤ ብዛት ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሰው ፡ ጉዳ ትና ፡ ኪሣራ ፡ ሁሉ ፡ አመላላሹ ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፪፻፮ ። ዕቃው ፡ ከመጫኑ ፡ በፊት ፡ የተሰጠ ፡ ደረሰኝ ።**

ዕቃው ፡ ከመጫኑ ፡ በፊት ፡ ለዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ የተሰጠ ፡ ዕቃ ፡ ደረሰኝ ፡ ሲኖር ፡ ይህ ፡ ደረሰኝ ፡ የተሰጠበት ፡ ዕቃ ፡ ለአመላላሹ ፡ ለመስጠቱ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆ ናል ። ዕቃውም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ከተጫነ ፡ በኋላ ፤ ለዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ የተሰጠ ፡ የዕቃው ፡ ደረሰኝ ፡ ዕቃው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ መሳፈሩን ፡ በሚያረጋግጥ ፡ ደን በኛ ፡ በሆነ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ይለወጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፯ ። ዋና ፡ የሆኑ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኞች ።**

(፩) ለጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚሰጠው ፡ ደረሰኝ ፡ ዋናው ፡ በሁለት ፡ ተጽፎ ፡ አንዱ ፡ ለዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ አንደኛው ፡ ለአመላላሹ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ለአመላላሹ ፡ የሚሰጠው ፡ አንዱ ፡ ደረሰኝ ፡ አስጫኙ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ፈር ሞበት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተላልፎ ፡ የማይሰጥ ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ይጻፍበታል ።

(፫) ለጫኙ ፡ የሚሰጠው ፡ ደረሰኝ ፡ ደግሞ ፡ አመላላሹ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ፈር ሞበት ፡ ሕጋዊ ፡ ለሆነው ፡ የደረሰኙ ፡ ያዥ ፡ ዕቃውን ፡ የመረከብና ፡ በዕቃውም ፡ የማዘዝን ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፰ ። የተባዛ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ።**

(፩) ለዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ ከተሰጠው ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ዋና ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ ቍጥራቸው ፡ በየሰነዱ ፡ ላይ ፡ እየተጻፈ ፡ ብዙ ፡ ግልባጮች ፡ ለማውጣት ፡ ይች ላል። እያንዳንዱም ፡ ግልባጭ ፡ ተባዝተው ፡ የወጡትን ፡ ግልባጮች ፡ ብዛት ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) እነዚህም ፡ ግልባጮች ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ መብት ፡ የሚያስገኙ ፡ ናቸው ፤ በአ ንዱ ፡ ግልባጭ ፡ ነገሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ካገኘ ፡ ሌሎቹ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፻፹፱ ። የጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ዐይነት ።

የጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ በሰው ፡ ስም ፤ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ለአምጪው፡ የሚል ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፺ ። የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ መዘዋወር ።

(፩) በስንዱ ፡ ላይ ፡ ስሙ፡ለተጠራ፡ላንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በንግድ ፡ ስም ፡ የሚተላለፍ ፡ አይደለም ፤ በደረሰኙ ፡ ላይ ፡ ስሙ ፡ ለተጠራው ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አመላላሹ ፡ ዕቃውን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስረከብ ፡ አይ ችልም ።

(፪) በትእዛዝ ፡ የሚል ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመ ፈረም፡ለሌላ፡ሰው፡ለመተላለፍ ፡ ይችላል ። በጀርባው ፡ ላይ ፡ ለተጻፈው ፡ ተጠ ቃሚ ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዕቃውን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስረከብ ፡ አይቻልም።

(፫) ላምጪው፡የሚል፡ወይም ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ስም ፡ ሳይሞላበት ፡ የተፈረመ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነው ። አመ ላላሹም ፡ ይህንን ፡ ደረሰኝ ፡ ተቀብሎ ፡ ዕቃውን ፡ ያስረክባል ።

ቍ ፡ ፻፺፩ ። ማስተላለፍ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ በንግድ ፡ አሠራር ፡ ለማስተላለፍ ፡ ክልክል ፡ መሆኑን ፡ በጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ተነባቢ ፡ ጽሑፍ፡ ማመልከት ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፻፺፪ ። ደረሰኞቹን ፡ በያዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ፡ክርክር ።

በአንድ ፡ በትእዛዝ ፡ በሆነ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ የተባዙትን፡ ግልባጮች ፡ በያዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ የተነሣ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመ ላላሹ ፡ የንግድ ፡ ዕቃውን ፡ ከማስረከቡ ፡ በፊት ፡ ከግልባጭ ፡ አቅራቢዎቹ ፡ መካ ከል ፡ በደረሰኙ፡ ጀርባ ፡በተጻፈውና፡በተፈረመው፡ቀን፡መሠረት ፡ቀዳሚ፡ለሆነው፡ ያዥ፡የቀዳሚነቱን ፡ መብት ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፺፫ ። ቅን ፡ ልቡና ፡ ላለው ፡ ያዥ ፡ ዕቃውን ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

በንግድ ፡ አሠራር ፡ ለማስተላለፍ ፡ ከሚቻሉት ፡ ግልባጮች ፡ አንዱን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ ዕቃው ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ሌላውን ፡ ግልባጭ ፡ የሚያ መጣው ፡ ሰው ፡ የቀረበው ፡ ግልባጭ ፡ ቀኑ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ግልባጭ ፡ በፊት፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አይሰጠውም ።

ቍ ፡ ፻፺፬ ። በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝና ፡ በመርከቡ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ስምምነት ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ ፡ ክርክር ።

(፩) ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ እንዲፈጸም ፡ የተስማሙበት ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ በጭነት፡ ማስታወቂያ፡ ደረሰኝ፡ላይ፡የተጻፈው ፡ የውል፡

ቃል ፡ ስለ ፡ መርከቡ ፡ መከራየት ፡ ጕዳይ ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ተቀ
ዳሚ ፡ ብልጫ ፡ አይሰጠውም ።

(፪) የመርከቡ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ ካወቀ ፡ የዚሁ ፡ ውል ፡ ቃሎች ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ያገኘ ፡ የሆነውን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፰ ። የማስረከብ ፡ ትእዛዝ ።

(፩) ከጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ የተነሣ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ለማዘዝ ፡ የሚችል ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በማመላለሻው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኞች ፡ የተመለከቱትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዕቃ ፡ ድብሎች ፡ ካፒቴኑ ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ ተቀባዩ ፡ ( ኮንሳይኒ ) ፡ እንዲያስረክባቸው ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ከአመላላሹ ፡ ወይም ፡ ከዕቃ ፡ ተቀባዩ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) አመላላሹም ፡ መረከቢያ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ በማመልከት ፡ በዋናው ፡ በንግድ ፡ ስም ፡ የሚተላለፍ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ። እነዚህንም ፡ ትእዛዞች ፡ አመላላሹና ፡ ጥያቄ ፡ አቅራቢው ፡ ይፈርሙባቸዋል ፤ እንዲሁም ፡ በጭነቱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ጭነት ፡ በብዙ ፡ የማስረከብ ፡ ትእዛዝ ፡ ተከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመላላሹ ፡ ዋናውን ፡ በንግድ ፡ ስም ፡ የሚተላለፍ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ መልሶ ፡ መውሰድ ፡ አለበት ።

(፫) በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተሰጡት ፡ የዕቃ ፡ መረከቢያ ፡ ትእዛዞች ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ (፫) የተመለከቱትን ፡ መብቶች ፡ ያስገኛሉ ። ትእዛዞቹም ፡ በሰው ፡ ስም ፤ በትእዛዙ ፡ ወይም ፡ ላምጪው ፡ የሚል ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፱ ። የአመላላሹ ፡ ግዴታዎች ።

(፩) አመላላሹ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፰ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ግዴታዎች ፡ ይኖሩበታል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የተጫኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ በጥንቃቄና ፡ በሚገባ ፡ ለመጫን ፤ ለአጠባበቃቸው ፤ በሚገባ ፡ አቀማመጥ ፡ እንዲደረደሩ ፡ ስለ ፡ ጕዞዋቸው ፤ ስለ ፡ ጥበቃቸው ፤ ስለ ፡ መልካም ፡ አያያዛቸውና ፡ ስለ ፡ ማራገፉ ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፲ ። የአመላላሹ ፡ አላፊነት ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ዕቃ ፡ አመላላሹ ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ አላፊነት ፡ አይደርስበትም ።

(ሀ) በካፒቴኑ ፤ በመርከበኞቹ ፤ በመርከብ ፡ ነጂዎች ፤ ወይም ፡ በሌሎቹ ፡ በአመላላሹ ፡ ሠራተኞች ፡ በመርከቡ ፡ የባሕር ፡ ጕዞ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ አስተዳ

BACK



ደር ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፤

(ለ) የአመላላሹ ፡ ቸልተኛነት ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቃ ጠሎ ፡ ምክንያት ፤

(ሐ) በባሕር ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ መርከብ ፡ በሚያንሳፍፉ ፡ በሌሎች ፡ ሐይቆች ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጉዳት ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ድንገተኛ ፡ መሰናከል ፡ ምክንያት ፤

(መ) በአልታሰቡ ፡ አደጋዎች ፡ አጋጣሚነት ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያቶች ፤

(ሠ)በጦርነት ፡ ምክንያት ፤

(ረ) የሕዝብ ፡ ጠላት ፡ በሆነ ፡ ሽብርና ፡ ሁከት ፡ ምክንያት ፤

(ሰ) በነጋሢ ፡ ወይም ፡ በመሪዎች ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ መርከቡ ፡ ሲታሰር ፡ ወይም፡ ሲታገድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በተደረገ ፡ ምክንያት ፡ ሲያዝ ፤

(ሸ) በኳረንቲን ፡ ክልከላ ፡ ምክንያት ፤

(ቀ) በዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ ወይም ፡ በዕቃው ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ በእንደራሴው፡ ወይም ፡ በወኪሉ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ግድፈት ፡ ምክንያት ፤

(በ) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢተነሣ ፡ ነገር ፡ ሥራን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል፡ በአድማ ፡ በመዝጋት ፡ ወይም ፡ በማቆም ፡ ወይም ፡ ሥራው ፡ እንዳይቀጥል ፡ በተደረገ ፡ መሰናከል ፡ ምክንያት ፤

(ተ) በአገር ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ ወይም ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፤

(ቸ) በባሕር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበትን ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ለማዳን ፡ ወይም ፡ ለማዳን ፡ በመሞከር ፡ ምክንያት ፤

(ኀ) ግዙፍነቱ ፡ ወይም ፡ ክብደቱ ፡ በመቀነሱ ፡ ወይም ፡ በተሰወረ ፡ ጕድለት ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ኪሣራ ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ዐይነት ፡ ባለው ፡ በራሱ ፡ ተፈጥሮ ፡ ጕድለት ፡ የተነሣ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፤

(ነ) በዕቃው ፡ መጠቅለያ ፡ በቂ ፡ አለመሆን ፡ የተነሣ ፤

(ኘ) በንግድ ፡ ዕቃው ፡ ላይ ፡ የተደረጉት ፡ ምልክቶች ፡ በቂ ፡ ባለመሆናቸው ፡ ወይም ፡ ባለመስተካከላቸው ፡ የተነሣ ፤

(አ) በቂ ፡ ከሆነ ፡ ትጋትና ፡ ጥንቃቄ ፡ የተሰወሩ ፡ በንግድ ፡ ዕቃው ፡ ላይ ፡ በሚገኙ ፡ የተደበቁ ፡ ጕድለቶች ፡ ምክንያት ፤

(ከ) በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በአመላላሹ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ወኪሎችና ፡ አሽከሮች ፡ ቸልተኛነትና ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ያልመጣ ፡ ጉዳይ፡ ሲሆን ፡ የአመላላሹ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ የወኪሎቹ ፡ የአሽከሮቹ ፡ ጥፋትና ፡ ቸል ተኛነት ፡ የተደረገውን ፡ ጉዳት ፡ ያላስከተለ ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ የዚህን ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰው ፡ ነው ።

በአስጫኙ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ወኪሎችና ፡ አሽ ከሮች ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ቸልተኛነት ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ በአመላላሹ ፡ ወይም ፡

በመርከቡ ፡ ላይ፡ለሚደርስ ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ፡ አስጫኙ፡ ኀላፊ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም።

**ቊ ፡ ፻፺፰ ። በሕግ ፡ የሚወሰን ፡ የአላፊነት ፡ ግምት ።**

(፩) የንግድ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ለሚደርስባቸው ፡ ጉዳትና ፡ ጥፋት ፡ አመላላሹ ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቅበት ፡ ሒሳብ ፤ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ይህ ፡ የሕግ ፡ ኪሣራ ፡ አወሳሰን ፡ የሚታሰበው ፡ በዕቃዎቹ ፡ ጥቅል ፡ ቊጥር ፡ ብዛትና ፡ ዕቃዎቹ ፡ የተጫኑት ፤ በጅምላ ፡ ተጠቃለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጭነቱ ፡ ዋጋ ፡ መወሰኛ ፡ በሆነው ፡ ልክ ፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ ነው ።

(፫) ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎቹን ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ከማሳፈሩ ፡ በፊት ፡ የዕቃዎቹን ፡ ዐይነትና ፡ የዋጋቸውን ፡ ልክ ፡ ካስታወቀና ፡ ይህም ፡ መግለጫ ፡ በጭነት ፡ ማስታወቂያው ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ኪሣራ ፡ አወሳሰን ፡ መከራከሪያ ፡ ሊሆንበት ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፻፺፱ ። ያልተገለጹ ፡ ወይም ፡ በትክክል ፡ ባልሆነ ፡ ዐይነት ፡ የተገለጹ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ።**

ሁኔታቸው ፡ ያልተገለጸ ፡ ወይም ፡ በማይገባ ፡ ዐይነት ፡ የተገለጹ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ ተሳፍረው ፡ ያገኘ ፡ ካፒቴን ፤ ማንኛውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱ ፡ ሳይነካ ፤ እተጫነበት ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ለማራገፍ ፡ ወይም ፡ ለነዚያው ፡ ዐይነት ፡ ዕቃዎች ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ የሚከፈለውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጭነት ፡ ዋጋ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፪፻ ። አደገኛ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ።**

(፩) ቃጠሎ ፡ የማንሣት ፤ የመፈንዳት ፡ ወይም ፡ የአደገኛነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ አመላላሹ ፡ ካፒቴን ፡ ዕቃዎቹ ፡ ወይም ፡ የአመላላሹ ፡ ወኪል ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ቢያውቅ ፡ ኖሮ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ እንዲጫኑ ፡ የማይፈቅድ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜና ፡ በየትኛውም ፡ ስፍራ ፡ ቢሆን ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ኪሣራ ፡ ከመርከቡ ፡ ላይ ፡ እንዲራገፉ ፤ እንዲጠፉ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ እንዳያደርሱ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ እነዚህን ፡ አደገኛ ፡ የሆኑትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለማራገፍ ፡ ለተከፈለው ፡ ወጪና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) አመላላሹ ፡ የዕቃዎቹን ፡ አደገኛነት ፡ ጠባይ ፡ እያወቀ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ እንዲሳፈሩ ፡ ፈቅዶ ፡ የተረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመርከቡ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ጭነት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የሚያደርሱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከላይ ፡ እንደተባለው ፡ ለማራገፍ ፡ ለማጥፋት ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ እንዲያደርሱ ፡ በማድረጉ ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ (ለኅብረት) ፡ ከሚከፈሉት ፡ ኪሣራዎች ፡ በቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፪፻፭ ። ዕቃው ፡ ሲጠፋ ፡ ወይም ፡ ሲበላሽ ፡ ለአመላላሹ ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።**

(፩) በተጫነው ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ የመጥፋት ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ደርሶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከመርከቡ ፡ ላይ ፡ ተራግፎና ፡ በማመላለሻው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ዕቃውን ፡ ለመረከብ ፡ መብት ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ ለተመለከተው ፡ ተቀባይ ፡ ዕቃው ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊትና ፡ በሱ ፡ ጠባቂነት ፡ ውስጥ ፡ ከመግባቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ለአመላላሹ ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ በሚራገፍበት ፡ ወደብ ፡ ለሚገኘው ፡ ወኪሉ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ። ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ በጽሑፍ ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጭነት ፡ ማስታወቂያው ፡ ደረሰኝ ፡ ላይ ፡ በተጻፉበት ፡ ሁኔታ ፡ እንዳለ ፡ እንዳስረከበ ፡ ያህል ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ጥፋቱ ፡ ወይም ፡ ጉዳቱ ፡ የማይታይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የበዓላት ፡ ቀኖች ፡ ሳይቈጠሩ ፡ ዕቃው ፡ ለተቀባዩ ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

(፫) ዕቃውን ፡ በተረካከቡበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ሁኔታ ፡ ተረካቢና ፡ አስረካቢው ፡ አብረው ፡ የተመለከቱትና ፡ የፈተሹት ፡ ከሆኑ ፡ ይህን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፪፻፮ ። የማመላለሻውን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።**

በቍጥር ፡ ፪፻፬ ፡ ፪፻፭ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ለተሰጠባቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ለማመላለሻ ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ ለማፍረስ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፯ ። ስለ ፡ ይርጋ ።**

(፩) ከማመላለሻው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የተገኙት ፡ መብቶች ፡ በይርጋ ፡ የሚታገዱት ፡ የንግድ ፡ ዕቃውን ፡ ከተረከበበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወይም ፡ የማስረከቡ ፡ ጕዳይ ፡ ሳይፈጸም ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕቃውን ፡ ማስረከብ ፡ ከሚገባበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) ሊከፈል ፡ የማይገባው ፡ ሒሳብ ፡ በመከፈሉ ፡ ምክንያት ፡ እንዲመለስ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ይርጋው ፡ መቈጠሩን ፡ የሚጀምረው ፡ ሒሳቡ ፡ ከተከፈለበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፤ ስለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ውሉን ፡ በማፍረስ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ዋናው ፡ ክስ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፰ ። በቀጥታ ፡ የሆነ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ።**

(፩) በቀጥታ ፡ የሆነ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ያወጣ ፡ ሰው ፡ ለማመላለሻ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በተሰጠው ፡ መብት ፡ ይጠቀምበ

ታል ፤ እንዲሁም ፡ ከብዙዎቹ አልፎ ፡ መሄጃ ፡ አጥቢያዎች ፡ በማለፍ ፡ ለሚ ደርሱት ፡ ግዴታዎች ፡ አላፊ ፡ ነው ፤ ራሱ ፡ ምትክ ፡ ላደረጋቸው ፡ ተከታ ታይ ፡ አመላላሾችም ፡ ሁሉ ፡ ዋስ ፡ የሚሆን ፡ ራሱ ፡ ነው ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ ተከታታይ ፡ አመላላሽ ፡ ራሱ ፡ ዕቃውን ፡ በሚጫነበት ፡ ጊዜ ፡ በሚ ደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በደረሰው ፡ በሌላው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ አይ ደለም ።

ቊ ፡ ፪፻፳ ። በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ውስጥ ፡ አመላላሹ ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ፡ ተብሎ ፡ የተደረገው ፡ ውል ፡ የማይጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) በጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ወይም ፡ ከጭነት ፡ ውል ፡ ውጭ ፡ በሆነው ፡ በማናቸውም ፡ የባሕር ፡ መመላለሻ ፡ ሰነድ ፡ በውል ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ባሉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ካለበት ፡ አላፊነት ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በዘወርዋራ ፡ አመላላሹን ፡ ነጻ ፡ የሚያደርገው ፡ ወይም ፡ በሚሠራባቸው ፡ ሕጎችና ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ባሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ያለበትን ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ ተብሎ ፡ የተደረገ ፡ ማንኛውም ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ የማይ ጸናና ፡ ውጤት ፡ የሌለው ፡ ነው ።

(፪) ላመላላሹ ፡ ስለ ፡ ጭነት ፡ የተደረገው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ የሚ ያስተላልፍለት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ከኀላፊነት ፡ ለመዳን ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ መቈጠር ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፪፻፳፩ ። ዕቃ ፡ አመላላሽ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ለማብዛት ፡ ነጻነት ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ዕቃ ፡ አመላላሹ ፡ ያሉትን ፡ መብቶቹንና ፡ ከኀላፊነት ፡ መብት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመተው ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ እንደተመለከተው ፡ ያሉበ ትን ፡ ኀላፊነቶችና ፡ ግዴታዎችን ፡ ለመጨመር ፡ ይህ ፡ የመብት ፡ መተው ፡ ወይም ፡ ግዴታን ፡ የመጨመሩ ፡ ጕዳይ ፡ ለጫኙ ፡ በሚሰጠው ፡ በጭነት ፡ ማስ ታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ከተጻፈ ፡ አመላላሹ ፡ የተባለውን ፡ ለማድረግ ፤

(፪) በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሰው ፡ ጥፋትና ፡ ጉዳት ፡ ከመጫናቸው ፡ በፊትና ፡ በባሕርም ፡ ከተጓዙበት ፡ መርከብ ፡ ከተራገፉ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ አጠባበቃቸው ፡ መልካም ፡ አያያዝና ፡ ጥንቃቄ ፡ አመላላሹን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ግዴታዎችና ፡ አላፊነቶች ፡ ልዩ ፡ ውለታዎችን ፤ ሁኔታዎችን ፡ መብት ፡ መጠበቅን ፡ ወይም ፡ ከግዴታ ፡ የሚያድኑ ፡ ስምምነቶችን ፡ አመላላሹ ፡ ወይም ፡ አስጫኙ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ አይከለከልም ።

ቊ ፡ ፪፻፳፪ ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ቢኖሩም ፡ እንኳ ፤ በዕቃዎች ፡ ልዩ ፡ ጠባይ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ታሰበው ፡ የዕቃ ፡ ማመላለስ ፡ ጕዳይ ፡ የሚያጋጥመው ፡ ልዩ ፡

BACK



የጊዜ ፡ ሁኔታ ፡ ልዩ ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ በንግድ ፡ አሠራር ፡ የሚተላለፍ ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ ያልወጣ ፡ ከሆነ ፤ ይህን ፡ ልዩ ፡ ስምምነት ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ተዋዋዮች ፡ ሊፈጽሙት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፰ ። ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ለተጫነው ፡ ዕቃ ፡ መድረሻ ፡ የተመደበው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃ ፡ ተቀባዩ ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ አስጫኙ ፡ ዕቃ ፡ አመላላሹን ፡ ለዕቃው ፡ መድረሻ ፡ በተወሰነው ፡ ወደብ ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሊከስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፱ ። ጉዳዩን ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ በግልግል ፡ ለመፈጸም ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።

በጭነት ፡ ማስታወቂያው ፡ የደረሰኝ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የገባው ፡ ክርክሩን ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ለመፈጸም ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ዳኞቹ ፡ የሕግን ፡ አሠራር ፡ ባለመከተል ፡ እንዲሠሩ ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጣቸውም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መንገደኞች ፡ ማመላለስ ።

ቍ ፡ ፪፻፲ ። ትርጓሜ ።

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ አመላላሽ ፡ ማለት ፡ የማጓጓዝ ፡ ውል ፡ የሚዋዋሉትን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ማናቸውንም ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብቶችን ፡ ተከራዮችንና ፡ የመርከቡን ፡ ኦፔራተሮች ፡ ይጨምራል ።

(፪) የማጓጓዝ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ የመርከብ ፡ ማከራየትን ፡ ውል ፡ የማይጨምር ፡ ተሳፋሪዎችን ፡ ለማጓጓዝ ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

(፫) ተሳፋሪ ፡ ማለት ፡ በማጓጓዝ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ በመርከብ ፡ የሚጓዝ ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፬) የተሳፋሪዎች ፡ የማጓጓዝ ፡ ውል ፡ በሕግ ፡ በተደነገገው ፡ ፎርም ፡ መሠረት ፡ መሠራት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። የመሳፈሪያውን ፡ ወረቀት ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

የሚሰጠው ፡ የመጓዣ ፡ መሳፈሪያ ፡ ወረቀት ፡ የመንገደኛውን ፡ ስም ፡ የሚገልጽ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመላላሹ ፡ ካልፈደቀለት ፡ በቀር ፡ መንገደኛው ፡ የመሳፈሪያ ፡ ወረቀቱን ፡ ለሌላ ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። የመንገደኛው ፡ የምግብ ፡ ሒሳብ ።

ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የመንገደኛው ፡ የጕዞ ፡ ምግብ ፡

ከመሳፈሪያ ፡ ወረቀቱ ፡ ዋጋ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ የሚታሰብ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፩፻፲፫ ። የመሳፈሪያ ፡ ወረቀት ፡ የሌለው ፡ መንገደኛ ።**

(፩) አንድ ፡ መንገደኛ ፡ የመሳፈሪያ ፡ ወረቀት ፡ ሳይኖረው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ተሳፍሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለካፒቴኑ ፡ ወይም ፡ ለመርከቡ ፡ መዝገብ ፡ ያዥ ፡ (ኮሚሴር ) ፡ ወዲያውኑ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ይህን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከሚደርስበት ፡ ወደብ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ ከወረደበት ፡ ወደብ ፡ ድረስ ፡ ላለው ፡ ጕዞ ፡ የሚከፈለውን ፡ ዋጋ ፡ በእጠፌታ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ ይኖርበታል ።

**ቊ ፡ ፩፻፲፬ ። በመንገደኛው ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ ጕዞ ።**

በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ሳይሆን ፡ ከራሱ ፡ ፈቃድና ፡ አሳብ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ መንገደኛው ፡ ጕዞውን ፡ ለመፈጸም ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ተሰርዞ፡ ለጕዞውም ፡ ተከፍሎ ፡ የነበረው ፡ ዋጋ ፡ ከመንገደኛው ፡ ምግብና ፡ ሥንቅ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ታስቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የምግቡ ፡ ሒሳብ ፡ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፡ ከጕዞው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ሩቡ ፡ ለአመላላሹ ፡ ይከፈለዋል ።

**ቊ ፡ ፩፻፲፭ ። ለመነሻ ፡ በተወሰነው ፡ ሰዓት ፡ ያልቀረበ ፡ መንገደኛ ።**

ለጕዞው ፡ መነሻ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያልቀረበው ፡ መንገደኛ ፡ ለጕዞው ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ለአመላላሹ ፡ ይከፈለዋል ።

**ቊ ፡ ፩፻፲፮ ። የውል ፡ መፍረስ ።**

(፩) በአመላላሹ ፡ ጥፋት ፡ ባልሆነ ፡ ጕዳይ ፡ መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ለማድረግ ፡ የማያስችለው ፡ መሰናከል ፡ ገጥሞት ፡ ከመሄዱ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንገደኛው ፡ ወይም ፡ አመላላሹ ፡ ማንኛውንም ፡ የጉዳት ፡ ካሣና፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፍል ፡ ውሉ ፡ ሊሰረዝ ፡ ይችላል ። አመላላሹም ፡ የተቀበለውን ፡ ዋጋ ፡ ለተሳፋሪው ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) ከአመላላሹ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ ከሚያዛቸው ፡ ሠራተኞች ፡ አሠራር ፡ የተነሣ ፡ ለመርከቡ ፡ መነሻ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ጕዞውን ፡ ሳይጀምር ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቁ ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ሆኖ ፡ መንገደኛው ፡ የጕዞውን ፡ ውል ፡ እንዲሰርዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፩፻፲፯ ። በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የጕዞውን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማስቀረት ።**

አንድ ፡ ጦርነት ፡ በመነሣቱ ፡ ምክንያት ፡ መርከቡ ፡ የመማረክ ፡ አደጋ ፡ እንደሚደርስበት ፡ የሚያሠጋ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ እንደ ፡ ነጻ ፡ የማይቈጠር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መንገደኛው ፡ የጕዞው ፡ ውል ፡ እንዲሰረዝለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፰ ። ጕዞው ፡ በመቅረቱ ፡ ምክንያት ፡ ውሉ ፡ ስለ ፡ መፍረሱ ።**

(፩) አመላላሹ ፡ የመርከቡን ፡ ጕዞ ፡ ያስቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ጕዞውም ፡ በሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ በአመላላሹ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ በቀድሞው ፡ ምትክ ፡ በተተካ ፡ በሌላ ፡ አመላላሽ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ጕዞውን ፡ ለመፈጸም ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጕዞው ፡ ውል ፡ ይፈርሳል ።

(፪) አመላላሹ ፡ በመንገደኞቹ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርስ ፡ በሚችል ፡ ሁኔታ ፡ የመርከቡን ፡ መንገድ ፡ መሥመር ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ በሁለቱ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ መንገደኛው፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራና፡ካሣ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ። ቢሆንም ፡ የጕዞው ፡ መቅረትና ፡ የመንገደኛው ፡ መንገድ ፡ መለወጥ ፡ በትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኪሣራው ፡ ሒሳብ ፡ ከጕዞው ፡ ዋጋ ፡ አጠፌታ ፡ በላይ ፡ ለማለፍ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፱ ። ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አጋጣሚ ፡ ኀይል ፡ ጕዞውን ፡ ስለ ፡ ማቋረጡ ።**

(፩) አንድ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ፡ በማጋጠሙ ፡ ምክንያት፡ ጕዞው ፡ የተቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጕዞው ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋ፡ለተፈጸመው ፡ የጕዞ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ቢሆንም ፡ አመላላሹ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በሚታሰብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በራሱ ፡ ሒሳብ ፡ ሌላ ፡ መርከብ ፡ አቅርቦ ፡ ተተኪው ፡ መርከብ ፡ ጕዞውን ፡ ባቋረጠው ፡ መርከብ ፡ ዐይነት ፡የመንገደኞቹን ፡ ምቾት ፡ የሚጠብቅ ፡ ሆኖ ፡ የመንገደኞቹም ፡ ምግብ ፡ ከጕዞው ፡ ዋጋ ፡ ጋራ፡አብሮ ፡ የተከፈለ፡ሲሆን፡ በተቋረጠው ፡ ጕዞ ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ ጊዜ ፡ ምግባቸውን ፡ አመላላሹ ፡ ችሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጕዞውን ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፳ ። ከራሱ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ጕዞውን ፡ ለማቋረጥ ፡ ስለ፡ ሚገደድ ፡ መንገደኛ ።**

(፩) በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ጕዞውን ፡ ለማቋረጥ፡ የተገደደ ፡ መንገደኛ ፡ የጕዞውን ፡ ዋጋ ፡ የሚከፍለው ፡ ከተጓዘው፡ መንገድ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የጕዞው ፡ ማቋረጥ ፡ የደረሰው ፡ በመንገደኛው ፡ ተግባር ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ መንገደኛው ፡ ለሚቀረው ፡ ጕዞ ፡ የሚከፈለውንም ፡ ዋጋ ፡ ጭምር ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ያዘው ፡ መንገደኛ ።

መንገደኛው ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ ተላላፊ ፡ በሽታ ፡ የያዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከቡ ፡ ሊደርስበት ፡ በሚቻለው ፡ ሕዝብ ፡ በሚኖርበት ፡ በመጀመሪያው ፡ መሬት ፡ እንዲ ወርድ ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። ስለ ፡ ጕዞው ፡ መዘግየት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ ያለ ፡ መፈጸም ፡ አመ ላላሹ ፡ ያለበት ፡ አላፊነት ።

ጕዞው ፡ የዘገየው ፡ ወይም ፡ በጕዞው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ውል ፡ በሚ ገባ ፡ ያልተፈጸመው ፡ ከራሱ ፡ ጕድለት ፡ የተነሣ ፡ አለመሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በመንገደኞቹ ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው አመላላሹ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። ባንድ ፡ መንገደኛ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ የሚ ደርስ ፡ አላፊነት ።

(፩) የመርከብ ፡ መንገደኛ ፡ በሚሞትበት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ በሚደርስበት፡ ጊዜ ፡ የደረሰው ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ የተፈጠረው ፡ አመላላሹ ፡ ኀላፊ ፡ ከማይሆንበት ፡ አካባቢ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፤ ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ የመርከብ ፡ መንገደኛው ፡ በመርከብ ፡ ከተሳፈረበት ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ወረደበት ፡ ቀን ፡ ደረስ ፡ ወይም ፡ በሚሳፈርበትና ፡ በሚወርድበት፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተባለው ፡ የመርከብ ፡ አመላላሽ ፡ በመርከቡ ፡ መን ገደኛ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) በማናቸውም ፡ የመርከብ ፡ መንገደኛ ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ የአመላላሹ ፡ አላፊነት ፡ ለያንዳንዱ ፡ የመርከብ ፡ መንገደኛ ፡ ከ፴፡ሺህ ፡ የኢ.ት/ ብር ፡ አይበልጥም ።

(፫) ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የተወሰነው ፡ ካሣ ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ሲሆን ፡ ለዚህ፡ ጕዳይ ፡ የተመደበው ፡ ካፒታል ፡ ከዚህ ፡ ወሰን ፡ ሊያልፍ ፡ አይችልም ።

(፬) ስለ ፡ ሆነም ፡ አመላላሹና ፡ መንገደኛው ፡ በልዩ ፡ ውል ፡ ከተስማሙ ፡ ኀላፊነ ቱን ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፭) ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ አመላላሹ ፡ ጉዳትን ፡ ዐቅዶ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ በፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ግድፈት ፡ የመጣ ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አመላላሹ ፡ የዚህን ፡ የአላፊ ነት ፡ አወሳሰን ፡ መጠቀሚያ ፡ ለማድረግ ፡ ሊከራከርበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፷፬ ። ስለ ፡ መንገደኞቹ ፡ ዕቃ ፡ አጫጫን ።

(፩) የመንገደኞቹ ፡ ዕቃ ፡ ለመርከቡ ፡ የተሰጠው ፡ በደረሰኝ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

BACK



የዕቃቸው ፡ አጫጫን ፡ ደንብ ፡ የሚመራው ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ዕቃ ፡ አጫጫን ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) አመላላሹ ፡ በደረሰኝ ፡ ባልተረከበውና ፡ መንገደኛው ፡ ራሱ ፡ እየጠበቀ ፡ በሚጓዘው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ የደረሰው ፡ በአመላላሹ ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ ፡ ጥፋት ፡ መሆኑን ፡ መንገደኛው ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ ለጠፋው ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ ለደረሰበት ፡ ዕቃ ፡ አመላላሹ ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፭ ። ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ ማመላለሻ ።**

(፩) መመላለሻው ፡ ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ ነጻ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፷፪ ። ፪፻፷፫ ። ፪፻፷፬ ። የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) በችሮታ ፡ ስም ፡ መመላለሻው ፡ ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ፡ ሲሆን ፡ በመንገደኛው ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በአመላላሹ ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ ፡ ተንኰል ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ቸልተኛነት ፡ መሆኑን ፡ መንገደኛው ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ አመላላሹ ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። ከቍጥር ፡ ፪፻፷፫ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷፭ ። የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፷፫ ፡ እስከ ፡ ፪፻፷፭ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። በመንደገኞቹ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ አመላላሹ ፡ ያለው ፡ የመያዣ ፡ መብት ።**

አመላላሹ ፡ በመንገደኞቹ ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ መብቶች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ መንገደኞች ፡ ዕቃ ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። ስለ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ።**

(፩) ስለ ፡ መንገደኞቹና ፡ ደረሰኝ ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ የመንገደኞች ፡ ዕቃዎች ፡ ጕዞ ፡ ምክንያት ፡ የሚነሣው ፡ ክስ ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፪) የይርጋውም ፡ ዘመን ፡ መቈጠሩን ፡ የሚጀምረው ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ከደረሰበት ፡ ወይም ፡ የጕዞው ፡ ውል ፡ ከተፈረመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) በደረሰኝ ፡ ስለ ፡ ተጫኑት ፡ ዕቃዎች ፡ ከማመላለሻ ፡ ውል ፡ የተነሣ ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የሚደረገው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ የሚመራው ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፫ ፡ በተደነገገው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ ፯ ።

## ስለ ፡ ግጭት ፡ ስለ ፡ ርዳታና ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ከአደጋ ፡ ማዳን ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ግጭት ።

ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ግጭት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ደንቦች ።

በመርከቦች ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመርከቦቹ ፡ በዕቃ ዎቹ ፡ ወይም ፡ በላዩ ፡ በሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ለሚደርስባቸው ፡ ጉዳቶች ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ ኪሣራዎች ፡ አከፋፈል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ባሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ይመራሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፸ ። ድንገተኛ ፡ ግጭት ።

ግጭቱ ፡ የተደረገው ፡ በድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ በማንኛቸውም ፡ ጥፋት ፡ ያለመሆኑ ፡ ሊታወቅ ፡ ባልተቻለ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳቱ ፡ በደረሰበት ፡ ላይ ፡ ይቀራል ፤ ማለት ፡ የጉዳቱን ፡ ካሣ ፡ ተጐጂዎቹ ፡ በየራሳቸው ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፸፩ ። ከመርከቦቹ ፡ ባንዱ ፡ ጥፋት ፡ የተደረገ ፡ ግጭት ።

ባንዱ ፡ ወገን ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ በተደረገ ፡ ግጭት ፡ በመርከብ ፤ በሰው ፡ ወይም ፡ በዕቃ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ኪሣራ ፡ መቻል ፡ ያለበት ፡ ጥፋቱን ፡ ያደረገው ፡ ወገን ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፸፪ ። የሁለት ፡ ወይም ፡ የብዙ ፡ መርከቦች ፡ የጋራ ፡ ጥፋት ።

(፩) ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ ጥፋተኞች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ በየበኩሉ ፡ ባደረገው ፡ ጥፋት ፡ መጠን ፡ ለደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ። ሁኔታዎቹ ፡ የያንዳንዱን ፡ ድርሻ ፡ ለይቶ ፡ ለመወሰን ፡ የማያስችሉ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላፊነቱን ፡ ትክክል ፡ አድርገው ፡ ይከፋፈላሉ ።

(፪) በመርከቦቹ ፡ ወይም ፡ በጭነታቸው ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ ፡ በመንገደኞቹ ፡ ወይም ፡ በላዩ ፡ በሚገኙ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ መጠን ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያንድነት ፡ አላፊነት ፡ ሳይኖርበት ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ ጥፋተኛው ፡ መርከብ ፡ ነው ።

(፫) ጥፋተኛ ፡ የሆኑ ፡ መርከቦች ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ በማቍሰል ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ላደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ባንድነት ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ። በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ አብዛኛውን ፡ ዕዳ ፡ የከፈለው ፡ መርከብ ፡ ድርሻውን ፡ ካልከፈለው ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛ ፡ ከሆነው ፡ መርከብ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፴፫ ። በነጂ ፡ ጥፋት ፡ የሚደረግ ፡ ግጭት ።

ግጭቱ ፡ በነጂ ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ነጂ ፡ ሕግ ፡ ያስገደደው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፴ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፫ ፡ የተወሰነው ፡ ኀላፊነት ፡ ይጸናበታል።

ቍ ፡ ፪፻፴፬ ። የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ወሰን ።

የመርከቡን ፡ አመራር ፡ በመፈጸም ፡ ወይም ፡ ባለመፈጸም ፡ ወይም ፡ ደንቦችን ፡ ባለመጠበቅ ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በዕቃዎች ፡ ወይም ፡ በላዩ ፡ በሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ግጭት ፡ ባይደረግም ፡ እንኳ ፡ መርከቡ ፡ ለሚያደርሳቸው ፡ ጉዳቶች ፡ ስለ ፡ ጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻፴ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፫ ፡ ያሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፴፭ ። የካፒቴኖቹ ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ግጭት ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ የተጋጩት ፡ መርከቦች ፡ ካፒቴን ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ለራሱ ፡ መርከብ ፡ ለሠራተኞውና ፡ ለመንገደኞቹ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ ለማድረግ ፡ ከቻለ ፡ ለሌላው ፡ መርከብ ፡ ለሠራተኞቹና ፡ ለመንገደኞቹ ፡ ርዳታውን ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሚቻለው ፡ መጠን ፡ የራሱን ፡ መርከብ ፡ ስምና ፡ የመርከቡ ፡ ቀዋሚ ፡ ወደብ ፡ እንዲሁም ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣና ፡ ወዴትም ፡ እንደ ሚሄድ ፡ ለሌላው ፡ መርከብ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፴፮ ። ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) በግጭት ፡ ምክንያት ፡ ለደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ኪሣራ ፡ ክስ ፡ አቀራረብ ፡ አንድም ፡ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ፎርማሊቴ ፡ ) አያስፈልገውም ።

(፪) ስለ ፡ ግጭቱ ፡ አላፊነት ፡ ሕጋዊ ፡ ግምት ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪፻፴፯ ። ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

በግጭት ፡ ምክንያት ፡ ለሚመጣ ፡ ኪሣራ ፡ ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) ግጭቱ ፡ በተደረገበት ፡ ቦታ ፡ ባንድ ፡ ወደብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ባሕር ፡ ክፍል ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ለ) በተከሳሹ ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ሐ) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ አከራይ ፡ መርከቡን ፡ ባስመዘገበበት ፡ ወደብ ፡ ያለው ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(መ) በዋስ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መድን ፡ መያዙ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ከታዘዘ ፡ በኋላ፡ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ መርከቡ ፡ በደንብ ፡ በተያዘበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

BACK



**ቊ ፡ ፪፻፴፫ ። ይርጋ ።**

(፩) ከቍጥር ፡ ፪፻፴ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፩ ፡ ከተመለከቱት ፡ ተግባሮች ፡ ባንዱ ፡ በንብረቶች ፡ ወይም ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ፡ ኪሣራዎች ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ አደጋው ፡ ከሆነበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳሉ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ ፫ኛ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አቀራረብ ፡ ክፍያው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከቱት ፡ ጊዜዎች ፡ የከሳሹ ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ዋናው ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ባለበት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በሆነው ፡ ባሕር ፡ ክፍል ፡ የተከሳሹ ፡ መርከብ ፡ ሊያዝ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የይርጋው ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ አይጀመርም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ርዳታ ፤ በባሕር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ከአደጋ ፡ ማዳን ።

**ቊ ፡ ፪፻፴፬ ። የርዳታና ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ በማዳን ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ደንቦች ።**

ርዳታና ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ማዳን ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራሉ ።

**ቊ ፡ ፪፻፴፭ ። የሥራ ፡ ዋጋ ።**

ማናቸውም ፡ ጠቃሚ ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ የርዳታ ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የማዳን ፡ ተግባር ፡ ከአደጋ ፡ ከዳኑት ፡ ዕቃዎች ፡ ግምት ፡ የማይበልጥ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈለዋል ።

**ቊ ፡ ፪፻፴፮ ። በግድ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የማዳን ፡ ተግባር ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የማይከፈልበት ሁኔታ ።**

ርዳታ ፡ የተደረገለት ፡ መርከብ ፡ ግልጽና ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ክልከላ ፡ ሲያደርግ ፡ ክልከላውን ፡ በመተላለፍ ፡ ለርዳታ ፡ ተግባር ፡ ተሳታፊ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

**ቊ ፡ ፪፻፴፯ ። ሀብትነታቸው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ በሆኑ ፡ መርከቦች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ መረዳዳት ።**

ሀብትነታቸው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ በሆኑ ፡ መርከቦች ፡ መካከል ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ በመረዳዳት ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ማዳን ፡ ሲደረግ ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፵፫ ፡ የመጐተትና ፡ የመንዳት ፡ ልዩ ፡ ርዳታ ።

ማንኛውም ፡ መርከቡን ፡ በመጐተትና ፡ በመንዳት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ተግባር ፡ ለመርዳት ፡ ውል ፡ የገባ ፡ ወገን ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ፡ የፈጸመው ፡ ተግባር ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ከሆነ ፡ የወሮታ ፡ ገንዘብ ፡ አይከፈለውም ።

ቍ ፡ ፪፻፵፬ ። ሰዎችን ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ማዳን ።

(፩) ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ዳኑት ፡ ሰዎች ፡ አንድም ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ አይሰጥም ።

(፪) በእንደዚሁ ፡ ያሉ ፡ አደጋዎች ፡ ርዳታ ፡ በማድረግ ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ለዳኑት ፡ ሰዎች ፡ መርከብን ፡ ጭነቱንና ፡ ተጨማሪ ፡ ነገሮቹን ፡ ለሚያድኑ ፡ ሰዎች ፡ ከሚሰጠው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ድርሻ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፪፻፵፭ ። የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ አወሳሰን ።

(፩) የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ይወሰናል ።

(፪) መርከቡን ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ያዳኑት ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብቶች ፡ ካፒቴኑና ፡ ሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ ያዳኑ ፡ ሰዎች ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ መከፋፈል ፡ አለባቸው ።

(፫) ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ያዳነው ፡ መርከብ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መርከብ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በባለቤቱ ፤ በካፒቴኑና ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ክፍያው ፡ የሚደረገው ፡ መርከቡ ፡ ዜጋ ፡ በሆነበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፵፮ ። የርዳታ ፡ ስምምነትን ፡ በፍርድ ፡ ስለ ፡ መሻር ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ።

(፩) አደጋው ፡ በሆነበት ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ የርዳታና ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የማዳን ፡ ስምምነት ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ባንዱ ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ የተስማሙባቸው ፡ ውለታዎች ፡ የማይገቡ ፡ መስለው ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመሻር ፡ ወይም ፡ ለመለዋወጥ ፡ ይችላል ።

(፪) በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ያንዱ ፡ ፈቃደኛነት ፡ በማታለል ፡ ወይም ፡ በመሸፈን ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ የቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የሥራው ፡ ዋጋ ፡ ባንዱ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ ከተደረገው ፡ ሥራ ፡ በላይ ፡ ግምቱ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገባብ ፡ ባለው ፡ ወገን ፡ አቤቱታ ፡ ስምምነቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያፈርሰው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፵፯ ። የሥራ ፡ ዋጋ ፡ አወሳሰን ።

፩ኛ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአገልግሎቱን ፡ ዋጋ ፡ የሚወስነው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

BACK



(፩) (ሀ) የማዳኑ ፡ ተግባር ፡ ያስገኘው ፡ መልካም ፡ ውጤት ፤

(ለ) ለማዳኑ ፡ ተግባር ፡ አፈጻጸም ፡ የተደረገው ፡ ችሎታና ፡ ዘዴ ፡ የፈጀው ፡ ጊዜና ፡ የሥራው ፡ ከባድነት ፤

(ሐ) በዳነው ፡ መርከብ ፤ መንገደኞች ፡ ሠራተኞች፤ ወይም ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ይደርስ ፡ የነበረውን ፡ አደጋ ፤

(መ) መርከቡን ፡ ባዳኑት ፡ ሰዎች ፡ ሕይወትና ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ይደርስ ፡ የነበረውን ፡ አደጋ ፡ መጠን ፤

(ሠ) አዳኞቹ ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ረገድ ፡ ወይም ፡ በማንኛቸውም ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ይደርስባቸው ፡ የነበረውን ፡ ኀላፊነት ፤

(ረ) በአዳኞቹ ፡ ሕይወት ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ ያወጡትን ፡ ወጪና ፡ የከሠሩትን ፡ ኪሣራና ፡ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ የማዳን ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ የሠሩባቸውን ፡ መሣሪያዎች ፡ ዋጋ ፤

(ሰ) አዳኞቹ፡የሠሩበት፡መርከብ ፡ ለማዳን ፡ ተግባር ፡ የተስማማ ፡ መሆኑን ፤

(ሸ) በመጀመሪያ ፡ የተገኘውን ፡ ውጤት ፡ ርዳታ ፡ ያደረጉትን ፡ ሰዎች ፡ ድካም ፡ እና ፡ ዋጋ ፡ ከአደጋ ፡ የዳነውን ፡ መርከብ ፡ መንገደኞች ፡ ሠራተኞች ፡ ጭነቱን ፡ ያዳነው ፡ መርከብና ፡ የዳኑት ፡ ሰዎች፡ይደርስባቸው ፡ የነበረውን ፡ አደጋ ፡ ያሳለፉትን ፡ ጊዜ ፡ የዳኑት ፡ ሰዎችና ፡ የሠሩባቸው ፡ መሣሪያዎች፡ የደረሰባቸውን ፡ ጉዳትና ፡ ወጪ ፡ እንዲሁም ፡ ይደርስባቸው፡ለነበሩት ፡ አደጋዎች ፡ የገቡበትን ፡ ኀላፊነት ፡ ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያዳነው ፡ መርከብ ፡ ለልዩ ፡ ሥራ ፡ ማገልገሉን ፡ በማመዛዘን ፤

(፪) የዳነውን ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ።

፪ኛ፤ ከባሕር፡አደጋ፡ያዳኑት ፡ ሰዎች ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ማዳን ፡ ወይም ፡ ርዳታው፡ እንዲደረግ ፡ ማስፈለጉ ፡ ከነሱ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እነዚሁ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ በመሥረቅ ፡ በመደበቅ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ አጥፊዎች፡መሆናቸው ፡ የተገለጠ ፡ እንደ፡ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአገልግሎቱን ፡ ዋጋ ፡ ለመቀነስ ፡ ወይም ፡ እንዳይከፈል ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

፫ኛ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ የተደረገው ፡ ክፍያ ፡ ሲወሰን ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ማመዛዘን ፡ ይገባል።

## ቍ ፡ ፪፻፴፰ ። በመጥፋት ፡ አደጋ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች፡የመርዳት፡ግዴታ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ካፒቴን ፡ ማድረግ ፡ እስከሚቻለው ፡ መርከቡን፡ ሠራተኛውንና፡ መንገደኞቹን ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ የማይደርስባቸው ፡ ከሆነ ፡ በመጥፋት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ርዳታ ፡ እንዲያደርግላቸው ፡ ይገደዳል ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ አከራዩን ፡ የሚያገኘው፡ግዴታና፡ ኀላፊነት፡የለም።

ቍ ፡ ፩፻፹፱ ። ስለ ፡ አገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ።

(፩) ስለ ፡ ርዳታ ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ ማዳን ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ፡አከፋፈል ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የርዳታ ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የማዳን፡ ተግባሮች ፡ ከተፈጸሙበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ። ሆኖም ፡ ርዳታ ፡ የተደረገለት ፡ ምወይ ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የዳነው ፡ መርከብ ፡ የጠያቂው ፡ መኖሪያ ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ በሚገኝበት ፡ በግዛቱ ፡ ባሕር፡ ውስጥ ፡ ያልተያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቆጠር ፡ አይጀምርም ።

(፪) ይህም ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ በቍጥር ፡ ፲፭ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፫) መሠረት ፡ በመርከቡና ፡ በጭነቱ ፡ ኪራይ ፡ በተጨማሪም ፡ በዳኑት ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ቀዳሚ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፩፻፺ ። በመንግሥት ፡ መርከቦች ፡ ላይ ፡ የርዳታ ፡ ደንቦች ፡ አፈጻጸም ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ በመንግሥት ፡ መርከቦችም፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። የመንግሥት ፡ መርከቦች ፡ ርዳታ ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ የማዳን ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንግሥቱ ፡ የግል ፡ መርከብ ፡ አከራይ ፡ ካሉት ፡ መብቶች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ መብቶች ፡ አሉት ።

## አንቀጽ ፡ ፯ ።

## የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

ቍ ፡ ፩፻፺፩ ። የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተግባር ።

አስቦና ፡ በሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ለጋራ ፡ ደኅንነት ፡ ላንድ ፡ የባሕር ፡ ጕዞ ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶችን ፡ ከአደጋ ፡ ለማዳን ፡ የተደረገ ፡ ድንገተኛ ፡ ቤዛነት ፡ ወይም ፡ ድንገተኛ ፡ ወጪዎች ፡ የጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፩፻፺፪ ። ኪሣራውን ፡ የሚከፍለው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

የጉዳት ፡ ኪሣራና ፡ ወጪ ፡ አግባብ ፡ ባላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎች ፡ የገንዘብ ፡ መዋጮ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ ሁኔታ ፡ ይከፈላል ።

ቍ ፡ ፩፻፺፫ ። ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተግባር ፡ በቀጥታ ፡ የተገኙ ፡ ኪሣራዎች ፡ ብቻ ፡ ስለመፈቀዳቸው ።

ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተግባር ፡ በቀጥታ ፡ የተገኙ ፡ አደጋዎች ፡ ኪሣራዎች ፡ ወይም ፡ ወጪዎች ፡ ብቻ ፡ የጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ ተብለው ፡ ይቈጠራሉ ።

ቍ ፡ ፩፻፺፬ ። የማይፈቀዱ ፡ ጉዳቶችና ፡ ኪሣራዎች ።

ከመዘግየት ፡ የተነሣ ፡ በመርከቡና ፡ በጭነቱ ፡ ላይ ፡ የደረሱ ፡ ኪሣራዎች ፡ ወይም ፡ አደጋዎች ፡ በጕዞም ፡ ሆነ ፡ ከጕዞው ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ የመጫኛ ፡ ማራገና

ፊያ ፡ ጊዜው ፡ በማለፉ ፡ በተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ ኪሣራና ፡ ማናቸውም ፡ ቀጥታ ፡ ያልሆኑ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ የገበያ ፡ ዋጋ ፡ መለዋወጥ ፡ ምክንያት ፡ የሆኑ ፡ ኪሣራዎች ፡ የጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ ተብለው ፡ አይቈጠሩም ።

<u>ቍ ፡ ፩፻፺፫ ። የአንደኛው ፡ ወገን ፡ ጥፋት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።</u>

ጥፋተኛ ፡ በሆነው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ቤዛነቱን ፡ ወይም ፡ ወጪውን ፡ ያስከተለው ፡ ምክንያት ፡ በባሕር ፡ ጕዞ ፡ ከተሳፈሩት ፡ ወገኖች ፡ ባንዱ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ ስለ ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ የገንዘብ ፡ ማዋጣት ፡ ተግባር ፡ አይቀርም ።

<u>ቍ ፡ ፩፻፺፬ ። የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ማስረጃ ።</u>

እንዲከፈለው ፡ የጠየቀውን ፡ ኪሣራ ፡ ወይም ፡ ወጪ ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በደንብ ፡ እንዲቀበሉት ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ጥያቄውን ፡ ያቀረበው ፡ ሰው ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፩፻፺፭ ። ልዩ ፡ ወጪ ።</u>

እንዳይደርስ ፡ ከተደረገው ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ወጪ ፡ ጋራ ፡ እስከ፡ተስተካከለ ፡ ድረስ፡ ቢጋራ ፡ ጉዳት ፡ ወጪ ፡ ውስጥ ፡ ይገባ ፡ በነበረው ፡ ወጪ ፡ ፋንታ ፡ የተደረገው ፡ ሌላ ፡ ወጪ ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፩፻፺፮ ። ኪሣራንና ፡ መዋጮን ፡ ስለ ፡ ማስተካከል ።</u>

(፩) የጋራ ፡ ጉዳት ፡ በኪሣራና ፡ በመዋጮ ፡ ረገድ ፡ መስተካከል ፡ የሚችለው ፡ ጕዞው ፡ ባለቀበት ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ የዋጋ ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ የጉዳቱ ፡ መግለጫ ፡ የሚደረግበትን ፡ ቦታ ፡ አወሳሰን፡ በሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

<u>ቍ ፡ ፩፻፺፯ ። የመርከቡን ፡ ጭነት ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ስለ ፡ መጣል ።</u>

ጭነቱ ፡ ቢታወቁ ፡ የንግድ ፡ ልማዶች ፡ መሠረት ፡ ካልተጓዘ ፡ በቀር ፡ የመርከብ ፡ ጭነት ፡ በባሕር ፡ መጣል ፡ እንደ ፡ ጋራ ፡ ጉዳት ፡ አይቈጠርም ።

<u>ቍ ፡ ፩፻፰ ፡ የመርከቡን ፡ ጭነት ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ቢመጣልና ፡ ለጋራ ፡ ደኅንነት ፡ በተደረገ ፡ ሁኔታ ፡ የመጣ ፡ ጉዳት ።</u>

በጋራ ፡ ደኅንነት ፡ ምክንያት ፡ ጭነቱን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ለመጣል ፡ ሲባል ፡ በተከፈተ ፡ በር ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ውሃ ፡ ገብቶ ፡ በመርከቦች ፡ በጭነታቸው ፡ ወይም ፡ በማንኛቸውም ፡ ሌላ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የደረሰ ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ፡ እንደ ፡ የጋራ፡ ጉዳት ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፩፻፸፭ ። ቃጠሎን ፡ በማጥፋት ፡ ስለሚደረግ ፡ አደጋ ።**

በመርከብ ፡ ወይም ፡ በጭነቱ ፡ ላይ ፡ በውሃ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ቃጠሎን ፡ ለማጥፋት ፡ በቃጠሎ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መርከብ ፡ በመቅረፍ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ በማውጣት ፡ የሚደርስ ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ ጋራ ፡ ጉዳት ፡ ይቈጠራል ። ስለ ፡ ሆነም ፡ በመርከቡ ፡ ከፊልና ፡ ባልተጠቀለለ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ በሆነ ፡ ጭነት ፡ ወይም ፡ በእሳት ፡ በተያያዙ ፡ ከንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በተለያዩ ፡ ጥቅሎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ እንደ ፡ ጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ አይቈጠሩም ።

**ቍ ፡ ፩፻፸፮ ። ከአደጋ ፡ የተረፉትን ፡ የመርከቡን ፡ ክፍሎች ፡ በመቍረጥ ፡ ስለ ፡ ማስተካከል ።**

ከአደጋ ፡ የተረፈውን ፡ ክፍል ፡ በመቍረጥ ፡ ወይም ፡ የተረፉትን ፡ አውታሮች ፡ ወይም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የባሕር ፡ አደጋው ፡ የወሰዳቸውን ፡ ክፍሎች ፡ በመቍረጥ ፡ የተነሣ ፡ የሚመጣው ፡ ጉዳት ፡ ከኪሣራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ አይገባም ።

**ቍ ፡ ፩፻፸፯ ። ሆነ ፡ ብሎ ፡ መርከቡን ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።**

መርከቡ ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ እንዲወጣ ፡ ሲደረግ ፡ ከሁኔታዎቹ ፡ የተነሣ ፡ ይህ ፡ ተግባር ፡ ባይደረግ ፡ ኖሮ ፡ መርከቡ ፡ ከጠረፍ ፡ ወይም ፡ ከቋጥኝ ፡ ለመጋጨት ፡ መኀዙ ፡ የማይቀር ፡ ነበር ፡ በሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ከማውጣት ፡ የተነሣ ፡ በመርከቡ ፡ በዕቃው ፡ ወይም ፡ በጭነቱ ፡ ላይ ፡ የሚደርሱ ፡ ጥፋቶችና ፡ ጉዳቶች ፡ በጋራ ፡ ጉዳቱ ፡ ውስጥ ፡ አይታሰቡም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ መርከብ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንዲንሳፈፍ ፡ ለማድረግ ፡ ሲባል ፡ የደረሱት ፡ ኪሣራዎችና ፡ ጉዳቶች ፡ ወይም ፡ ወጪዎች ፡ ቢጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ።

በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ የጋራ ፡ጸጥታ ፡ ለመጠበቅ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ መርከቡን ፡ ከባሕር ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ የማውጣት ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚደርሰው ፡ ኪሣራና ፡ አደጋ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፩፻፸፰ ። ከመጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ የሸራ ፡ መዘርጋት ፡ የሚደርስ ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ።**

የጋራ ፡ ደኅንነትን ፡ ለመጠበቅ ፡ መርከቡ ፡ ተንሳፎ ፡ እንዲኄዝ ፡ ወይም ፡ ጥልቅ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ባሕር ፡ ለመውሰድ ፡ በሚደረግ ፡ ጥረት ፡ ምክንያት ፡ በተዘጉት ፡ ሸራዎች ፡ መበላሸት ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ በአንደኛው ፡ መሣሪያዎች ፡ መበላሸት ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ የሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ መርከቡ ፡ ከተንሳፈፈ ፡ በኋላ ፡ ለጊዜው ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ ሸራውን ፡ በማብዛት ፡ ምክንያት ፡ በመርከቡ ፤ በዕቃዎቹ ፤ በጭነቱ ፡ ወይም ፡ ከእነዚሁ ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ የደረሱ ፡ ጉዳቶች ፡ ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ አይታሰቡም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፭ ። ስለ ፡ መኪናዎችና ፡ ማፍሊያዎች ፡ መበላሸት ።**

የጋራ ፡ ደኅንነትን ፡ ለመጠበቅ ፡ በጠረፍ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበትን ፡ መርከብ ፡ በእርግጠኛ ፡ ሐሳብ ፡ ለማንሳፈፍ ፡ በመጣጣር ፡ በመርከቡ ፡ መኪናዎች ፡ ማጋያ ፡ (ማፍሊያ) ፡ ጋኖች ፡ ላይ ፡ የደረሱ ፡ ጉዳቶች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መርከቡ ፡ በመንሳፈፍ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመኪናዎቹ ፡ በሞተሮቹና ፡ በማፍሊያዎቹ ፡ ጋኖች ፡ ማደስና ፡ ማገጣጠም ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ የመጡ ፡ ጉዳቶችና ፡ ኪሣራዎች ፡ በምንም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ አይታሰቡም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። ደወ ፡ ጠረፍ ፡ የወጣውን ፡ መርከብ ፡ ለማራገፍና ፡ መልሶ ፡ ለመጫን ፡ የሚደረግ ፡ ወጪና ፡ ኪሣራ ።**

መርከቡ ፡ በጠረፍ ፡ የመቆም ፡ ግዴታ ፡ በይረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ጭነቶች ፡ ነዳጆች ፤ ስንቆች ፤ ወይም ፡ ከነዚህ ፡ አንደኛው ፡ የተራገፈ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለው ፡ ወጪ ፡ እንደጣራ ፡ ጉዳት ፡ የሚቆጠር ፡ ሲሆን ፤ ተጨማሪ ፡ የማቃለል ፡ የዕቃ ፡ ማመላለሻ ፡ ጀልባ ፡ ኪራይና ፡ እንደገና ፡ ለማስጫን ፡ ያለም ፡ ሲሆን ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎችና ፡ ይህን ፡ ለመፈጸም ፡ ለደረሱ ፡ ጉዳቶች ፡ የሚከፈለው ፡ ኪሣራና ፡ ወጪ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። እንደ ፡ ነዳጅ ፡ ሆነው ፡ ለተቃጠሉ ፡ የመርከብ ፡ ዕቃዎችና ፡ ሥንቆች ።**

መርከቡ ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ለጋራ ፡ ደኅንነት ፡ ሲባል ፡ የመርከቡን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ሥንቆች ፡ እንደ ፡ ነዳጅ ፡ ለማቃጠል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከቡ ፡ በሰፌው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ነዳጅ ፡ የያዘውና ፡ ያለቀው ፡ ነዳጅ ፡ ዋጋ ፡ መርከቡ ፡ ቢመጨረሻ ፡ ከተነሣበት ፡ ወደብና ፡ በተነሣበት ፡ ቀን ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ ሒሳብ ፡ ተመዛዝኖ ፡ የተቃጠለው ፡ ነዳጅ ፡ ዋጋ ፡ ካልተቀነሰ ፡ ቢቀር ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ አይታሰብም ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። ባንድ ፡ መጠጊያ ፡ ወደብ ፡ ለመግባት ፡ የሚደረግ ፡ ወጪ ።**

(፩) ለጋራ ፡ ደኅንነት ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ ባንድ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ የመጠጊያ ፡ ቦታ ፡ የገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በቤዛነት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ አደራረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ባደረጉ ፡ ሌሎች ፡ በራሱ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ በተጫነበት ፡ ቦታ ፡ የተመለሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ ለመግባት ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ። መርከቡ ፡ የፊተኛውን ፡ ጭነት ፡

በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ተመልሶ ፡ ይዞ ፡ የሄደ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ ትቶ ፡ ለመሄድ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ወደብ ፡ በመግባት ፡ ወይም ፡ በመመለስ ፡ ምክንያት ፡ የሚደረጉ ፡ ወጪዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተባለው ፡ በጋራ ፡ ጉዳቶች ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ።

(፪) መርከቡ ፡ ሊበጅ ፡ በማይቻልበት ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ መጠጊያ ፡ ቦታ ፡ ያለ ፡ እንደ፡ሆነና ፡ ለመበጀት ፡ ወደሚቻልበት ፡ ሌላ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ የተዛወረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውሳኔዎች ፡ በሁለተኛው ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ መጠጊያ ፡ ወደብ ፡ ተቈጥሮ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ባሉት ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፱ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ በመዛወር ፡ ምክንያት ፡ በተጨመረው ፡ ጕዞ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ባንድ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ የመጫኛ ፡ ቦታ ፡ በማረፊያ ፡ ወይም ፡ በመጠጊያ ፡ ቦታ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ጭነቱን ፡ ነዳጁን ፡ ወይም ፡ ሥንቆችን ፡ ለማራገፍ ፡ የተደረጉ ፡ ወጪዎች ፡ መጠበቁ ፡ ወይም ፡ ማራገፉ ፡ ለጋራ ፡ ደኅንነት ፡ ወይም ፡ በቤዛነት ፡ ወይም ፡ በአደጋ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ የደረሱትን ፡ ጉዳቶች ፡ ለማደስ ፡ ይህም ፡ ማደስ ፡ በጸጥታ ፡ ጕዞን ፡ ለመቀጠል ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ።

(፬) ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተጠቀሱት ፡ ለመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ለማራገፍ ፡ የሚደረጉ ፡ ወጪዎች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰቡ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መልሶ ፡ የመጫንና ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ዕቃውን ፡ የማደራጀት ፡ ወጪዎች ፡ እንዲሁም ፡ የመጋዘን ፡ ኪራይና ፡ (አርዲያ) ፡ የሚገባ ፡ ውል ፡ ላለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የጭነት ፡ የነዳጅ ፡ ወይም ፡ የሥንቆች ፡ ወጪዎች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ። መርከቡ ፡ በፍጹም ፡ የተበላሸ ፡ ወይም ፡ የመጀመሪያ ፡ ጕዞውን ፡ የማይቀጥል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጋዘን ፡ ኪራይ ፡ በጋራ ፡ ጕዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰቡት ፡ መርከቡ ፡ በፍጹም ፡ እስከ ፡ ተበላሸበት ፡ ወይም ፡ ጕዞውን ፡ እስከ ፡ ተወበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። መርከቡ ፡ ከማራገፉ ፡ በፊት ፡ በፍጹም ፡ የተበላሸ ፡ ወይም ፡ ጕዞው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህ ፡ ወጪዎች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚሆኑት ፡ ጭነቱ ፡ ተራግፎ ፡ እስካለቀበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

(፭) ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ መርከብ ፡ ጭነቱን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ጕዞውን ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ ባለበት ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ ሊታደስ ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወጪውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀነስ ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ማደሻው ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ እስከሚጓዝበት ፡ ወደብ ፡ መድረሻ ፡ ድረስ ፤ መርከቡን ፡ ጐትቶ ፡ ለመውሰድ ፡ ወይም ፡ (ይህ ፡ ቀርቶ) ፡ ጭነቱን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መርከብ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ጭነቱን ፡ ለመላክ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡

ሆነ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አደራረግ ፡ ሳይከፈለው ፡ እስከ ፡ ተገኘው ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ድረስ ፡ መርከቡን ፡ ለመገሎተት ፡ ለማሻገር ፡ ወይም ፡ ጭነቱን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ የተደረገውን ፡ ተጨማሪ ፡ ወጪ ፡ በዳነው ፡ ልዩ ፡ ወጪ ፤ መጠን ፡ የሚከፍሉት ፡ በጉዞው ፡ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። መርከቡ ፡ ቢተጠጋበት ፡ ስፍራ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ወጪና ፡ ስለ ፡ መርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ የኑሮ ፡ ወጪና ፡ ደሞዝ ።

(፩) ለካፒቴኑ ፤ ለመኰንኖቹና ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ የኑሮ ፡ ወጪ ፡ ደሞዝና ፡ አንድ ፡ መርከብ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መጠጊያ ፡ ስፍራ ፡ በመግባቱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሚነበት ፡ ስፍራ ፡ በመመለስ ፡ የተነሣ ፡ ጉዞውን ፡ ባስረዘመበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚያልቀው ፡ ነዳጅና ፡ የተከማቸው ፡ ሥንቅ ፡ ሁሉ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰበው ፡ መርከቡ ፡ ወደ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ወደብ ፡ ለመግባት ፡ የሚያወጣው ፡ ወጪ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ቢተ መለከተው ፡ መሠረት ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰብ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) የጋራ ፡ ጸጥታን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ በቤዛነት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የተለየ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ በመድረሱ ፡ የተነሣ ፡ መርከቡ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወደብ ፡ የገባ ፤ ወይም ፡ የታገደ ፡ (የተያዘ) ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ጉዞውን ፡ ለመ ቀጠል ፡ እንዲችል ፡ በአደጋና ፡ በቤዛነት ፡ ምክንያት ፡ የደረሱትን ፡ ጉዳ ቶች ፡ በማሻሻል ፡ መርከቡን ፡ ለማደስ ፡ እንዲቻልና ፡ ይህም ፡ የመታደስ ፡ ሥራ ፡ መርከቡ ፡ ጉዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ እንዲችል ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ መርከቡ ፡ ታግዶ ፡ ከቈየበት ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ደንበኛ ፡ መንገዱን ፡ ለመቀጠል ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እስከሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለመገኘት ፡ ይችል ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፤ ለካፒቴኑ ፤ ለመኰንኖቹና ፡ ለሠራተኞቹ ፡ የሚገባው ፡ የኑሮ ፡ ወጪና ፡ ደመወዝ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባል ። ነገር ፡ ግን ፡ መርከቡ ፡ በፍ ጹም ፡ የተበላሸ ፡ ወይም ፡ የቀድሞ ፡ ጉዞውን ፡ የማይቀጥል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመርከቡ ፡ መታገድ ፡ ምክንያት ፡ የሚያልፈው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ ከተበላሸበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ጉዞውን ፡ ከተወበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የጭነት ፡ ማራ ገፍ ፡ ሥራ ፡ አላለቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ካለቀበት ፡ ቀን ፡ ሊያልፍ ፡ አይችልም ።

በተለይ ፡ መርከቡን ፡ የማደስ ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ ካለቁት ፡ ነዳጆችና ፡ ሥን ቆች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ከማይታሰቡበት ፡ ወጪዎች ፡ በቀር ፡ መርከቡ ፡ ሥራውን ፡ ፈትቶ ፡ በወደብ ፡ በቆመበት ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ የሚያልቁት ፡ ነዳጆ ችና ፡ ሥንቆች ፡ ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ።

በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ከማይገቡት ፡ ለመርከቡ ፡ ማደሻ ፡ ከወጡት ፡ ወጪዎች ፡ በቀር ፡ መርከቡ ፡ በወደብ ፡ ለቈየበት ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ለወደቡ ፡ የሚከፍሉት ፡ የወደብ ፡ ወጪዎች ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባሉ ።

(፫) ይህና ፡ ሌሎቹም ፡ ቊጥሮች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለሚውሉበት ፡ ጉዳይ ፡ ደመወዝ ፡ ማለት ፡ ለካፒቴኑ ፤ ለመኰንኖቹና ፡ ለመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ ባለመርከቡ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በስምምነት ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ለጥቅማቸው ፡ ሲባል ፡ ሊከፈላቸው ፡ የሚገባውን ፡ ወጪዎች ፡ ይጠቀልላል ።

(፬) ለመርከቡ ፡ አጠባበቅ ፡ ወይም ፡ ማደስ ፡ ካፒቴኑ ፡ መኰንኖቹ ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ ስለ ፡ ፈጸሚቸው ፡ ሥራዎች ፡ ወጪ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ እንዲታሰቡ ፡ አይፈቀድም ፤ ቢሆንም ፡ በትርፍ ፡ ሰዓት ፡ ሥራ ፡ የሚከፈላቸው ፡ ዋጋ ፤ የትርፍ ፡ ሰዓት ፡ ሥራ ፡ ባያስፈልግ ፡ ኖሮ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚገባው ፡ ለሥራው ፡ የወጣው ፡ ወጪ ፡ ታስቦ ፡ ቀሪው ፡ ወጪ ፡ በጋራ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባል ።

ቊ ፡ ፪፻፸ ። ጭነቱ ፡ በሚራገፍበት ፡ ጊዜ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ።

በመጫን ፤ በማስተካከል ፤ በማራገፍ ፤ መጋዘን ፡ በማግባት ፤ መልሶ ፡ በመጫንና ፡ ቦታ ፡ በማስያዝ ፡ የተነሣ ፡ በጭነቱ ፤ በነዳጁ ፡ ወይም ፡ በሳንቆቹ ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ሁሉ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ሊገባ ፡ የሚችለው ፡ ለነዚሁ ፡ ተግባሮች ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ እንዲታሰብ ፡ የተፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፪፻፸፩ ። ከማደስ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ቅናሽ ።

ስለ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉዳት ፡ የሚከፈለው ፡ የገንዘብ ፡ ጥያቄ ፡ እንዲተካከል ፡ ሲደረግ ፡ ጉዳቱ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ እንዲታሰብ ፡ በሚፈቀድበት ፡ ጊዜ ፡ አሮጌዎቹ ፡ በአዲስ ፡ መሣሪያ ፡ እንዲተኩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚሁ ፡ እንደሚከተለው ፡ ካዲሱ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ያሮጌውን ፡ ዋጋ ፡ በመቀነስ ፡ ማስተካከል ፡ ያስፈልጋል ።

በግል ፡ ዕድሜያቸውና ፡ በአገልግሎት ፡ ዘመናቸው ፡ መሠረት ፡ ቅናሽ ፡ ከሚደረግባቸው ፡ ሥንቆች ፤ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ እንዳያልፍ ፡ የሚከላከሉ ፡ መሣሪያዎች ፤ ያደጋ ፡ ጀልባዎች ፤ ኮምፖስ ፤ ራዲዮ ፡ አቅጣጫ ፡ መፈለጊያ ፤ የሚያስተጋባ ፡ ድምፅ ፡ (የገደል ፡ ማሚቶ ) ፡ መቈጣጠሪያ ፤ ይህንንም ፡ የመሰለ ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ማፍሊያና ፡ ማጋያ ፡ በቀር ፡ ቅናሽ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ ከተመዘገበበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ አደጋ ፡ እስከ ፡ ደረሰበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የነበሩበትን ፡ ዕድሜ ፡ መገመት ፡ ያሻል ።

BACK



ካልተሠራባቸው ፡ ሥንቆች ፡ ከተቀማጭ ፡ ዕቃዎችና ፡ ከመለወጫዎች ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ቅናሽ ፡ አይደረግም ፤ አዲስ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ቅናሽ ፡ የሚደረገው ፡ ከመጠቅለ ያው ፡ መክፈቻ ፡ ዋጋ ፡ በቀር ፡ ካዲስ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ መለወጫዎች ፡ ዋጋ ፡ የሥራ ፡ አባልና ፡ የማገጣጠሚያ ፡ ዋጋ ፡ ጭምር ፡ ላይ ፡ ነው ።

የመርከቡ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ዋጋና ፡ የደረቅ ፡ ወደብና ፡ (ድራይ ፡ ዶክ)፡ የመውጫ ፡ መንገድ ፡ (ስሊፕ ፡ ዌይ ) ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ይከፈላል ።

አደጋው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ፡ ውስጥ ፡ የመርከቡ ፡ መሠረት ፡ ቀለም ፡ የተቀባ ፡ ካልሆነ ፤ መሠረቱን ፡ ለማጽ ጂያና ፡ ቀለም ፡ ለመቀቢያ ፡ ወጪ ፡ አይፈቀድም ።

ሀ/ ከ፩ ፡ ዓመት ፡ የማይበልጥ ፡ ዕድሜ ፡ ስላለው ፡ መርከብ ።

ማጽጃና ፡ የጥልቀት ፡ ምልክት፤ለማሠሪያ፡ወይም ፡የመሠረቱ ፡ መለበጃና፡ቀለም፡ መቀቢያ ፡ ሒሳብ ፡ ዋጋ ፡ ከአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ የሚቀነስ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ የተከና ወነው ፡ የማደስ ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ በሙላ ፡ ይከፈላል ።

ለ/ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ስላለው ፡ መርከብ ።

መሠረቱን ፡ ለማጽጃና ፡ ቀለም ፡ ለመቀቢያ ፡ የጥልቀት ፡ ምልክት ፡ ለማሠሪያ ፡ የሚደረገው ፡ ቅናሽ ፡ በ/ ሀ/ ፊደል ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ይሆናል ።

በተዘረጉት ፡ ሸራዎች ፤ አውታሮች ፤ ገመዶች ፤ ወፍራም ፡ ገመዶች ፤ ለመጐ ተቻ ፤ ለመሳቢያ፡ ለአቅጣጫ፡መስጫ፤ለሚያገለግሉ ፡ ገመዶች ፤ (ከሽቦና ፤ ከሰንሰ ለት ፡ በቀር ፤ ) የሸራ ፡ አጐበሮች ፤ መሸፈኛዎች ፤ ለሥንቅ ፤ ለቀለም ፡ መቀቢያ፡ ከወጡት ፡ ዋጋዎች ፡ ላይ ፡ ከአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ይቀነሳል ።

ከዕንጨት ፡ ከተሠሩት ፡ የመርከቡ ፡ አካሎች ፤ የውስጥ ፡ ፕላፎን ፤ የዕንጨት ፡ ምሰሶ ፤ ዋልታዎችና ፤ ጀልባዎች ፤ የቤት ፡ ዕቃዎች ፤ የቤት ፡ ማጌጫዎች ፤ የሸክላ ፡ ሥራዎች ፤ የብረትና ፡ የመስተዋት ፡ መሣሪያዎች ፤ ሽቦ ፡ አውታሮች ፡ የሽቦ ፡ ገመ ዶችና ፡ የሽቦ ፡ መጐተቻዎች ፤ የኮምፓስ ፡ መሣሪያዎች ፤ በአየር ፡ ራድዮ ፤ አቅጣጫ ፡ መፈለጊያ ፤ የሚያስተጋባ ፡ ድምፅ ፡ (የገደል ፡ ማሚቶ ) ፡ መቈ ጣጠሪያና ፡ እነዚህንም ፡ የመሳሰሉት ፡ መሣሪያዎች ፤ ማስተላለፊያና ፡ ማገናኛ ፡ ሽቦዎች ፤ መወጠሪያዎች ፤ የከባድ ፡ ጭነት ፡ ማንሻዎችና ፡ የኤሌክትሪክ ፡ መሥሪያዎችና ፤ መገናኛዎች ፤ እንዲሁም ፡ በኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ የማይሠሩ ፡ የማገናኛዎቹ ፡ መሣሪያዎች ፡ ዋጋ ፡ ከአንድ ፡ ስድስተኛ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሌሎቹ ፡ ክፍሎች ፡ የታደሱት ፡ ዋጋ ፡ በሙላ ፡ ይከፈላል ። የዕንጨት ፡ ሥራዎችንና ፡ ተገጣጣሚ ፡ መርከቦችን ፡ የመለበጃው ፡ ብረት ፡ ዋጋ ፡ ለሥራው ፡ ያስፈለገው ፡ የብረት ፡ መለበጃ ፡ ዋጋ ፡

በመላ ፡ ርክብደቱ ፡ ልክ ፡ እንዲከፈል ፡ ተደርጎ ፡ ካሮጌው ፡ ብረት ፡ ሽያጭ ፡ የተገኘው ፡ ዋጋ ፡ ተቀንሶ ፡ እንዲታደስ ፡ ይደረጋል ። ለምስማሮች ፡ እስር ፡ የሚነጠፍ ፡ ጨርቅ ፡ (ፌልት) ፡ የተደረገ ፡ ለብረቱ ፡ ማጋጠሚያ ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ከአንድ ፡ ሦስተኛው ፡ ይቀነሳል ።

## ሐ/ ከ፫ ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ስላለው ፡ መርከብ ።

ከዕንጨት ፡ የተሠራው ፡ የመርከቡ ፡ አካልና ፡ የውስጥ ፡ ፕላሮን ፤ የዕንጨት ፡ ምሰሶዎች ፤ ዋልታዎችና ፡ ጀልባዎች ፤ የቤት ፡ ዕቃዎች ፤ የቤት ፡ ማጌጫዎች ፤ ዋጋ ፡ ከአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ የሚቀነስ ፡ ሆኖ ፡ ከብረታ ፡ ብረት ፡ የተሠሩ ፤ ምሰሶና ፤ አግዳሚ ፤ እንዲሁም ፡ ከሁሉም ፡ ዐይነት ፡ መኪናዎች ፡ (ማፍያዎችና ፡ ግጣማቸው) ፡ ዋጋ ፡ ጭምር ፡ አንድ ፡ ስድስተኛው ፡ የሚቀነስ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ የሚደረገው ፡ ቅናሽ ፡ ሁሉ ፡ እላይ ፡ በ„ለ„ ፊደል ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## መ/ ከ፮ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ስላላቸው ፡ መርከቦች ።

አውታሮች ፡ ሌሎች ፡ ገመዶች ፤ የመርከቡን ፡ ሚዛንና ፡ አቅጣጫ ፡ መስጫ ፡ ሽቦ ፡ መጐተቻ ፡ ወፍራም ፡ ገመዶች ፤ የብረት ፡ ምሰሶና ፡ ‘ ልታዎች ፤ ኮምፓስ ፤ ራዲዮ ፤ የአቅጣጫ ፡ መፈለጊያ ፤ የሚያስተጋባ ፡ ድምፅ ፡ (የገደል ፡ ማሚቶ) ፡ መቈጣጠሪያና ፡ እነሱንም ፡ የመሳሰሉት ፡ መሣሪያዎች ፡ የኤሌክትሪክ ፡ ኀይል ፡ ማቋረጫዎች ፤ ተጨማሪ ፡ መኪናዎች ፤ መርከቡን ፡ መሪ ፡ የክብደት ፡ ማንሻዎች ፡ ማገናኛዎችና ፡ ሌሎችንም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ መወጠሪያዎችና ፡ (ማፍያዎችና ፡ የግጣማቸው ፡ ዋጋ ፡ ጭምር) ፡ ከአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ የሚቀነስ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ዕድሜ ፡ ላይ ፡ ስላሉ ፡ መርከቦችም ፡ የሚደረገው ፡ ቅናሽ ፡ በ „ሐ„ ፊደል ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## ሠ/ ከ፲ ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ስላላቸው ፡ መርከቦች ።

ከብረት ፡ የተሠራ ፡ የመርከቡ ፡ አካል ፤ ማገጣጠምያ ፡ ማስተላለፊያ ፡ ሽቦዎች ፡ ዋጋ ፡ በአንድ ፡ ስድስተኛ ፡ የሚቀነስ ፡ ከመሆኑና ፡ የመልሕቆች ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ የሚከፈል ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ለመለዋወጫዎች ፡ የተደረገው ፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

## ረ/ ከ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ መርከቦች ።

የማስተላለፊያ ፡ ሽቦዎች ፡ ዋጋ ፡ በአንድ ፡ ስድስተኛ ፡ የሚቀነስና ፡ የመልሕቆች ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ የሚከፈል ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ የተደረገው ፡ መለወጫ ፡ ዋጋ ፡ በአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ይቀነሳል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፪ ። ለጊዜው ፡ የተደረገ ፡ የመርከብ ፡ መታደስ ።**

(፩) ዕቃ ፡ በሚጫንበት ፤ መርከብ ፡ በሚያርፍበት ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ መጠጊያ ፡ በሚገኝ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ደኅንነት ፡ ወይም ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ቤዛነት ፡ ሲባል ፡ ለደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ለጊዜው ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ማደሻዎች ፡ የተደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የነዚህ ፡ የማደስ ፡ ሥራዎች ፡ ዋጋ ፡ በጋራው ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

(፪) በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፤ ለማደሻው ፡ ወጪ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንዲታሰብ ፡ የሚፈቀደው ፡ ለሌላ ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ በጊዜው ፡ የተደረገውን ፡ ቁጠባ ፡ መሠረት፡ አድርጎ ፡ በመያዝ ፡ ሳይሆን ፡ መርከቡ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሳይታደስ ፡ ቢቀር ፡ ኖሮ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ጉዳት ፡ ወጪ ፡ ይደረግ ፡ የነበረው ፡ ሒሳብ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መታሰቡ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ ወጪ ፡ የሆነው፡ ሒሳብ ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝነት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፫) በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ ለሆኑት ፡ ለጊዜው ፡ ለማደሻ ፡ ከወጡት ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፡ አሮጌዎቹ ፡ በአዲስ ፡ መሣሪያ ፡ እንዲተኩ ፡ ሲባል ፡ ለሚደረግ ፡ ወጪ ፡ ቅናሽ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፫ ። ለመርከብ ፡ ኪራይ ፡ የተቈረጠው ፡ ዋጋ ፡ ስለ ፡ መጥፋቱ ፡ (መክሠር) ።**

ለጋራ ፡ ጉዳቱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ጥፋቱ ፡ ወይም ፡ ጉዳቱ ፡ ራሱ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ከሆነ ፡ ከመርከቡ ፡ ጭነት ፡ ወይም፡ ጉዳት ፡ የተነሣ ፡ በመርከቡ ፡ ጭነት ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ነው ። ከጠፋው ፡ ጠቅላላ ፡ የመርከብ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ኪራዩን ፡ ለማግኘት ፡ ቢፈልግ ፡ ኖሮ ፡ ሊያ ወጣው ፡ የነበረው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከቤዛነቱ ፡ የተነሣ ፡ ሳያወጣ ፡ የቀረው ፡ ገንዘብ ፡ ያገኝ ፡ ከነበረው ፡ ጠቅላላ ፡ የመርከብ ፡ ኪራይ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ መቀነስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፬ ። በዕቃው ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ የቤዛነት ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰበው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ።**

(፩) በንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ የቤዛነት ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ በጋራ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሚታሰበው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ በደረሰው፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ በዕቃው ፡ ባለሀብት ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ኪሣራ ፡ መርከቡ ፡ ጭነቱን ፡ ባራገፈበት ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ በነበረው ፡ የገበያ ፡ የዕለት ፡ ዋጋ ፡ መሠረት፡ ወይም፡ የጕዞ ፡ ዓላማው ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ተነሣበት ፡ ስፍራ ፡ ሳይደርስ ፡ ዕቃዎቹ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ የተራገፉ ፡ ሲሆኑ ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ በሚያወጡት ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ጉዳት ፡ የደረሰባቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ እንደዚሁ ፡ የተሸጡ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የጉዳቱን ፡ ጠቅላላ ፡ ዋጋ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የሚወስን ፡ ስምምነት ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚገባው ፡ ሒሳብ ፡ የሚታሰበው ፡ ዕቃው ፡ ከመርከቡ ፡ በሚራገፍበት ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ጕዞው ፡ ባንድ ፡ ሌላ ፡ ቦታ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሽያጩ፡ ከሚገኘው ፡ ገንዘብና ፡ ዕቃዎቹ ፡ ባላቸው ፡ የተጣራ ፡ ዋጋ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የገንዘብ ፡ ልዩነት ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፪፻፸፫ ። ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሚከፈል ፡ ድርሻ ፡ አወሳሰን ።

(፩) ለጋራ ፡ ጉዳት፡የሚደረግ ፡ የርዳታ ፡ ድርሻ ፡ አከፋፈል ፡ የሚወሰነው ፡ ንብረቶቹ ፡ በጕዞው ፡ መድረሻ ፡ ስፍራ ፡ ባላቸው ፡ እርግጠኛና ፡ እውነተኛ ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ የቤዛነት ፡ ጉዳት ፡ለደረሰባቸው ፡ ንብረቶች ፡ የተከፈለው ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ አስቀድሞ ፡ አልተደመረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ከተደመረ ፡በኋላ፡ የሠራተኞቹ ፡ ወጪና ፡ ደመወዝ ፤ እንዲሁም ፡ በጋራ ፡ አደጋ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ተግባር ፡ በደረሰበት ፡ ዕለት ፡ መርከቡና ፡ ጭነቱ ፡ በፍጹም ፡ ጠፍቶ ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ የጭነቱን ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ ወጪ ፡ ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ ገንዘብና ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ፡ ያልገቡትንም ፡ ሌሎች ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ለመርከቡ፡አከራይ ፡ ከሚደርሱት ፡ የጭነትና ፡ የተሳፋሪዎች ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ በማድረግ ፡ነው፤ እንዲሁም ፡ የጋራ ፡ አደጋ ፡ አስተሳሰብ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገው ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ የተደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ከጋራ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው፡ ከሚታሰቡት ፡ በቀር ፡ ከንብረቶቹ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ ደረሰኝ ፡ የሌላቸው ፡ የመንገደኞቹ ፡ ጓዞችና ፡ የግል ፡ ዕቃዎች ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተካፋይ ፡ አይሆኑም ።

(፫) በመርከቡ፡ላይ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ መሣሪያዎችና ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ የደረሰው፡ ጉዳት ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚገባው ፡ እነዚህን ፡ ጉዳቶች ፡ ለማደስ ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ የሚያስፈልገው ፡ እርግጠኛ ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፸፩፡ የተመለከተው ፡ አስፈላጊ ፡ ቅናሽ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ጉዳቱም ፡ አልታደሰ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጉዳቱ ፡ ማደሻ ፡ ከተገመተው ፡ የማደሻ ፡ ወጪ ፡ ሳይበልጥ ፡ በየጊዜው ፡ ለመሣሪያው ፡ ዋጋ ፡ የሚቀነስ ፡ ተገቢ ፡ ሒሳብ ፡ ይፈቀዳል ።

## ቍ ፡ ፪፻፸፬ ። መርከቡ ፡ ስለሚያገኘው ፡ ጉዳት ።

በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተግባር ፡ ምክንያት ፡ ተበላሽቷል ፡ ወይም ፡ ጠፍቷል ፡ የሚያሰኝ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የሚታሰበው ፡ ቤዛነቱ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ መርከቡ ፡ ከነበረው ፡ ዋጋ ፡ ላይ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ የማይገቡትን ፡ የማደሻ ፡ ገንዘብ ፡ ግምት ፡ ወይም፡ (ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ) ፡ በሽያጭ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀናሽ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የሚተርፈው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፮ ። መግለጫ ፡ ያልተደረገባቸው ፡ ወይም ፡ በትክክል ፡ ያልተገለጹ ፡ የንግድ፡ ዕቃዎች ።**

ዕቃዎቹ ፡ በተጫኑበት ፡ ጊዜ ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ሳያ ውቀው ፡ በተጫኑትና ፡ ሆን ፡ ተብሎ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ በተሰጣቸው ፡ የንግድ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የደረሱ ፡ ኪሣራዎችና ፡ ጉዳቶች ፡ በጋራ ፡ አደጋ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ፡ ገብተው ፡ አይታሰቡም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከአደጋ ፡ እንዲድኑ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ። አዲስ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ በትክክል ፡ ባልተገለጹ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ በተሰጣቸው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጉዳቱ ፡ የሚከፈላቸው ፡ በመግለጫው ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ ከእውነተኛው ፡ ዋጋቸው ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ ተገልጸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእውነተኛው ፡ ዋጋቸው ፡ መሠረት ፡ ለጋራው ፡ ጉዳት ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፯ ። በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ የሚታሰብ ፡ ኮሚሲዮን ።**

(፩) ለካፒቴኑ ፤ ለመኰንኖቹና ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ከሚከፈለው ፡ ደሞዝና ፡ የኑሮ ፡ ወጪዎች ፤ በጕዞው ም ፡ ጊዜ ፡ ላልተተኩት ፡ ነዳጆችና ፡ ሥንቆች ፡ ከሚወ ጡት ፡ ገንዘቦች ፡ ሌላ ፤ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ በመቶ ፡ ፪ ፡ የሚከፈለው ፡ ኮሚሲዮን፡ በዚሁ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሊታሰብ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ገን ዘብ ፤ ለአከፋፈል ፡ ተሳታፊ ፡ እንዲሆኑ ፡ ከሚገደዱት ፡ ጥቅሞች ፡ በኩል ፡ ሳይ ከፈል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ሒሳብ ፡ በውል ፡ መርከብን ፡ አስይዞ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ብድር ፡ ለማግኘት ፡ የተደረ ገው ፡ መደበኛ ፡ ወጪና ፡ እንዲሁም ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ሲባል ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ቻቸው ፡ የተሸጠባቸው ፡ ባለሀብቶች ፡ በጋራ ፡ ጕዳት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ የጥ ቅሙ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ወጪ ፡ እንዲውል ፡ በቅድሚያ ፡ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ በኢ ንሹራንስ ፡ ለማስቀመጥ ፡ የተደረገ ፡ ወጪ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ይታሰባል።

**ቍ ፡ ፪፻፸፰ ። በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ወጪ ፡ ስለ ፡ ተከፈሉ ፡ ገንዘቦች ፡ ወለድ ።**

ይህ ፡ የጋራ ፡ ጉዳቱ ፡ ሒሳብ ፡ እስከ ፡ ተከፈለበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በጋራ ፡ ጉዳት፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ በገቡት ፡ ወጪዎችና ፡ ለቤዛነት ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አበል ፡ ወጪ፡ ለሆኑት ፡ ገንዘቦች ፡ ሕጋዊ ፡ ወለድ ፡ የሚከፈለው ፡ ባመት ፡ በመቶ ፡ ፫ ፡ ሲሆን ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሂሳብ ፡ ከመከፈያው ፡ በፊት ፡ ወጪውን ፡ መክፈል ፡ ካለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተቀማጭ ፡ ከሆነው ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ የተከ ፈለው ፡ ሂሳብ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፹ ። የተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ አያያዝ ።**

(፩) ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ወጪዎች ፡ ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ለጭነቱ ፡ ክፍያ ፡ መድን ፡ ለማድረግ ፡ ተቀ

ማጨ ፡ ገንዘብ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ የተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘቦች ፡ የመርከቡ ፡ አደራጅ ፡ በመረጠው ፡ አንድ ፡ እንደራሴና ፡ አስቀማጮቹ ፡ በሾሙት፡አንድ ፡ እንደራሴ ፡ ስም ፡ እነሱ ፡ በመረጡት ፡ ባንክ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ የጋራ ፡ ሒሳብ ፡ ተከፍቶ ፡ አንድም ፡ ቀን ፡ ሳይሰጥ ፡ ወዲያውኑ ፡ መከፈል ፡ አለባቸው ።

(፪) ይህ ፡ ተቀማጭ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከነወለዱ ፡ ከጋራ ፡ ጉዳቱ ፡ ወይም ፡ ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ከማዳኑ ፡ ተግባር ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑት ፡ ወይም ፡ ገንዘቡ ፡ ተቀማጭ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ በሚከፍላቸው ፡ ወጪ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ለማረጋገጫ ፡ ዋስትና ፡ ይሆናል ። የየድርሻ ፡ አደላዳይ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በጽሑፍ ፡ በሚሰጠው ፡ ምስክርነት ፡ ለተቀማጭነት ፡ የተመደበውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ወይም ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ። እነዚህ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ክፍያዎች ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መመለስ ፡ ተግባሮች ፡ የሚፈጸሙት ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ያለባቸውን ፡ የመጨረሻ ፡ አላፊነቶች ፡ ሳይነኩ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፩፻፹፩ ። የጋራ ፡ ጉዳትን ፡ በየድርሻው ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ መቻል ።

የጋራው ፡ ጉዳት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በቀጥታ ፡ አደጋ ፡ ሊደርስባቸው ፡ የነበሩት ፡ መርከቡ ፤ የመርከቡ ፡ ጭነት ፡ ኪራይ ፤ የመሳፈሪያ ፡ ዋጋ ፤ ጭነቱና ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፷፰ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፤ ይደርሳል ፡ በሚባለው ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ የጋራውን ፡ ጉዳት ፡ እንደ ፡ ድርሻቸው ፡ መጠን ፡ መቻል ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፩፻፹፪ ። ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ መዋጮ ፡ ለማድረግ ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ስላለመቀበል ።

የበዓል ፡ ቀኖች ፡ ሳይቈጠሩ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ በተሰጡበት ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ፡ በካፒቴኑ ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲወሰኑ ፡ ካልተደረጉ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ በጋራ ፡ ጉዳት ፡ መዋጮ ፡ ለማድረግ ፡ የቀረበ ፡ ጥያቄ ፡ ተቀባይነትን ፡ አያገኝም ።

ቍ ፡ ፩፻፹፫ ። ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ፡ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት።

(፩) ከጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፤ ከአደጋ ፡ ከዳኑት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ተካፋይ ፡ በሆኑበት ፡ መጠን ፡ መብታቸውን ፡ በቀዳሚነት ፡ ለማስጠበቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) መርከቦችን ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ይህ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ የተጻፉትን ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፡ በሚመለከቱ፡ ደንቦች ፡ ይመራል ።

(፫) ወደፊት ፡ ለሚደረገው ፡ ድርሻ ፡ አከፋፈል ፡ መልካምና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የተገመተ ፡ ዋስትና ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ የሚጸናባቸውን ፤

ንብረቶች ፡ በሚደርሱበት ፡ መጨረሻ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ አመላላሹ ፡ ሊይዛቸው ፡ ይችላል። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ እነዚህ ፡ ንብረቶችና ፡ የሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲከፈል ፡ በተወሰነው ፡ ድርሻ ፡ ልክ ፡ እንዲያዙ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፬) የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ብዙዎች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት፡ ያገኙበት ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራቸው ፡ የሚመደበው ፡ በግልብጦሽ ፡ አቈጣጠር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፩ ። የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ አመዳደብ ።**

በጋራ ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ስለሚታሰበው ፡ ኪሣራም ፡ ሆነ ፡ ለጉዳቱ ፡ ተካፋይ ፡ ለሚኮንበት ፡ ዕዳ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጥቅም ፡የሚደርሰው ፡ ሒሳብ ፡ የሚመደበው ፡ ጕዞው ፡ በሚያልቅበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የንብረት ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ በማድረግና ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ የመጨረሻው ፡ መድረሻ ፡ እንዲሆን ፡ በተወሰነው ፡ ስፍራና ፡ እዚህ ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ተደረሰ ፡ ወዲያውኑ ፡ ንብረቱ ፡ ያለውን ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። አከፋፋዮች ።**

(፩) የጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሒሳብ ፡ አደረጃጀት ፡ የሚፈጸመው ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ አከፋፋዮች ፡ ነው ። ባለጕዳዮቹ ፡ በእነዚህ ፡ አከፋፋዮች ፡ አመራረጥ ፡ ባይስማሙ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አከፋፋዮችን ፡ ለመሾም ፡ ይችላል። እነዚህም፡ አከፋፋዮች ፡ ከመረጧቸው ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ እርዳታን ፡ ለመቀበል ፡ ይችላሉ ።

(፪) ባለጕዳዮቹ ፡ የጋራ ፡ ጉዳትን ፡ ሒሳብ ፡ ድርጅት ፡ ያልተቀበሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለባለጕዳዮቹ ፡ የሚገባ ፡ ጥሪ ፡ ከተላከ ፡ በኋላ ፡ ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሚያደርገው ፡ ጥያቄ ፡ የጋራውን ፡ ሒሳብ ፡ ድርጅት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያጸድቀው ፡ ያቀርባል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። ወጪዎችና ፡ የሥራ ፡ ዋጋዎች ።**

የጋራ ፡ ጉዳትን ፡ ሒሳብ ፡ ለማቋቋም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ወጪዎችና ፡ የሥራ ፡ ዋጋዎች ፡ ከድርሻዎቹ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ በቀደምትነት ፡ ይነሣሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። ስለ ፡ ድርሻ ፡ አከፋፈል ፡ የሚደረግ ፡ ክስ ፡ ይርጋ ።**

(፩) ስለ ፡ ድርሻ ፡ አከፋፈል ፡ የሚደረገው ፡ ክስ ፡ መርከቡ ፡ ከወደቡ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ መድረስ ፡ ይገባው ፡ ከነበረው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፪) በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ አከፋፋዮቹን፡ በመምረጥ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ ይቋረጣል ። አከፋፋዩ ፡ ወይም ፡ አከፋፋዮቹ፡ ሥራ

ቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ አንችልም ፡ ብለው ፡ ከገለጹበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ የሚቈይ ፡ አዲስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ ይጀመራል ።

## አንቀጽ ፡ ፺ ።

## ስለ ፡ ኢንሹራንስ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የኢንሹራንስ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፰ ። የዚህ ፡ ደንብ ፡ አፈጻጸም ፡ ወሰን ።**

ዋናው ፡ ዓላማ ፡ በባሕር ፡ የሚደርሰውን ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተጨማሪ ፡ የሆኑትን ፡ አደጋዎችም ፡ ለማረጋገጥ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ማንኛውም ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይመራል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፱ ። የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፎርም ።**

(፩) የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ (ፖሊሲ) ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) መጀመሪያ ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የሚደረጉት ፡ ተጨማሪ ፡ ነገሮችና ፡ መለዋወጦች ፡ ሁሉ ፡ በጽሑፍ ፡ መደረግ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፪፻፺ ። ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የሚደረግ ፡ ተቀዳሚ ፡ ስምምነት ፡ (ከቨርኖት) ።**

ውሉ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ በጽሑፍ ፡ ማስታወሻ ፡ የተደረገ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ከቨርኖት) ፡ ተዋዋዮቹን ፡ ያስገድዳቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፩ ። በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ሊነገር ፡ የሚገባው ።**

(፩) በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ (ፖሊሲ) ፡ ውስጥ ፡ መገለጥ ፡ ያለበት ፡

(ሀ) የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ የተፈረመበት ፡ ቦታ ፤

(ለ) የተፈረመበት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፤

(ሐ) የተዋዋዮቹ ፡ ስምና ፡ ደንበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፤ አስፈላጊ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ መሆኑንም ፤

(መ) ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ እከፍላለሁ ፡ ብሎ ፡ የገባባቸው ፡ አደጋዎች ፤ ኢንሹራንስ ፡ የተገባበት ፡ ነገር ፤

(ሠ) በኢንሹራንስ ፡ የተጠበቀው ፡ ጕዞ ፡ ወይም ፡ ጊዜ ፡ (ወይም ፡ ሁለቱም) ፤

(ረ) ኢንሹራንስ ፡ የተገባበት ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤

(ሰ) ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የሚከፈለው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፤

(ሸ) ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ለአምጪው ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ነው ።

(፪) ውሉን ፡ የሚፈርመው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ነው ። ተዋዋዮቹ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የውሉን ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ በራሳቸው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲቀበሉ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

ቊ ፡ ፪፻፺፪ ። ኢንሹራንስ ፡ ሊደረግላቸው ፡ የሚቻል ፡ ነገሮች ።

(፩) ግባቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ለሆነው ፡ የገንዘብ ፡ ግምት ፡ ዋጋ ፡ ላላቸውና ፡ ሊደርስ፡የሚችል ፡ የባሕር ፡ አደጋ ፡ ለሚያስፈራቸው ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሊደረግላቸው ፡ ይቻላል ።

(፪) በባሕር ፡ አደጋ ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ማንም፡ሰው፡ በኢንሹራንስ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

ቊ ፡ ፪፻፺፫ ። በኢንሹራንስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ስለ ፡ መግባት ።

ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ላደረገላቸው ፡ ነገሮች ፡ ራሱ ፡ በሌላ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለመግባት ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪፻፺፬ ። በመሠራት ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ መርከብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ስለ ፡ ማስገባት ።

በመሠራት ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ መርከብ ፡ መሠራቱ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ ወዲያውኑ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለማስገባት ፡ ይቻላል ።

ቊ ፡ ፪፻፺፭ ። መርከቡን ፡ በሚመለከት ፡ ሁኔታ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉት ፡ አደጋዎች ፡ አቈጣጠር ፡ መጀመሪያ ።

(፩) መርከቡን ፡ በሚመለከት ፡ ሁኔታ ፡ የጕዞ ፡ አስፈሪ ፡ አደጋዎች ፡ የሚጀመሩት ፡ የሸቀጥ ፡ ዕቃዎች ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ መጫን ፡ ከጀመሩበት፡ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ሸቀጦቹ ፡ እስከሚራገፉበት ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ የመንገድ ፡ አስፈሪ ፡ አደጋዎች ፡ መርከቡ ፡ ወደ ፡ መድረሻው ፡ ከደረሰበት፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ በዚያው ፡ በደረሰበት ፡ ቦታ ፡ ለሌላ ፡ አዲስ ፡ ጕዞ ፡ ሸቀጥን ፡ መጫን ፡ ከጀመረበት ፡ ከ፲፭ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሊያልፉ ፡ አይችሉም ።

(፪) መርከቡ ፡ ጥልቀት ፡ ወዳለው ፡ ባሕር ፡ የሚጓዝ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በመንገድ ፡ ላይ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ አደጋዎች ፡ አቈጣጠር ፡ ጊዜዎች ፡ መርከቡ ፡ የቆመበትን ፡ ቦታ ፡ በለቀቀበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ መልሕቁን ፡ ባነሣበት ፡ ጊዜ ፡ ተጀምረው ፤ በመድረሻው ፡ ወደብ ፡ መልሕቁን፡ በጣለ ፡ ወይም ፡ ባሰረ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጸማሉ ።

ቊ ፡ ፪፻፺፮ ። በጕዞ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኘው ፡ መርከብ ።

(፩) የተደረገው ፡ የመርከብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ አደጋዎች ፡ ለሚጀመሩበት ፡ ወይም ፡ ለማይቈጠሩበት ፤ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ፡አደጋዎች ፡ ለመቈጠር ፡ የሚጀምሩት ፡ ከጕዞው ፡ መጨረሻ ፡ አንሥቶ ፡ ወይም ፡ ተራዝሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ጕዞው ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

BACK



(፪) ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ አደጋዎች ፡ ለመቈጠር ፡ የሚጀምሩበት ፡ በመርከቡ ፡ ጕዞ፡ መጨረሻ ፡ ሲሆን ፤ ባልተሄደበት ፡ ጊዜ ፡ መጠን ፡ ለኢንሹራንሱ ፡ የተከፈለው፡ ዋጋ ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉ ፡ አደጋዎች ፡ ጊዜ ፡ ተራዝሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተጨማሪው ፡ ጊዜ ፡ መጠን ፡ ለኢንሹራንሱ ፡ ዋጋ ፡ በተጨማሪ ፡ ይከፈላል ።

## ቊ ፡ ፪፻፺፯ ። የሸቀጦችን ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ ስለ ፡ መወሰን ።

(፩) የሸቀጦቹ ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ በውሉ ፡ ያልተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ሸቀጦቹ ፡ በተገዙበት ፡ ዋጋ ፤ የግዢው ፡ ዋጋ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ሸቀጦቹ ፡ በተጫኑበት፡ ጊዜና ፡ በተጫኑበት ፡ ቦታ ፡ በነበረ ፡ የጊዜ ፡ ዋጋና ፡ ደግሞ ፡ እስከ ፡ ባሕሩ ፡ ዳር፡ ድረስ ፡ በተከፈለው ፡ ቀረጥና ፡ በወጣው ፡ ኪሣራ ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ በተገኘው ፡ የመርከብ ፡ ኪራይ ፡ ዋጋ ፤ እንዲሁም ፡ ለኢንሹራንስ ፡ በተከፈለው፡ ዋጋና ፡ ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተስፋ ፡ ተደርጎበት ፡ በነበረው ፡ ትርፍ ፡ መሠረት፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ግምቱ ፡ የሚወሰነው ፡ በመድረሻቸው ፡ ቦታና ፡ በሚደርሱበት ፡ ቀን ፡ ዋጋ ፡ ነው ። ሸቀጦቹ ፡ ያልደረሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ የተባለው ፡ ግምት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ግምት ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ ሸቀጦቹ ፡ ሊደርሱ፡በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ይገመታል ።

## ቊ ፡ ፪፻፺፰።በንግዱ፡ ዕቃዎች፡ ላይ፡ ሊደርሱ፡ የሚችሉ፡አደጋዎች፡ አቈጣጠር፡መጀመር።

በንግዱ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉት ፡ አደጋዎች ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምሩት ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገቡለት ፡ በጕዞ ፡ ቦታ ፡ መነሻ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ለአመላላሹ ፡ ከተሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። ከተራገፉበት ፡ አንሥቶ ፡ ከሠላሳ ፡ ቀን ፡ ለማለፍ ፡ ሳይቻልና ፡ በጕዞው ፡ ማለቂያ ፡ ቦታ ፡ ለተቀባዩ ፡ በተሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ ይፈጸማሉ ።

## ቊ ፡ ፪፻፺፱ ። ውሉን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የተጀመረውን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሁሉ ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ።

(፪) ለኢንሹራንሱ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በጊዜው ፡ ያልተከፈለና፡ኢንሹራንስ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ በሕያ ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እንዲከፍለው ፡ ማስጠንቀቂያ፡ ከላከለት ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ የማፍረስ ፡ ችሎታ ፡ ይኖረዋል ።

(፫) የውሉ ፡ መፍረስና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ የሚደረገው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ወይም ፡ በቴሌግራም ፡ ሊደረጉ ፡ ይችላሉ ።

(፬) የሚከፈሉት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራዎች ፡ ሳይነኩ ፤ የውሉ ፡ መፍረስ ፤ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ (ሪስክ) ፡ ከተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ ባልደረሱት ፡ ጊዜዎች ፡ መጠን ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ከተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ተመላሽ ፡ ያደርጋል ።

(፭) ኢንሹራንስ፡ የገባው፡ ሰው፡ ያልከፈለውን፡ የኢንሹራንስ፡ ዋጋ፡ሦስተኛው፡ወገን፡ ከከፈለ ፡ ማንኛውም ፡ አደጋ ፡ ከመድረሱና ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ፡ ማስታወቂያ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ቢተላለፊለት ፡ ቢቅን ፡ ልቡና ፡ ተጠቃሚ ፡ ቢሆን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ፡ ውጤት ፡ አይኖረውም።

(፮) ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ቢከሠረ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው፡ እንደዚሁ፡ ያሉ ፡ መብቶች ፡ ይኖሩታል ።

ቍ ፡ ፫፻ ።ስላለመግለጽና ፡ አሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ሳይገልጽ ፡ መቅረቱ ፡ ወይም ፡ አስተኛ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ መስጠቱ ፡ ምንም ፡እንኳ፡ በማታለል ፡ መንፈስ ፡ የተደረገ ፡ ባይሆን፡ ለመድረስ ፡ በሚያሠጉ ፡ አደጋዎች ፡ (ሪስክ) ፡ ላይ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ የሚቀንሱ ፡ ከሆኑ ፤ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ የሚያፈርሱ ፡ ናቸው ።

(፪) ሳይገለጽ ፡ መቅረቱ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የተሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ኢንሹራንስ፡በተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ፡ ባይገኝም ፡ እንኳ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የማታለል ፡ ሐሳብ ፡ አሳይቶ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በኢንሹራንስ ፡ የተከፈለው፡ ዋጋ ፡(ፕሬሚየም) ፡ በሞላው ፡ የማታለል፡ መንፈስ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቢግማሽ ፡ የኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ገንዘብ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይቀራል ።

ቍ ፡ ፫፻፩ ። ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ መክበዱ።

(፩) የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ በሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው፡ አደጋ ፡ የከበደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ እንዳወቀ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ካላስታወቀ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ የአደጋው ፡ መክበድ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊ፡ የተነገረው ፡ እንደ፡ ሆነና፡ ይህም ፡ የአደጋ ፡ መክበድ ፡ የደረሰው ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው፡ሰው ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንሱ ፡ ገንዘብ ፡ ለርሱ ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ ወዲያውኑ ፡ ውሉን ፡ መሻር ፡ ወይም ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጨመር ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል። አደጋው ፡ የከበደው ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ግን ፡ ገንዘቡን ፡ በመጨመር ፡ ኢንሹራንሱ ፡ ይቀጥላል ።

ቍ ፡ ፫፻፪ ። ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ መፍረስ ።

ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር፡ ካልጀመረ ፡ ኢሹራንስ ፡ ቢተደረገለት ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ ዘወትር ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

BACK



ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ ያፈረሰው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ለመሆኑ፡ ማስረዳት ፡ ካልቻለ ፤ በኪሣራ ፡ ስም ፡ ለኢንሹራንስ፡ አድራጊው ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ዋጋ ፡ (ፕሬሚየም) ፡ ግማሽ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፡፡

### ኢንሹራንስ ፡ የገባውና ፡ የኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡፡

**ቍ ፡ ፫፻፫ ፡፡ የደረሱትን ፡ ጉዳትና ፡ መጥፋት ፡ ኢሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ስለ ፡ መቻሉ ፡፡**

ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፤ በማዕበል፡ በመስጠም ፤ መሥመርን፡በመሳት ፤ በመጋጨት ፤ ጭነቱን ፡ በመጣል ፤ በቃጠሎ ፤ በመፈንዳትና ፡ በጠቅላላው ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ በሚደርሱ ፡ አደጋዎች ፡ ሁሉና ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ የሚደርሱ ፡ ጉዳቶችና ፡ መጥፋት ፤ በኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ላይ ፡ የሚወድቁ ፡ ይሆናሉ ፡፡

**ቍ ፡ ፫፻፬ ፡፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ሲባል ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተገባባቸው ፡ ዕቃዎች ፡፡**

ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ ከኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አደጋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ የሚከፈል ፡ ድርሻ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ኀላፊ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፫፻፭ ፡፡ አስገዳጅ ፡ በሆነ ፡ የመንገድ ፡ መለወጥ ፡ ምክንያት ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውጤት፡ ስላለመቅረቱ ፡፡**

(፩) በአስገዳጅ ፡ ምክንያት ፡ የመንገዱ ፡ ጕዞ ፡ ወይም ፡ መርከብ ፡ ቢለወጥ ፤ እንደ ሁም ፡ በካፒቴኑ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ሠራተኞች ፡ ጥፋት ፡ የሆነ ፡ ቢሆንም ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉ ፡ አደጋዎች ፡ የተደረገ ፡ ኢንሹራንስ ፤ እንደ ጸና ፡ ይቈያል ፡፡

(፪) የመርከቡ ፡ አከራይ ፡ የመረጠው ፡ ካፒቴን ፡ ባደረገው ፡ የአታላይነት ፡ ወይም፡ የተንኰል ፡ ጠባይ ፡ ባላቸው ፡ ጥፋቶች ፡ ምክንያት ፡ በመርከቡ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ኢንሹራንስ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ ኀላፊ ፡ አይሆንም ፡፡

**ቍ ፡ ፫፻፮ ፡፡ በአስገዳጅ ፡ ምክንያት ፡ የመንገድ ፡ መለወጥን ፡ የሚመስሉ ፡ ሁኔታዎች ፡፡**

አከራዩ ፡ ወይም ፡ኢሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የጕዞው ፡ መንገድ ፡ እንዲለወጥ ፡ ሳይጠይቅ ፡ ቀርቶ ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ ለማዳን ፡ ወይም ፡ ለመርዳት ፡ ሲል ፡ ካፒቴኑ ፡ የመርከቡን ፡ ጕዞ ፡ ወይም ፡ መርከቡን ፡ የለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአስገዳጅ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ተለወጠ ፡ ጕዞ ፡ ይቈጠራል ፡፡

**ቍ ፡ ፫፻፯ ፡ ጕዞን ፡ ስለ ፡ ማሳጠር ፡፡**

(፩) የመነሻ ፡ ወይም ፡ የመድረሻ ፡ ወደብ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ለማረፊያ ፡ የተወሰነ፡ ወደብ ፡ ከሆነ ፡ ጕዞው ፡ በማጠሩ ፡ የመርከቡ ፡ ጕዞ ፡ እንደ ፡ ተለወጠ፡ አይቈጠርም፡፡

(፪) ጉዞው ፡ ወይም ፡ መንገዱ ፡ የተለወጠው ፡ በፈቃድ ፡ ሲሆን ፡ በተስማሙበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ መድረሱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫፻፳ ፡ ሌሎች ፡ የጉዞ ፡ የመንገድ ፡ ወይም ፡ የመርከብ ፡ መለወጥ ፡ ጉዳዮች ።**

ማናቸውም ፡ የጉዞ ፡ የመንገድ ፡ ወይም ፡ የመርከብ ፡ መለወጥ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የተገመተው ፡ አደጋ ፡ መድረስ ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፡ ወዲያውኑ ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንሱ ፡ የተሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡(ፕሬሚየም)፡ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው፡ ለራሱ ፡ አስቀርቶ ፡ እንዲሁም ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ዕዳ ፡ ከመክፈል ፡ ነጻ ፡ ይሆናል።

**ቍ ፡ ፫፻፱ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ጥፋቶች ፡ ስለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፤ በኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ላይ ፡ አላፊነት ፡ ስለ ፡ አለመኖሩ ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፰ ፡ ከተነገረው ፡ በቀር ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በሠራተኞቹ ፡ ወይም ፡ በእንደራሴዎቹ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እነሱ ፡ መብት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ተግባሮች ፡ ወይም ፡ ጥፋቶች ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፤ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ አላፊ ፡ አይደለም ።

(፪) ከዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ በአታላይነት ፡ ወይም ፡ በተንኰል ፡ ሥራ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ አያስከፍልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፲ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ የራሱ ፡ ጒድለት ።**

(፩) አንድ ፡ የመርከብ ፡ ትጉ ፡ አከራይ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያውቀው ፡ ወይም ፡ ሊከለክለው ፡ የማይችለው ፡ የተደበቀ ፡ የመርከቡ ፡ የራሱ ፡ ጒድለት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገለት፡ዕቃ ፡ ጒድለት ፡ ወይም ፡ ዐይነት ፡ የሚደርሱ ፡ ጉዳቶችና ፡ መጥፋት ፡ እንዲሁም ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የሚሆነው ፡ መቀነስና ፡ መጉደል ፡ በኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ኀላፊነት ፡ ላይ ፡ አይወድቅም ።

(፪) በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገ፡ ጊዜ፡ የምርመራ ፡ ምስክር፡ ወረቀት፡ አለመኖር ፡ በመርከቡ፡ ላይ ፡ የተደበቀ ፡ ጒድለት ፡ እንደ ፡ አለበት ፡ ያስቈጥራል ።

(፫) እንዲሁም ፡ የዕቃው ፡ አጠቃለልና ፡ አጠባበቅ ፡ በቂ ፡ አለመሆን ፡ ዕቃውን ፡ የራሱ ፡ ጒድለት ፡ እንዳለበት ፡ ያስቈጥረዋል ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፩ ። ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ በሌሎች ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ስለማያደርጋቸው ፡ ጉዳቶች ።**

ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ በሌሎች ፡ ንብረቶችና ፡ ሰዎች፡ ላይ ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ጉዳቶች ፡ ኢሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ አላፊ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፪ ። በጦርነት ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉትን ፡ አደጋዎች ፡ ስለ ፡ ማስወገድ ።**

(፩) እርስ ፡ በርስ ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ ጋራ ፡ በሚደረገው ፡ ጦርነት ፡ ሊደርሱ ፡ የሚችሉት ፡ አደጋዎች ፡ በኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ላይ ፡ አላፊነት ፡ አያመጡም ።

BACK



(፪) ስምምነት ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በጦርነት ፡ መፈንዳትና ፡ በጠቅላላውም ፡ በናቸውም ፡ በጦርነትና ፡ በባሕር ፡ ወንበዴነት ፡ ምክንያት ፡ በማናቸውም ፡ መንግሥትና ፡ ባለሥልጣን ፡ በጥላቻ ፡ ብድር ፡ መበመለስ ፡ በመያዝ ፤ በማስያዝ ፤ በማቆም ፤ በማሳገድ ፤ ወይም ፡ በማንገላታት ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተገባላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደርሱት ፡ ጉዳዮች ፡ መጥፋቶች ፡ ሁሉ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፫፻፲፫። ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ዋጋ፡ ግምት ፡ ለሚበልጥ ፡ ገንዘብ፡ የተደረገ ፡ የስምምነት ፡ ውል ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ዋጋ ፡ ግምት ፡ ለሚበልጥ ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ የኢንሹራንስ፡ ስምምነት ፡ ውል ፤ አታላይነት ፡ ወይም ፡ ተንኰል፡ ያለበት፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ጥያቄ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ። የኢንሹራንሱም ፡ ገንዘብ ፡ ለርሱ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) አታላይነት ፡ ወይም ፡ ተንኰል ፡ የሌለበት ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ውሉ፡ የጸና፡ ይሆንና ፡ ኢንሹራንስ፡ አድራጊውም፤ በበላጭነት ፡ ከሚከፈለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ግማሹን ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቊ ፡ ፫፻፲፬ ። ከዕቃው ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ የተደረገ ፡ ኢንሹራንስ ።

ለዕቃው ፡ የተከፈለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ዋጋ ፡ ከዕቃው ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ በሆነ ፡ ግምት፡ የሆነ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ስለ ፡ ልዩነቱ ፡ ራሱ ፡ ኢንሹራንስ፡ አድራጊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቈጥሮ ፡ ለሚደርሱት ፡ መጥፋቶችና ፡ ጉዳቶች ፡ በመጠኑ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናል ።

ቊ ፡ ፫፻፲፭ ። ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ በብዙ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ የሚጠበቅ ፡ ሲሆን ፤

ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው ፡ አደጋ፡በብዙ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ የተጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋራ ፡ የአንድነት ፡ ኀላፊነት ፡ ሳይኖረው ፡ ተገዳጅ ፡ የሚሆነው፡ ኢንሹራንስ ፡ ባደረገው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ብቻ፡ነው።

ቊ ፡ ፫፻፲፮ ። ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ ላይ ፡ በመብቶቹ ፡ ስለሚሠራበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ የሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገለት ፡ ሰው ፡ ተንኰል ፡ ሳይሆን ፡ ብዙ፡ ኢንሹራንስ ፡ ተደርጎበት ፡ እንደ ፡ ሆንና ፡ እነዚህም ፡ የተከማቹት፡ ኢንራንሶች ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ግምት ፡ የሚበልጡ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር፡ እሱ ፡ በመረጠው ፡ ተራ ፡ እያንዳንዱ ፡ ኢንሹራንስ ፡

አድራጊ ፡ ገንዘቡ ፡ በኢንሹራንስ ፡ በሚጠበቅበት ፡ መጠንና ፡ በደረሰው ፡ ጉዳት፡ ልክ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑት ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ ላይ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ በመብቶቹ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ኢንሹራንስ፡ ገቢው፡ የገባባቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውሎች ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊዎች ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ እያወቀ ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫ ፡ የሰጠ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ሲጠይቅ ፡ እያንዳንዱ ፡ ውል ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፬) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ኢንሹራንሱ ፡ ለመግባት ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ (ፕሬሚየም ) ፡ ለያንዳንዱ ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊ ፡ ቀሪ፡ ይሆንለታል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፲፫። ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ከጠፉ ፡ ወይም ፡ ከቦታው ፡ ከደረሱ፡ በኋላ ፡ የተደረገ ፡ ውል ።</u>

(፩) ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ከጠፉ ፡ ወይም ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ በነበረበት ፡ ቦታ ፡ የዕቃዎቹ ፡ መጥፋት ፡ ወይም፡መድረስ ፡ ወሬ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ፊርማውን፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ ውሉ ፡ በተፈረመበት ፡ ቦታ ፡ የመጥፋቱ ፡ ወይም፡ የመድረሱ ፡ ወሬ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) «ቢጠፋም፡ ባይጠፋም» ፡ በሚል ፡ መሠረት ፡ የኢንሹራንሱ፡ ስምምነት ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ የሚሆነው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ዕቃው፡ ለመጥፋት ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ዕቃው ፡ ለመድረሱ ፡ ለማወቃቸው ፡ አስረጂ ፡ ለማቅረብ ፡ የቻሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ መሥራቱ ፡ የተረጋገጠበት ፡ ወገን ፡ ስምምነቱ ፡ የተደረገበትን ፡ የኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ (ፕሬሚየም) ፡ ዕጥፍ ፡ የሚሆን ፡ ኪሣራ ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ ይከፍላል ።

(፬) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ መጥፋቱ፡ የተነገረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ ቢጣም ፡ በሚያፋጥን ፡ ዘዴ ፡ ትእዛዙን ፡ ለማገድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ያላደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፲፬ ። ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ የሚደርሱ ፡ ጉዳቶች ።</u>

ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ያወቀው ፡ ወይም ፡ ለማወቅ ፡ የሚችለው ፡ ነገር፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ውሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ ለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ኢንሹራንስ፡ አድራጊው ፡ አላፊ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፫፻፲፱ ። ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ ጉዳቶች ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እንደ፡ ተጀመረ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ገንዘብ ፡ (ፕሬሚየም) ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ማድረጉ ።

ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ ጉዳቶች ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ገቢ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፳ ። ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።

ስለ፡ደሱረት፡አጋጣሚ፡ሁኔታዎች፡በኢንሹራንስ፡አድራጊው፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማ ቅረብ፡የሚቻል፡ሲሆን ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የደረሱትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ካወቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሚከተሉት ፡ ሦስት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ለኢንሹ ራንስ ፡ አድራጊው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፳፩ ። ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የሚያደርጋቸው ፡ የአጠባበቅ ፡ ጥንቃቄዎች ።

ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ መርከቡን ፡ ስለ ፡ መተው ፡ ያለውን ፡ መብቱን ፡ ሳያጣ ፡ ኢንሹራንስ፡የተደረገላቸውን፡ዕቃዎች ፡ በመጠበቅ ፡ ወይም ፡ ከአደጋ ፡ የማዳንን ፡ ተግባር ፡ በማድረግና ፡ አላፊ ፡ በሆኑትም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ሊቀርቡ ፡ የሚችሉትን ፡ መብቶቹን ፡ በመጠበቅ ፡ የአጠባበቅ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ ሁሉ ፡ ማድ ረግ ፡ አለበት ። ኢንሹራንስ፡አድራጊውም ፡ በበኩሉ ፡ ኀላፊነትን ፡ ወይም ፡ ባለ ቤት ፡ ነው ፡ መባልን ፡ ሳያስከትል ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ ለማድረግ ፡ ይች ላል ።

ቍ ፡ ፫፻፳፪ ። ግዴታዎችን ፡ ባለመፈጸም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ አላፊነት ።

ኢንሹራንስ፡የገባው ፡ ሰው፡ በቍጥር ፡ ፫፻፳ና ፡ ፫፻፳፩ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታ ዎች ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፳፫ ። ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ መብቶች ፡ የኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መዳረግ ።

የጠፉትን ፡ ወይም ፡ የተበላሹትን፡ዕቃዎች ፡ የከፈለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊ፡ አላፊ ፡ በሆኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ ጉዳት ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ባሉት ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ ተግባሮች ፡ ለመሥራት ፡ ተዳራጊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፳፬ ። ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረጉ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውሎች ።

(፩) ኢንሹራንስ፡ የተገባላቸው ፡ዕቃዎች ፡ «ተዘዋዋሪ» ፡(ፍሎቲንግ) ፡ ወይም፡«እንደ፡ አስፈላጊነቱ » ፡ በሚባሉ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውሎች ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ ጸንቶ ፡ ባለበት ፡ ጊዜና ፡ በዕቃዎቹም ፡ ላይ፡ የሚፈጸም ፡ ከሆነ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ የጭነት ፡ ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ እንዲሁም ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ስም ፡

ወይም ፡ እሱ ፡ ኢንሹራንስ ፡ እንዲገባላቸው ፡ አደራ ፡ ባሉት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች፡ ስም ፡ የተላኩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ በነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ኢን ሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ጥቅም ፡ ካለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መቀበል ፡ አለ በት ።

(፪) ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ የዕቃውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ለኢንሹራንስ፡ አድራጊው ፡ ከመላኩ ፡ በፊት ፡ ለደረሱትና ፡ ለዐወቃቸው ፡ አደጋዎች ፡ ቢሆ ንም ፡ እንኳ ፡ የትነሡትን ፡ ዕቃዎች ፡ ጉዞ ፡ የሚመለከቱ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በደረሱት ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ የዕቃውን ፡ ማስታ ወቂያ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ልኮ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው፡ ስም ፡ የሚላኩት ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ የተጠበቁ፡ ናቸው። በኢትዮጵያ ፡ ወደቦች ፡ መካከል ፡ ለሚደረጉት ፡ ጉዞዎች ፡ ይህ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ፡ ከሦስት ፡ ቀኖች ፡ ያለፈ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፫) ማስታወቂያ ፡ የተላከው ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ዕቃዎች ፡ የተላኩት ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሲሆን ፡ ኢንሹራንስ፡ ለገባው ፡ ወይም፡ ለ፫ኛው ፡ ወገን፡ በቍጥር፡ ፫፻፲፮ና፡ ፫፻፲፯ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ውጤት ፡ የሚኖረው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፳፩ ። በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጥቅም ፡ ሳይገልጹ ፡ ስለ፡ መቅረት ።</u>

(፩) በቍጥር፡ ፫፻፳፬፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በዕቃው ፡ ላይ፡ ያለውን ፡ ጥቅም ፡ ሳይገልጽ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ከሚከፍ ለው ፡ ገንዘብ ፡ በቀር ፡ ይኸንኑ ፡ ገንዘብ ፡ የሚተካከል ፡ ኪሣራ ፡ ማስታወቂያ፡ ስላልተላከላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ይከፍላል ።

(፪) መግለጫ ፡ ያለመስጠቱ ፡ ከባድነት ፡ ወይም ፡ መደጋገም ፡ የተደረገው ፡ በፈ ቃድ ፡ መሆኑን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል። ከዚህም ፡ በቀር ፡ መጀመሪያ ፡ መግለጫ ፡ ሳይላ ክለት ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ቢተላኩት ፡ ሸቀጦች ፡ ላይ ፡ ለደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ኢን ሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የከፈለውን፡ ገንዘብ ፡ ከዚህ ፡ በላይ፡ እንደ ፡ ተመለከተው፡ ከሚከፈለው ፡ ኪሣራ፡ ሌላ፡ እንዲመለስለት ፡ በተጨማሪ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል።

<u>ቍ ፡ ፫፻፳፯። ሀብትነታቸው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ የሆኑ ፡ መርከቦች ፡ መጋጨት ፡ ወይም ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ።</u>

(፩) ኢንሹራንስ ፡ በተደረገለት ፡ መርከብና ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ሌላ ፡ መር ከብ ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ ወይም ፡ ከአደጋ ፡ የማዳን ፡ ወይም ፡ የመርዳት ፡ ተግ

BACK



ባር ፡ ሲሆን ፤ በሁለቱም ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚመሩት ፡ ሁለ ቱም ፡ መርከቦች ፡ ሀብትነታቸው ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ መርከብ ፡ አከራዮች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፪) በመጥፎ ፡ አመራር ፤ አመራርን ፡ በመተው ፡ ወይም ፡ ደንቦችን ፡ ባለመጠበቅ ፡ ግጭት ፡ ሳይኖር ፡ እንዲሁም ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገለት ፡ መርከብና ፡ ሀብትነቱ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በሆነ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ወይም ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ መካከል ፡ በሚደረገው ፡ ግጭት ፡ ለሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ ይፈጸማል ።

(፫) ሸቀጦቹ ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ የጫነው ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ ይኸንኑ ፡ መር ከብ ፡ የገጨው ፡ ወይም ፡ ርዳታ ፡ የሰጠው ፡ መርከብ ፡ ሀብትነታቸው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ከሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተወሰነው ፡ ይፈጸማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የጉዳቶች ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈል ።

### ክፍል ፡ ፩ ። ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፯ ። ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ የኪሣራ ፡ ልክ ።**

ኢንሹራንስ፡ አድራጊው ፤ ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገለት፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ በማናቸውም፡ ሁኔታ ፡ የበለጠ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ወይም፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ መልሶ ፡ እንዲሠራ ፡ ወይም ፡ እንዲተካ ፡ ሊገደድ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፰ ። ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የሚያቀርባቸው ፡ ማስረጃዎች ።**

(፩) ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ የሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ መድረሳቸውንና ፡ እንዲሁም ፡ ኪሣራዎችንና ፡ ጉዳቶችን ፡ ወይም ፡ መርከቡን ፡ እንዲተው ፡ የሚያደርግ ፡ ምክ ንያት ፡ መኖሩን ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

(፪) የመጥፋትና ፡ የጉዳቶች ፡ ወይም ፡ መርከቡን ፡ የመተው ፡ መብት ፡ አቋም ፡ የሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገ በት ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ተደረጉ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ አድራጊውም ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ እንዲችል ፡ እነዚህ ፡ ጕዳዮች ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት፡ ጉዳቶች፡ በተደረገው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ አለመግባታቸውን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

(፬) ስለ ፡ ሆነም ፡ የኢንሹራንስ፡ ውል፡ የተደረገው ፡ በተለይ ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉ ፡ አደጋዎች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ አደ ጋው ፡ የደረሰው ፡ ከነዚሁ ፡ አደጋዎች ፡ ባንዱ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

BACK



ቊ ፡ ፫፻፷፱ ። ስለ፡ካሣ ፡ አከፋፈል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) የኢንሹራንሱ ፡ ካሣ ፡ የሚከፈለው፡ አስረጂ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶችና ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ የመርከቡን ፡ መልቀቅ ፡ ( መተው ) ፡ ተግባር ፡ በጽሑፍ ፡ የሚያመለ ክት ፡ ማስታወቂያ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ከተሰጠበት ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊውን ፡ ለመክሰስ ፡ አይቻልም ።

(፪) በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስምምነት ፡ ሊደረግ ፡ ካልቻለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ሰነዶቹን ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ክፍል፡ ፪ ።

በደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ መጠን ፡ ኪሣራን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

ቊ ፡ ፫፻፸ ። በደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ መጠን ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፈልበት፡ሁኔታ ።

(፩) ለደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ወይም ፡ ኪሣራዎች ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ መርከቡን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ ሳይለቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ኪሣ ራዎቹ ፡ የሚከፈሉት ፡ በደረሱት ፡ ጉዳቶች ፡ መጠን ፡ ነው ።

(፪) መርከቡን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ የመልቀቅ ፡ ሥራ ፡ ወደው ፡ እስከ ፡ ተቀበሉት፡ ወይም ፡ ይጸናል ፡ እስኪባል ፡ ድረስ ፡ ኢንሹራንስ፡የገባው ፡ ሰው ፡ ለደረሰበት፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መርከቡን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ በመልቀቅ ፡ ከሚያገኘው ፡ ገንዘብና ፡ በደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ከሚከፈለው ፡ ኪሣራ ፡ አንዱን ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ።

(፫) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ መርከቡን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ የመተው ፡ መብት ፡ በደረሰው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ የመከፈልን ፡ መብት ፡ አይሰጥም ። የዚህም ፡ ዐይነት ፡ አከፋ ፈል ፡ ሊደረግ ፡ የሚቻለው ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ዐይነት ፡ ከኢንሹራንሱ ፡ ውል፡ ጋራ ፡ የማይጋጭ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፫፻፸፩ ። ኢንሹራንስ፡የተደረገለትን ፡ ዕቃ ፡ በቀጥታ ፡ ለሚነኩ ፡ ጉዳቶች ፡ የኢን ሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ግዴታ ፡ አወሳሰን ።

ኢንሹራንስ፡ አድራጊው ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ በሚ ደርሱት ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሥራ ፡ በማጣት ፡ በዕቃው ፡ መዘግ የት ፡ በዋጋ ፡ መለዋወጥ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ በሚደርሰው ፡ መሰናክልና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለሚደርሱት ፡ የግል ፡ ጉዳቶች፡ ኣላፊ ፡ አይሆንም ።

ቊ ፡ ፫፻፸፪ ። ከአዲሱ ፡ ላይ ፡ አሮጌውን ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።

መርከቡን ፡ ወይም ፡ መለወጫዎቹን ፡ ለማደስ ፡ የሚደረገው ፡ ወጪ ፡ በልዩነት ፡ ከአዲሱ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የአሮጌውን ፡ ዋጋ ፡ መቀነስን ፡ ያስከትላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፫፻፴፫ ። የሠራተኞች ፡ ደመወዝና ፡ ጥቅም ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ የማ ይታሰብ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

የሠራተኞችን ፡ ደመወዝ ፡ ጥቅምና ፡ ማናቸውንም ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ መርከቡ ፡ አያያዝ ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪና ፡ ሠራተኞቹ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ የሚመለሱበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሌሎች ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ መርከቡን ፡ ኢንሹራ ንስ ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ መክፈል ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። በተጫኑት ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ሁኔታ ።**

በተጫኑት ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ስለ፡ደረሰው ፡ መበላሸት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ፡ የሚከፈለው ፡ የተበላሹት ፡ ዕቃዎች ፡ በሚያወጡት ፡ ዋጋና ፡ ከመበላሸታቸው ፡ በፊት ፡ ያወጡ ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ በማመዛዘን ፡ ሆኖ፡ ኢንሹራንሱም ፡ የሚከፈለው ፡ በነዚሁ ፡ ዋጋዎች ፡ መካከል ፡ የተገኘውን ፡ ልዩ ነት ፡ ተቀናሽ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፭ ።የጋራ ፡ ጉዳት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የሚከፍለው ፡ ድርሻ።**

የጋራ ፡ ጉዳት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ የሚከፈለውን ፡ ኪሣራ ፡ ኢንሹራንስ፡ ባደረገው፡ ዕቃ፡ዋጋ፡መጠን ፡ ኢንሹራንስ፡ አድራጊው፡ መቻል ፡ አለበት።ስለ፡ሆነም፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ከከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የበለጠ ፡ ሳይሆን ፡ በተለይ ፡ ኢንሹራንስ፡አድራጊው ፡ ራሱ ፡ መቻል ፡ ላለበት ፡ ጉዳቶች ፡ የሚከፍላቸው ፡ ኪሣ ራዎች ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ከሚከፍላቸው ፡ ኪሣራዎች ፡ ላይ ፡ ይቀነሱለታል ።

## ክፍል ፡ ፫ ። ስለ ፡ መተው ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፮ ። የመተውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

ተቃራኒ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ በተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለትን ፡ ዕቃ ፡ ለመ ተው ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፯ ። መርከብ ፡ ስለሚተውባቸው ፡ ሁኔታዎች ።**

መርከቡን ፡ ለመተው ፡ የሚቻለው ፡—

(፩) መርከቡ ፡ በሙሉ ፡ ሲጠፋ ፤

(፪) መርከቡ ፡ በፍጹም ፡ ለመታደስ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡

(፫) ለማደስ ፡ ወደሚቻልበት ፡ ቦታ ፡ ለመውሰድ፡ ካልተቻለ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ የማደሻ ፡ መሣሪያዎች ፡ ባለመገኘታቸው ፡ ለማደስ ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፤

(፬) በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ስለ፡ደረሰው ፡ መበላሸት ፡ ለመርከቡ ፡ ማደሻ ፡ የሚያስፈል ገው ፡ ጠቅላላው ፡ ገንዘብ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከመርከቡ ፡ ዋጋ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ የሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

BACK



የሒሳቡም ፡ አደራረግ ፡ አሮጌው ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ ሲለወጥ ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ አሮጌ ፡ ከሆኑት ፡ መጣሪያዎች ፡ ዋጋ ፡ ጋራ ፡ በማመዛዘንና ፡ በርግጥ ፡ ተበላሽተው ፡ ከተ ገኙት ፡ ነገሮች ፡ ጋራ ፡ ቀጥታ ፡ ግንኙነት ፡ የሌለውን ፡ የወጪ ፡ ገንዘብ ፡ ሒሳብ ፡ ሁሉ ፡ ባለማሰብ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፴፰ ። ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) ዕቃዎችን ፡ ለመተው ፡ የሚቻለው ፡—

(ሀ) እነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ በሙሉ ፡ ሲጠፉ ፡ ወይም ፡ ሲበላሹ ፤

(ለ) መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ በማይችልበት ፡ ጊዜ ፡ ጭነቱ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ማመላለሻ ፡ ዘዴ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ጕዞውን ፡ ሳይጀምር ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የአራት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ የመርከቡን ፡ ጕዞ ፡ መቀጠል ፡ አለመቻል ፡ ካስታወቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ይህ ፡ የመርከቡ ፡ ጕዞ ፡ ለመቀጠል ፡ አለመቻል ፡ መገናኛ ፡ በተቋረጠበት ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚቈጠረው ፡ ጊዜ ፡ የመገናኛው ፡ መቋረጥ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ይረዝማል ።

(ሐ) መርከቡ ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ ዕቃዎቹ ፡ የሚበላሹ ፡ ሲሆኑ ፡ በዚሁ ፡ ምክ ንያት ፡ ዕቃዎቹ ፡ እንዲሸጡ ፡ የታዘዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(መ) ማናቸውም ፡ ወጪ ፡ ሳይታሰብ ፡ የነዚህ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ፡ ሒሳቡ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፩ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ሲደረግ ፡ ከዋጋቸው ፡ ግምት ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ የሚደርስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በፊደል ፡ (ሀ) (ለ) (መ) በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆንና ፡ ኢንሹራንስም ፡ የተ ደረገው ፡ በተለይ ፡ ምክንያቶች ፡ ለሚደርሱ ፡ ጉዳቶችና ፡ ኪሣራዎች ፡ ብቻ ፡ የተ ወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ጉዳቱ ፡ ከነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ከአንዱ ፡ የተወለደ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዕቃዎቹን ፡ መተው ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፫፻፴፱ ። የመርከብን ፡ ኪራይ ፡ ስለ ፡ መተው ።

በቍጥር ፡ ፫፻፴፰ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በ (ለ) ፊደል ፡ በተነገረው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ ዕቃዎቹ ፡ ጕዞዋቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ለማድረግ ፡ ያሳየውን ፡ ትጋት ፡ በማ ስረዳት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተከፋይ ፡ ያልሆነውን ፡ የመርከብ ፡ ኪራይ ፡ የተወ ፡ መሆ ኑን ፡ የመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ለማስታወቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፵ ። በወሬ ፡ መጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የሚደረግ ፡ የመተው ፡ ተግባር ።

(፩) የመጨረሻ ፡ ወሬ ፡ ከደረሰ ፡ እንሥቶ ፡ የመርከቡ ፡ ወሬ ፡ ሳይሰማ ፡ አራት ፡ ወር ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መርከቡን ፤ ሸቀጦቹን ፡ የመርከቡን ፡ ኪራይ ፡ ለመ ተው ፡ ይቻላል ።

BACK



(፪) መገናኛዎች ፡ በተቋረጡ ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ የሚቈጠረው ፡ ጊዜ ፡ የመገናኛው ፡ መቋረጥ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ይራዘማል ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ የመጨረሻው ፡ ወሬ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መርከቡ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ በኋላ ፡ ወደሚደርስበት ፡ በታ ፡ አለመድረሱን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፬) መርከቡ ፡ የጠፋው ፡ የመጨረሻው ፡ ወሬ ፡ በተሰማበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ።

(፭) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በባሕር ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ አደጋ ፡ ጠፋ ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ አመዛዝኖ ፡ በሚፈርደው ፡ በሁለቱ ፡ ዐይነት ፡ አደጋዎች ፡ መካከል ፡ የሚደርሰውን ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለማከፋፈል ፡ ሁኔታዎቹን ፡ በመመልከትና ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ በማለት ፡ አስፈላጊውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ችሎታ ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ መርከቡን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ ስለ ፡ መተው ።

(፩) በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ዕቃ ፡ ባንድ ፡ መንግሥት ፡ የተማረከ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ የተጎዳ ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡ ወንበዴዎች ፡ የተነጠቀ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ በአራት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ ያልተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርከቡን ፡ ወይም ፡ ሸቀጦቹን ፡ ለመተው ፡ ይቻላል ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ አጋጣሚውን ፡ ሁኔታ ፡ ካስታወቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ይኸው ፡ ጊዜ ፡ መቆጠር ፡ የሚጀመር ፡ ይሆናል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከቱትና ፡ በሸቀጡ ፡ ላይ ፡ ከደረሱት ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ የተነሣ ፡ በአራት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኪራዩን ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለትን ፡ የመርከብ ፡ ኪራይ ፡ ለመተው ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። ተቀባይነት ፡ የሌለው ፡ መተው ።

በቍጥር ፡ ፫፻፴፰ ፡ (፩) (ለ) ፫፻፴፱ ፡ ፫፻፵ና ፡ ፫፻፵፩ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፡ የመርከብ ፡ ጭነት ፡ መጀመርና ፡ መጓዝ ፡ የመርከቡ ፡ ወሬዎች ፡ መድረስ ፡ ወይም ፡ የተማረኩት ፡ የተያዙት ፡ ወይም ፡ የተጎዱት ፡ ዕቃዎች ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ መመለስ ፡ በእነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውጭ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፱ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ የተደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መተውን ፡ ተቀባይነት ፡ የሌለው ፡ ያደርገዋል ። እነዚሁ ፡ ሁኔታዎች ፡ የደረሱት ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መተው ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፫ ። የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ማለቅ ፡ የሚቃወም ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊ ።**

ኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) (ለ) ፫፻፹፱ ፡ ፫፻፺ና ፡ ፫፻፺፩ ፡ እንደተመለከተው ፡ ጊዜው ፡ ያለቀ ፡ ላለመሆኑ ፡ መከራከር ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማስታወቂያ ፡ በደረሰው ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ መከራከሪያውን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፬ ። ስለ ፡ መርከቡ ፡ ጭነት ፡ ኪራይ ፡ ልዩ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሁኔታዎች ።**

በቍጥር ፡ ፫፻፹፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር፡ (፩) (ለ) ፫፻፺ና ፡ ፫፻፺፩፡በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ስለ ፡ ሽቀጡ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ለሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ ለሽቀጡ ፡ ኪራይ፡ልዩ ፡ ኢንሹራንስ፡ተደርጎ፡እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፺፪ና ፡ ፫፻፺፫ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ይህን ፡ የመርከብ ፡ የጭነት ፡ ኪራይ ፡ የከፈለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተወሰነው ፡ጊዜ፡ሲያልቅ ፡ ከኢንሹራንስ ፡ አድራጊው፡ካሣን፡ለማግኘት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፭ ። ስለ፡መተው ፡ ዐይነት ።**

መተው ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በገደብ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፮ ። ያደረጋቸውን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወቅ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ግዴታ ።**

(፩) መተውን ፡ ሲያስታውቅ፡ኢንሹራንስ ፡ የገባው፡ሰው፡ የገባባቸውን ፡ ሌሎች ፡ ኢንሹራንሶች ፡ ሁሉ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ አንድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢሹራንስ ፡ ጥቅምን ፡ ያጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፯ ። የመተው ፡ ውጤቶች ።**

(፩) እሺ ፡ የተባለበት ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነ ፡ መተው ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለትን ፡ ገንዘብ ፡ ራሱ ፡ በመክፈል ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገላቸውን ፡ ዕቃዎች፡ ባለሀብትነት ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ያስተላልፍለታል።

(፪) በኢንሹራንስ፡አድራጊውና፡ኢንሹራንስ፡በገባው፡ሰው፡መካከል ፡ ባሉት፡ግንኙነቶች፡ ውስጥ ፡ የመተው ፡ ውጤቶች ፡ የሚጀመሩት ፡ መተውን ፡ ያስከተለው፡ ሁኔታ ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ይርጋ ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፰ ። ከኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ የሚመነጭ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ ይርጋ ።**

ከኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ የሚመነጩ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ፡መብቶች፡ሁሉ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፵፱ ። ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ (ፕሬሚየም) ፡ አከፋፈል ፡ ክስ ።

የኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ (ፕሬሚየም) ፡ አከፋፈልን ፡ የሚመለከተው ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ የውሉ ፡ ስምምነት ፡ ተቀባይነትን ፡ ካገኘበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፶ ። ስለ ፡ መተው ፡ ተግባር ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።

ስለ ፡ መተው ፡ ተግባር ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ —

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፴፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) (ለ) ፫፻፴፱ ፡ ፫፻፵ና ፡ ፫፻፵፩ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፤ በነዚሁ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከሚያልቅበት ፡ አንሥቶ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ መርከቡ ፡ የማይጓዝበትን ፡ የተማረከበትን ፤ የተያዘበትን ፡ ወይም ፡ የታገደበትን ፡ ካወቀበት ፡ አንሥቶ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ አድራጊው ፡ ማስታወቂያ ፡ እስከ ፡ ሰጠበት ፡ ቀን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ተቀንሶ ፡ ነው ።

(፪) በቍጥር ፡ ፫፻፴፰ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) (ሐ) እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፡ ሽያጩ ፡ ከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። ስለ ፡ ደረሰ ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።

ስለ ፡ ደረሰ ፡ የጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ —

(፩) ይህን ፡ ክስ ፡ የማቅረቡ ፡ ጕዳይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ በርዳታ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ባልታሰቡ ፡ ልዩ ፡ ወጪዎች ፡ ከውል ፡ ወይም ፡ ከአጥፊነት ፡ በመነጨ ፡ ኀላፊነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፤ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ሰው ፡ ክሱን ፡ ካቀረበበት ፡ አንሥቶ ፡ እንዲህም ፡ ካልሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ኪሣራውን ፡ ከከፈለው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፤

(፪) በቍጥር ፡ ፫፻፵፩ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሲሆን ፤ በቍጥር ፡ ፫፻፶ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) እንደ ፡ ተጠቀሰው ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፪ ። በመርከቡና ፡ በመርከቡ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መነሻ ።

በመርከቡና ፡ በመርከቡ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ለሚያሠጋው ፡ አደጋ ፡ ስለ ፡ መርከብ ፡ መተውና ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ጉዳት ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ የተደረገ ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለመተው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ለጋራ ፡ ጉዳት ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። በሸቀጦቹና ፡ በሸቀጦቹ ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚያሠጋ ፡ አደጋ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መነሻ ።

ልዩ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተደረገላቸው ፡ በሸቀጦችና ፡ በሸቀጦች ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡

BACK



ይደርሳሉ ፡ ተብለው ፡ ለሚያሠጉት ፡ አደጋዎች ፡ የመተመና ፡ የጉዳት ፡ ክስ ፡ የይርጋ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ የተ ደረገ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ መርከቡ ፡ ከወደቡ ፡ ከሚደርስበት ፡ ቀን ፡ ወይም፡ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ሊደርስበት ፡ ይገባው ፡ ከነበረው ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ለመተው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ለጉዳት ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ የደረ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፲፻፶፩ ። ያለ ፡ አገባብ ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ይርጋ።

በአንድ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ እንዲመለስ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ከተከፈለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

ቊ ፡ ፲፻፶፪ ። ይርጋው ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ፡ ተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ ይርጋው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሱ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በተከለከሉና ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸው ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

ቊ ፡ ፲፻፶፫ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ መቋረጥ ።

መደበኛ ፡ ከሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፳፱ ፡ የተወሰነውን ፡ በመ ፈጸም ፡ የአቤቱታውን ፡ አስረጂ ፡ ሰነዶች ፡ በመስጠት ፡ ይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ ይቋረጣል ። በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ሲያልፍ ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድ ራጊው ፡ ሰነዶቹን ፡ የመለሰው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ለቀ ረው ፡ ጊዜ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ መቈጠሩን ፡ ይቀጥላል ።

## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## የወንጀል ፡ ድንጋጌዎች ።

ቊ ፡ ፲፻፶፬ ። በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ መርከቡ ፡ እንዲፈተሽ ፡ በማድረግ ፡ ባለሀብቱን፡ ስለ ፡ መጉዳት ።

በመርከቡ ፡ ባለሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስበት ፡ በማቀድ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያለ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መርከቡ ፡ እንዲፈተሽ ፡ በማድረግ ፡ መርከቡን ፡ ከጕዞው ፡ ያሰና ከለ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ከ፪ሺ ፡ የኢት/ ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጫ ፡ ይቀጣል ።

ቊ ፡ ፲፻፶፭ ። በመጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ምክንያት ፡ በሰው ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ በመርከብ ፡ ላይ፡ የአደጋ ፡ ሥጋት ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።

ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ካፒቴን ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ መር ከብ ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ መርከበኛ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ተግባሩን ፡ በማጓደል ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ በስካር ፡ ምክንያት ።

(ሀ) መርከቡ ፡ በድንገት ፡ እንዲጠፋ ፡ እንዲበላሽ ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ እንዲደርስበት ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ እንዲደርስባቸው ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡—

(ለ) መርከቡ፡ በድንገት ፡ እንዳይጠፋ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ወይም፡ ከፍተኛ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስበት ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ አባሎች ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ በተሳፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ አካል ፡ ላይ ፡ አሥጊ ፡ የሆነውን ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ለመከላከል ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ከ፪ሺ ፡ የኢት/ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

## ቊ ፡ ፫፻፶፱ ። ጠቅላላ ፡ ወንጀሎች ።

በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ የተቀጠረ ፡ ማንኛውም ፡ መርከበኛ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከተመለከቱት ፡ ጥፋቶች ፡ አንደኛውን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚከተሉት ፡ ቅጣቶች፡ ይቀጣል ።

(ሀ) የመርከቡን ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ ኋደኛውን ፡ ወይም ፡ በምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተረጋገጠለትን ፡ የመርከቡን ፡ እንጂኔር ፡ የመታ ፡ (የደበደበ) ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(ለ) የተሰጠውን ፡ ሕጋዊ ፡ ትእዛዝ ፡ አልቀበልም ፡ በማለት ፡ ሥራውን ፡ ለመተው ፡ ወይም ፡ መርከቡ ፡ እንዳይጓዝ ፡ ወይም ፡ ጉዞውን ፡ እንዳይቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ ከማንኛቸውም ፡ ከመርከበኛ ፡ አባል ፡ ጋራ ፡ የተባበረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(ሐ) ሆን ፡ ብሎ ፡ መርከቡን ፡ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ ከተጫነው ፡ ሥንቅ ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ የሰረቀ ፡ ወይም ፡ ያበላሸ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ ሲፈረድበት ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት፡ ይቀጣል ።

## ቊ ፡ ፫፻፷ ። ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ የመርከቡን ፡ ካፒቴን ፡ ሥልጣን ፡ መቀማት ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ እንዳይሠራ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

በባሕር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የማንኛውንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ወይም፡ በሕግ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠውን ፡ የሌላ ፡ መኰንን ፡ የመርከብ ፡ አዛዥነት ፡ ሥልጣን ፡ የቀማ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ በሥልጣኑ ፡ እንዳይሠራ ፡ የከለከለ ፡ ወይም፡ በሕግ ፡ በተፈቀደለት ፡ ሥልጣኑ ፡ እንዳይሠራ ፡ ያሰናከለ ፡ ሰው ፤ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ካ፲ ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

BACK



ቍ ፡ ፫፻፷፩ ። ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መርከብ ፡ መተው ።

(፩) ማንኛውም ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ችግር ፡ (ሥቃይ) ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መርከቡን ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ በተፈረደበት፡ ጊዜ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) ማንኛውም ፡ መርከበኛ ፡ ችግር ፡ (ሥቃይ) ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት፡ መርከቡን ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ ሲፈረድበት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፪ ። ከመርከቡ ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ ጥፋቶች ።

ማንኛውም ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ (መሐንዲስ) ፡ እንጂኔር ፤

(ሀ) ሐሰት ፡ ነገር ፡ የመዘገበ ፡ ወይም ፡ እንዲመዘገብ ፡ ያደረገ ፤

(ለ) ሆነ ፡ ብሎ ፡ በመዝገብ ፡ መመዝገብ ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ያልመዘገበ ፡ ወይም ፡ እንዲመዘገብ ፡ ያላደረገ ፤

(ሐ) በመርከቡ ፡ የዕለት ፡ ሁኔታ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ተጠብቀው ፡ እንዲኖሩ ፡ በታዘዙ ፡ የመርከብ ፡ ሰነዶች ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገበውን ፡ ጉዳይ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የለወጠ ፡ ወይም ፡ እንዲለወጥ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ካ፳፻ ፡ የኢት/ ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጫ ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፫ ። ግጭት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ግጭቱን ፡ ሳያስታውቁ ፡ ስለ ፡ መቅረት ።

ማንኛውም ፡ መርከብ ፡ ከመርከብ ፡ ጋራ ፡ በተጋጨ ፡ ጊዜ ፤

(ሀ) የመርከቡን ፡ ስም ፤

(ለ) የተመዘገበበትን ፡ ወደብ ፤

(ሐ) የሚሄድበትንና ፡ በመጨረሻ ፡ የሚደርስበትን ፡ ወደብ ፡ ለተጋጨው ፡ ለሌላው ፡ መርከብ ፡ ካፒቴን ፤ ያልገለጸ ፡ የማንኛውም ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ካ፩ሺ ፡ የኢት/ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፬ ። መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችልበትን ፡ ሁኔታ ፡ ሳያረጋግጥ ፡ የቀረ ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ ካፒቴን ።

(ሀ) መርከቡ ፡ ጕዞውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ለመቀጠል ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ፡ ወይም ፡

(ለ) ስለ ፡ መርከበኞቹ ፡ ስለ ፡ ተሳፋሪዎቹ ፡ ወይም ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙት፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ደኅንነት ፡ የሚገባውን ፡ የጥበቃ ፡ ጥንቃቄ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ የመርከብ ፡ ባለሀብት ፡ ወይም ፡ ካፒቴን ፡ ጥፋቱ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ከ፪ሺ ፡ የኢት/ ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፭ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግዴታዎቹን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ።**

ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መርከብ ፡ ካፒቴን ፡—

(ሀ) አንድ ፡ ሰው ፡ አሳፍሮ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲያደርስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ኀላፊ ፡ የሆኑለትን ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ አላሳፍርም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) በእርሱና ፡ በቦታኞቹ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ተነሣው ፡ ጸብ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት፡ ችሎታ፡ ያለው፡ ባለሥልጣን፡የሰጠውን፡ ውሳኔ፡ ያልጠበቀ፡ እንደ፡ ሆነ፤ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ፡በተፈረደበት፡ ጊዜ፡ከ፭፻፡ የኢት/ብር፡በማይበልጥ፡መቀጮ፡ይቀጣል።

**ቍ፡ ፫፻፹፮። በቂ ፡ ችሎታ፡ ሳይኖረው ፡ የመርከብ፡ ረዳት፡ ካፒቴን፡ ሆኖ፡ ስለ ፡ መሥራት።**

(፩) በሕግ ፡ የተደነገጉት ፡ ችሎታዎች ፡ ሳይኖሩት ፡ ራሱ ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ ረዳት ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ እንጂኔር ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ እንዲሾም ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ጥፋተኛ፡ ሆኖ፡ በተፈረደበት፡ ጊዜ ፡ ከ፩፡ ሺሕ፡ የኢት/ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሕግ ፡ የተደነገጉት ፡ ችሎታዎች ፡ የሌሉት ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ እንዲሠራ ፡ ማንኛቸውንም ፡ ሰው ፡ የቀጠረ ፡ የመርከብ ፡ ካፒቴን ፡ ወይም ፡ የመርከብ ፡ ባለሃብት ፡ ጥፋቱ ፡ ተረጋግጦ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ከ፩ ፡ ሺሕ ፡ የኢት/ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፯ ። ስለ ፡ ዲሲፕሊን ፡ ጥፋቶች ።**

የዲሲፕሊን ፡ ጥፋቶች ፡ በልዩ ፡ ደንብ ፡ ይደነገጋሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፰ ። ስለ ፡ ቅጣቶች ።**

የዚህን ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የጣሰ ፡ ወይም ፡ የተለየ ፡ ቅጣት ፡ ያልተወሰነላቸውን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የወጡትን ፡ ደንቦች ፡ የጣሰ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ፡ በተፈረደበት ፡ ጊዜ፡ ከ፩፡ ሺሕ ፡ የኢት/ብር፡ በማይበልጥ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፱ ። ሌሎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ቅጣት ፡ እንዳያገኘው ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ እንዳይቀርብ ፡ መከላከያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

## አንቀጽ ፡ ፱ ።

## ልዩ ፡ ልዩ ።

**ቍ ፡ ፫፻፺ ። ትርጓሜ ።**

ይህ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለሚውልበት ፡ ጕዳይ ፡ ሁሉ ፡ የሚከተሉት ፡ ቃላቶችና ፡ አግባቦች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ፍቺ ፡ ይኖራቸዋል ።

“መንግሥት ፡ ” ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ን. ነ. መንግሥት ፡ ነው ።

BACK



"ሚኒስትር ፡" ማለት ፡ የመከላከያ ፡ ሚኒስትር ፡ ነው ።
"ድንጋጌ ፡" ማለት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ የወጣ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፩ ። ደንብ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ ሥልጣን ።**

(፩) የባሕር ፡ ክፍል ፡ በሚያቀርበው ፡ አሳብና ፡ ማሳሰቢያ ፡ መሠረት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆንበትን ፡ ደንብ ፡ ለማውጣት ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተመለከተው ፡ ሥልጣን ፡ ጠቅላላ ፡ መሆኑ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ ደንቦች ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(ሀ) ማንኛውንም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚደነገገውን ፡ ወይም ፡ መደንገግ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ደንብ ፤

(ለ) ስለሚሠሩባቸው ፡ ፎርሞች ፤

(ሐ) ስለሚከፈሉት ፡ ኪራዮችና ፡ ቀረጦች ፤

(መ) መርከቦች ፡ ጕዞዋቸውን ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ በሚችሉበት ፡ ሁኔታ ፡ የተዘጋጁ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ፡ ፍተሻና ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ማንኛውንም ፡ ጕዳይ ፤

(ሠ) የመርከብ ፡ አመዘጋገብ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሥርዐትና ፡ መከተለም ፡ ስለሚገባቸው ፡ ሁኔታዎች ፤

(ረ) ለመርከብ ፡ ነጂዎች ፤ ለወደብ ፡ ሹሞች ፤ ለእንጂኔሮችና ፡ ለመርከበኞች ፤ ፈቃድ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሥርዐትና ፡ መከተልም ፡ ስለሚያስፈልጉት ፡ ሁኔታዎች ፤

(ሰ) ስለ ፡ መርከበኛ ፡ የሥራ ፡ ውልና ፡ ሁኔታ ፤

(ሸ) ስለ ፡ መርከብ ፡ አነዳድና ፡ አመራር ፤

(ቀ) አደገኛ ፡ የሆኑ ፡ ጭነቶች ፡ ስለሚጫኑበት ፡ ሥርዐትና ፡ መጠበቅም ፡ ስለሚገባቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ ሁኔታዎች ፤

(በ) ስለ ፡ መርከብ ፡ ክብደት ፡ አለካክ ፡ ሥርዐትና ፡ መከተልም ፡ ስለሚያስፈልጉት ፡ ደንቦች ፤

(ተ) ከባሕር ፡ አደጋ ፡ ሕይወትን ፡ የማዳን ፡ ተግባር ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፤

(ቸ) ከወደቦችና ፡ ከወደብ ፡ ሥራ ፡ ደንቦች ፡ ጋራ ፡ግንኙነት ፡ ስላላቸው ፡ ጕዳዮች ፤

(ኀ) ስለ ፡ መብራትና ፡ ፋናዎች ፤

(ነ) ደንቦች ፡ በተጣሱ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሰጡት ፡ ቅጣቶች ፤

(፫) ሚኒስትሩ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ በሚወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ በቍጥር ፡ ፹፮ና ፡ ፪፻፷፫ ፡ የተወሰነውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ማሻሻል ፡ ይችላል ።